የገንዘብ ሚኒስቴር

**MINISTRY OF FINANCE**

# መመሪያ ቁጥር 1070/2017
# በፌዴራል መንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የግዥ አፈጻጸም መመሪያ

ግንቦት, 2017 ዓ.ም

**May, 2025**

ማውጫ ገጽ


ምዕራፍ አንድ ........ 2

ጠቅላላ........ 2

1. አጭር ርዕስ ........ 2
2. ትርጓሜ ........ 2
3. የተፈፃሚነት ወሰን ........ 4

ምዕራፍ ሁለት ........ 4

ተግባርና ኃላፊነት........ 4

4. የግዥና ንብረት ባለስልጣን ተግባርና ኃላፊነት ........ 4
5. የመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያው ወይም ተቆጣጣሪ አካል ተግባርና ኃላፊነት........ 5
6. የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ዳይሬክተሮች ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት........ 5
7. የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ተግባርና ኃላፊነት ........ 6
8. የግዥ ሥራ ክፍል ተግባርና ኃላፊነት........ 7
9. የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት ........ 8
10. የቴክኒክ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት ........ 9
11. ተጠያቂነት ........ 10

ምዕራፍ ሶስት ........ 10

መሠረታዊ የግዥ ድንጋጌዎች ........ 10

ክፍል አንድ ........ 10

የግዥ ዕቅድ ........ 10

12. የግዥ ዕቅድ ማዘጋጀት........ 10
13. የፕሮጀክት ግዥ ስትራቴጂ........ 11

ክፍል ሁለት ........ 11

የኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓት፣ የግዥ ሠነዶችና መረጃዎች ........ 11

14. የኤሌክትሮኒክ ግዥ ስርዓት ........ 11
15. የግዥ ሰነዶችን ስለመያዝ ........ 11
16. የግዥ መረጃዎችን ለሕዝብ ይፋ ስለማድረግ ........ 12

ክፍል ሦስት........ 12

የተወዳዳሪዎች ቅድመ ብቃት መስፈርቶች ........ 12

17. ተወዳዳሪዎች ማሟላት ያለባቸው የቅድመ ብቃት መስፈርቶች........ 12
18. የጥቅም ግጭት ........ 14
19. የቀድሞ ሰራተኞች በጨረታ ስለሚሳተፉበት አግባብ........ 15

ክፍል አራት........ 16

ዘላቂነት ያለው የግዥ ሥርዓት ተፈጻሚ ስለማድረግ ........ 16

20. የሕይወት ዘመን ወጪ ትንተና........ 16
21. የአካባቢ ጥበቃን ታሳቢ ያደረገ ግዥ ........ 18
22. የማህበረሰብ ተጠቃሚነትን ታሳቢ ያደረገ ግዥ ........ 18

ክፍል አምስት ........ 18

የግዥ ስነ ምግባር ........ 18

23. ጠቅላላ ድንጋጌ ........ 18
24. ሚስጥርን መጠበቅ........ 18
25. የጥቅም ግጭትን በተመለከተ ........ 19

26. ፍትሐዊነት ........ 20
27. ግልጽነት ........ 21
ምዕራፍ አራት ........ 21
የግዥ ዘዴዎች እና አፈጻጸማቸው ........ 21
28. የግዥ ዘዴዎች ........ 21
ክፍል አንድ ........ 21
ብሔራዊ ግልጽ ጨረታ ........ 21
29. ብሔራዊ ግልጽ ጨረታ አፈጻጸም ........ 21
30. ዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ አፈጻጸም ........ 23
31. ዓለም አቀፍ ግዥዎች ........ 25
የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ ........ 25
32. የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ አፈጻጸም ........ 25
የሁለት ደረጃ ጨረታ ........ 27
33. የሁለት ደረጃ ጨረታ ግዥ አፈጻጸም ........ 27
የፍላጎት መግለጫ መጠየቂያ ጨረታ ........ 29
34. የፍላጎት መግለጫ መጠየቂያ ጨረታ አፈጻጸም ........ 29
35. በጥራት እና በዋጋ ላይ የተመሰረተ መረጣ ........ 31
36. በጥራት ላይ የተመሠረተ መረጣ ........ 32
37. በቁርጥ በጀት ላይ የተመሰረተ መረጣ ........ 33
38. በዝቅተኛ ዋጋ ላይ የተመሠረተ መረጣ ........ 34
39. በአማካሪዎች ብቃት ላይ የተመሠረተ መረጣ ........ 35
40. በተገደበ ጨረታ የግዥ አፈጻጸም ........ 35
41. በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ አፈጻጸም ........ 39
42. በቀጥታ የሚፈጸም ግዥ አፈጻጸም ........ 42
43. ልዩ የቀጥታ ግዥ አፈጻጸም ........ 47
44. በልዩ ፈቃድ የሚፈጸም ግዥ አጠቃላይ ድንጋጌ ........ 52
45. የልዩ ሁኔታ ፈቃድ አቀራረብና ምላሽ አሰጣጥ ላይ መከተል የሚገባቸው መርሆዎች ........ 52
46. የልዩ ፈቃድ አቀራረብና ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ........ 53
ምዕራፍ አምስት ........ 53
የግዥ ስልቶች ........ 53
47. የግዥ ስልት ዓይነቶች ........ 53
48. በስትራቴጂክ አጋርነት የሚፈጸም ግዥ ........ 54
49. አቅራቢዎች የሚመረጡበት ሂደት ........ 55
50. የቅድመ ብቃት ሰነዶች ምዘናና ግምገማ ........ 56
51. የግዥ አፈጻጸም ዘዴዎች ........ 57
52. የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ አፈጻጸም ........ 58
53. የማዕቀፍ ስምምነት ውል አፈጻጸም ........ 58
54. በጋራ የሚፈጸም ግዥ አፈጻጸም ........ 60
55. በሊዝ ስምምነት የሚፈፀም ግዥ አፈፃፀም ........ 61
56. በራስ ኃይል የሚከናወን ግዥ አፈፃፀም ........ 61
57. የተርንኪ ግዥ አፈፃፀም ........ 62
58. የኤሌክትሮኒክ ልውጥ ሀራጅ ጨረታ አፈጻጸም ........ 63
ምዕራፍ ስድስት ........ 63
ለግንባታ ሥራ ግዥ የብቃት መስፈርቶች ........ 63

59. የግንባታ ሥራ አፈፃፀም ምዘና ........ 63
60. የግንባታ ስራ ግዥ አጠቃላይ ልምድ ........ 64
61. ግንባታ ሥራ ግዥ ተዛማጅ የስራ ልምድ ........ 64
62. የግንባታ ስራ ግዥ የፋይናንስ አቋም ........ 66
63. የግንባታ ስራ ግዥ ዓመታዊ የተርንኦቨር መጠን ........ 66
64. የባለሙያዎች የትምህርት ዝግጅትና ብቃት ........ 67
65. የግንባታ ስራ መሳሪያ ማሟላት ........ 68
66. ከአንድ በላይ በሆኑ የግንባታ ስራዎች ላይ የልምድ አያያዝ ........ 68
67. ለህንፃ ግንባታ ስራ የሚጠየቅ ዝቅተኛ መስፈርት ........ 69
68. ለድልድይ ግንባታ ስራ የሚጠየቅ ዝቅተኛ መስፈርት ........ 70
69. የመንገድ ፕሮጀክቶች አመዳደብ በንጣፍ ዓይነት ........ 71
70. ለመንገድ ፕሮጀክቶች የግንባታ ስራ የሚጠየቅ ዝቅተኛ መስፈርት ........ 71
71. ለግድብ ግንባታ ሥራ እና ለመስኖ ግንባታ ሥራ የሚጠየቅ ዝቅተኛ መስፈርት ........ 72
የጨረታ ሥነ ሥርዓት ........ 73
72. የጨረታ ጥሪ ማስታወቂያ ........ 73
73. የጨረታ ሰነድ ........ 74
74. የጨረታ ዝርዝር መረጃ ........ 75
75. የብቃትና የግምገማ መስፈርት አዘገጃጀት ........ 77
76. የጨረታ ቅፅና የዋጋ ማቅረቢያ ሠንጠረዥ ........ 77
77. የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ........ 78
78. አጠቃላይና ልዩ የውል ሁኔታዎች ........ 79
79. ጨረታ ተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ የሚቆይበትን ጊዜ ስለመወሰን ........ 80
80. ስለ ናሙና አቀራረብ ........ 80
81. በጨረታ ሰነድ ላይ ስለሚደረግ ማብራሪያ ወይም ማሻሻያ ........ 82
82. የጨረታ ቋንቋ ........ 84
83. የመጫረቻ ዋጋ ........ 85
84. የመጫረቻ ሰነድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ........ 85
85. የጨረታ ማስከበሪያ ........ 86
86. የመጫረቻ ሰነድ አቀራረብ ........ 87
87. የጨረታ አከፋፈት ........ 87
88. ጨረታን መገምገምና ማወዳደር ........ 89
89. የሒሳብ ስህተቶችን ስለማረም ........ 92
90. የተሰበረ እና የተጋነነ የጨረታ ዋጋ ........ 93
91. ከተጫራቾች ጋር ስለሚደረግ ድርድር ........ 94
92. ጨረታን ማፅደቅ ........ 95
93. ድህረ ግምገማ ........ 96
94. የጨረታ ውጤትን እና አሸናፊነት ማሳወቅ ........ 97
95. ጨረታን ስለመሰረዝ ........ 98
ምዕራፍ ስምንት ........ 99
የውል አስተዳደር ........ 99
96. የውል አጠቃላይ ድንጋጌዎች ........ 99
97. የውል አዘገጃጀት ........ 99
98. የውል ቅድመ ሁኔታዎች ........ 99
99. ውል መፈረም ........ 100
100. የተዋዋይ አካላት ኃላፊነት ........ 101
101. ውልን ይፋ ስለማድረግ ........ 102

102. ውል ስለማሻሻል ........ 103
103. የውል ማስከበሪያ ........ 103
104. የውልን አፈፃፀም መከታተል ........ 104
105. የቅድመ ክፍያ አከፋፈል ........ 105
106. የዋጋ ማስተካከያ ........ 106
107. ለግንባታ ሥራ ግዥ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ ........ 109
108. በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈፀም ግዥ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ ........ 109
109. ለምክር አገልግሎት ግዥ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ ........ 111
110. ርክክብ እና ፍተሻ ........ 111
111. ክፍያ ስለመፈጸም ........ 111
112. ውል ማጠናቀቅ ........ 112
113. የጉዳት ካሳ ........ 113
114. ውልን ስለማቋረጥ ........ 114
115. ከአቅም በላይ ሁኔታ ........ 114
116. ማስታወቂያዎችና የጽሑፍ ግንኙነቶች ........ 115
117. የውል አለመግባባቶችን ስለመፍታት ........ 115
ምዕራፍ ዘጠኝ ........ 116

የአቤቱታ እና ይግባኝ አቀራረብና አወሳሰን ሥርዓት ........ 116

118. አቤቱታና ይግባኝ አቀራረብ ጠቅላ ድንጋጌ ........ 116
119. አቤቱታን ለልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ስለማቅረብ ........ 116
120. አቤቱታ የሚቀርብበት ጊዜ ........ 117
121. የግዥ አፈጻጸም ሂደትን ማገድ ስለመቻላቸው ........ 118
122. የአቤቱታ የሚጣራበት ሂደት እና ውሳኔ አሰጣጥ ........ 118
123. ይግባኝ ለቦርዱ ስለሚቀብበት አግባብ ........ 119
124. ይግባኝ ለመደበኛ ፍርድ ቤት ስለማቅረብ ........ 119
ምዕራፍ አስር ........ 120

የጥፋተኝነት ሪፖርት የሚቀርብበት እና የሚጣራበት ሥርዓት ........ 120

125. *የጥፋተኖነት ሪፖርት አጠቃላይ ገጽታ* ........ 120
126. *የጥፋተኝነት ሪፖርት አቀራረብ* ........ 120
127. *የሚሰጡ ውሳኔዎች* ........ 121
128. ውሳኔውን እንደገና ማየት ........ 123
129. *መረጃን* ስለማቅረብ ........ 124
ምዕራፍ አስራ አንድ ........ 124

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ........ 124

130. የተሻሩ *መመሪያዎች* ........ 124
131. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ ........ 124
132. መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ ........ 124
አባሪ -5 ........ 130

## መመሪያ ቁጥር 1070/2017

## በፌዴራል መንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የግዥ አፈፃፀም መመሪያ

የፌዴራል መንግሥት ባለቤት የሆነባቸው የመንግሥት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ለትርፍ የተቋቋሙ እና ከግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ጋር ውድድር የሚያደርጉ በመሆኑ፣ እነዚህ ድርጅቶች ካላቸው ልዩ ባህሪ አኳያ ልዩ የግዥ አፈፃፀም መመሪያ የሚያስፈልጋቸው በመሆኑ፤

የፌዴራል መንግሥቱ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በዳይሬክተሮች ቦርድ በማጸደቅ ሲጠቀሙበት የነበረው የግዥ አፈጻጸም መመሪያ  የተለያዩ ክፍተቶች ያሉበት ከመሆኑም በተጨማሪ የተለያየ ይዘት ያለው በመሆኑ ድርጅቶቹ የተሻሻለ እና ወጥ የሆነ የግዥ አፈጻጸም መመሪያ እንዲኖራቸው ለማድረግ፣

በፌደራል መንግስት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 1314/2016 በተመለከተው መሰረት የልማት ድርጅቶቹ የንግድ የአሰራር ስርዓትን እና ትርፋማነታቸውን ጠብቀው እንዲሄዱ ለማድረግ የግዥ አፈጻጸማቸው በሚፈለገው ጥራት፣ ጊዜ፣ ቦታ እና የአቅርቦት አስተማማኝነት እንዲኖር በማድረግ የልማት ድርጅቶቹ የተቋቋሙበትን ዓላማ ለማሳካት እንዲችሉ እና ለግዥው የሚውለው ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ተመጣጣኝ ፋይዳ ማስገኘቱን ለማረጋገጥ፣

በመንግሥት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የግዥ አፈፃፀም ሥርዓት ሕግን ያልተከተሉ ውሳኔዎች እና እርምጃዎች ላይ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ፤

የገንዘብ ሚኒስቴር በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1333/2016 አንቀጽ 87(3) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

# ምዕራፍ አንድ
# ጠቅላላ

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "**በፌዴራል መንግስት ባለቤትነት የተያዙ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር** 1070/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላትና ሐረጎች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. **"አዋጅ"** ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የመንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1333/2016 ነው፡፡
2. **"ባለስልጣን"** ማለት በአዋጁ አንቀጽ 9 እንደገና የተቋቋመው የፌደራል የመንግስት የግዥና ንብረት አስተዳዳር ባለስልጣን ነው፡፡
3. **"የዳይሬክተሮች ቦርድ"** በፌዴራል መንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 1314/2016 አንቀጽ 15 መሰረት የተቋቋመው በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የመንግሥት የልማት ድርጅትቦርድ ነው፡፡
4. **"የመንግሥት የልማት ድርጅት የበላይ ኃላፊ"** ማለት በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የመንግሥት የልማት ድርጅትበበላይነት ለመምራት ኃላፊነት የተሰጠው ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣ ፕሬዚዳንት ወይም ተመሳሳይ የኃላፊነት ደረጃ ያለው ሰው ነው፡፡
5. **"የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ"** ማለት የልማት ድርጅቱ በሚፈጽማቸው ግዥዎች የወጡ ጨረታዎችን ወይም በሌሎች የግዥ ዘዴዎች የሚፈጸሙ ግዥዎችን መርምሮ የሚያፀድቅ እንዲሁም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11 መሰረት የተሰጠውን ኃላፊነት የሚወጣ ኮሚቴ ነው፡፡
6. **"የቴክኒክ ገምጋሚ ኮሚቴ"** ማለት ውስብስብና የቴክኒክ ግምገማ ለሚያስፈልጋቸው ግዥዎች የቴክኒክ ግምገማ በማድረግ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ በልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ የሚሰየም ኮሚቴ ነው፡፡
7. **"የግዥ የሥራ ክፍል"** ማለት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የሚኖራቸው የውስጥ አደረጃጀት እንደተጠበቀ ሆኖ የግዥ ዕቅድና የጨረታ ሠነድ የሚያዘጋጅ፣ እንደአስፈላጊነቱ የገበያ ጥናት የሚያካሂድ ወይም በሚመለከተው ክፍል ጥናቱ

እንዲከናወን የሚያደርግ፣ አጠቃላይ የግዥ ሂደትንና እንደአስፈላጊነቱ የውል አስተዳደር ሥራን ለማከናወን ኃላፊነት የተሰጠው የሥራ ክፍል ወይም ኮሚቴ ነው፡፡

8. **"የኢንዱስትሪ ግብዓቶች"** ማለት ለኢንዱስትሪዎች በጥሬ ዕቃነት ወይም በግብዓትነት የሚያገለግሉ ወይም በኢንዱስትሪዎች የማምረት ሂደት እሴት ተጨምሮባቸው ለሌሎች ኢንዱስትሪዎች ለግብዓትነት የሚጠቀሙባቸው በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቁ ምርቶች ናቸው፡፡

9. **"የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ"** ማለት የዕቃው፣ የአገልግሎቱ፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎቹ ወይም የምክር አገልግሎት ሊያሟላ የሚገባውን ጥራት፣ አቅም፣ ዓይነት፣ ደረጃ፣ የአካባቢ ተቀባይነት፣ ሙያዊ ድጋፍ፣ ድህረ ሽያጭ አገልግሎቶችን ጨምሮ በሁሉም ተጫራቾች መካከል ፍትሐዊ ውድድርን ሊያስገኝ በሚያስችል መልኩ የተዘጋጀ የፍላጎት መግለጫ ነው፡፡

10. **"ጠቅላላ ዋጋ"** ማለት ለአንድ ግዥ አፈጻጸም ታክስን ጨምሮ ማናቸውም ሌሎች ወጪዎችን በማካተት ለሚፈፀም ግዥ የሚከፈል ዋጋ ነው፡፡

11. **"የሊዝ ስምምነት"** ማለት የመንግሥት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በግዥ ምትክ ወጪ ሊቆጥቡ የሚችሉ፣ ተለዋዋጭነት እና የቅርብ ጊዜ ቴክኖሎጂን መጠቀም የሚያስችሉ ንብረቶችን በሊዝ ስምምነት ለተወሰነ ጊዜ ማግኘት የሚችሉበትን ሁኔታ የሚገልጽ ውል ነው፡፡

12. **"የጨረታ ማስከበሪያ"** ማለት ተጫራቾች በጨረታው ተሳታፊ ከሆኑበት ጊዜ ጀምሮ ውል እስከሚፈርሙበት ጊዜ ድረስ በጨረታ ሰነዱ ላይ በሚገለጸው ዓይነትና መጠን መሠረት የሚያሲዙት ዋስትና ነው፡፡

13. **"የኤሌክትሮኒክ ግዥ"** ማለት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ዕቃዎችን፣ አገልግሎቶችን፣ የምክር አገልግሎቶችን እና የግንባታ ዘርፍ ሥራዎችን ግዥ በኢሜይል ወይም በቀጥታ የመረጃ መረብ ወይም በኤሌክትሮኒክ ግብይት ወይም ሌሎች የኤሌክትሮኒክ የግዥ ዘዴዎችን በመጠቀም ግዥ የሚፈጸምበት ሥርዓት ነው፡፡

14. **"የኤሌክትሮኒክ ልውጥ ሐራጅ ጨረታ"** ማለት ተጫራቾች በመንግሥት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ለሚፈለጉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የመረጃ መረብን በመጠቀም ዋጋ በመቀነስ የሚወዳደሩበት ስልት ሲሆን ዝቅተኛ ዋጋ ላቀረበው ተጫራች አሸናፊ የሚሆንበት የግዥ ስልት ነው፡፡

15. **"የታገዱ አቅራቢዎች ዝርዝር"** ማለት ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ በልማት ድርጅቶች ወይም በመንግስት መ/ቤቶች በሚፈጸም ግዥ ላይ እንዳይሳተፉ በባለስልጣኑ የታገዱ አቅራቢዎችን ዝርዝር የያዘ መረጃ ነው፡፡
16. **"ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ"** ማለት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሥራቸውን ለማከናወን ዓመታዊ ግዢያቸውን መቼ፣ በምን ያህል ገንዘብ እና እንዴት እንደሚፈጽሙ የሚያመለክት ሰነድ ነው፡፡
17. **"የጥምረት"** ወይም **"የእሽሙር ማህበር"** ማለት የንግድ ግብን ለማሳካት ወይም ግዥን ለመፈፀም ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ግለሰቦች፣ ኩባንያዎች ወይም ድርጅቶች የጋራ ሥራን ለማከናወን እና የጋራ ኃላፊነትን ለመወጣት የተቋቋመ ጊዜያዊ ወይም ቋሚ የትብብር ማህበር ወይም ጥምረት ነው፡፡
18. **"የስትራቴጂክ አጋርነት ግዥ"** ማለት አቅርቦትን አስተማማኝ ለማድረግ የልማት ድርጅቱ የሚያወጣውን ቅድመ ግምገማ መስፈርት የሚያሟሉ ድርጅቶችን በአቅራቢነት በመመዝገብ ለተወሰነ ጊዜ እነዚህን ድርጅቶች በማወዳደር ወይም በቀጥታ ግዥ የሚፈጸምበት ስልት ነው፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በፌዴራል መንግሥት ባለቤትነት በተያዙ የልማት ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት
# ተግባርና ኃላፊነት

## 4. የግዥና ንብረት ባለስልጣን ተግባርና ኃላፊነት

በአዋጁ ከተሰጡት ሥልጣን እና ኃላፊነቶች በተጨማሪ ባለስልጣኑ ከዚህ በታች የተገለጹት ኃላፊነቶችና ተግባራት ይኖሩታል፣

1) የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን የግዥ አፈጻጸምን መከታተል እና የአቅም ግንባታ ሥልጠና እና ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

2) በልማት ድርጅቶች የሚፈጸሙ ይህን አፈጻጸም መመሪያና ሌሎች አግባብነት ያላቸው አሰራሮችን ተከትለው መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ የግዥ ኦዲት፣ ክትትል እና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

3) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በተጫራቾች ወይም አቅራቢዎች ላይ ለሚያቀርቡት የጥፋተኝነት ሪፖርት በማጣራት ጥፋት የተፈፀመ መሆኑን ሲያረጋግጥ እንደጥፋቱ ክብደት ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡

4) የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ልዩ የስራ ባህሪን ታሳቢ ያደረገና በአዋጁና በዚህ የአፈጻጸም መመሪያ መሠረት በልማት ድርጅቶች የተዘጋጀውን የግዥ አፈጻጸም ማንዋል ያጸድቃል፡፡

## 5. የመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያው ወይም ተቆጣጣሪ አካል ተግባርና ኃላፊነት

ከልማት ድርጅቶች የግዥ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ በፌዴራል መንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 1314/2016 መሰረት የመንግሥት ሆልዲንግ ኩባንያው ወይም ተቆጣጣሪ አካሉ ከዚህ በታች የተገለጹት ዝርዝር ተግባራት እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

1) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የግዥ አፈፃፀም የኮርፖሬት አስተዳደር ሥርዓትን ይመራል፡፡

2) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ከተሰጣቸው ኃላፊነት እና የስራ ባህሪ አንጻር ወጥ የሆነ የግዥ ስራ ክፍል አደረጃጀት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

3) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የግዥ አፈጻጸማቸውን በዘመናዊ መንገድ እንዲፈጽሙ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

## 6. የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ዳይሬክተሮች ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት

ከግዥ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ዳይሬክተሮች ቦርድ ከዚህ በታች የተገለጹት ዝርዝር ተግባራት እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፣

1) የኢንቨስትመንት እና የካፒታል ግዥዎችን በጀት አፈፃፀም ሪፖርቶችን ይገመግማል፡፡

2) የውስጥ ኦዲት ወይም የቦርድ ኦዲት ንዑስ ኮሚቴ የሰጡት አስተያየትና የማስተካከያ ሀሳብ ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

## 7. የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ተግባርና ኃላፊነት

ከግዥ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ የልማት ድርጅቱ በላይ ኃላፊ ከዚህ በታች የተገለጹት ዝርዝር ተግባራት እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

1) የግዥ ስራን እንዲያከናውኑ የሚመደቡ ሰራተኞች እና ኃላፊዎች በዘርፉ በቂ የትምህርት ዝግጅት፣ የስራ ልምድ እና ጥሩ ሥነ- ምግባር ያላቸው መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

2) የልማት ድርጅቱን ግዥ አፈጻጸም ሂደት በዳይሬክተሮች ቦርድ በፀደቀው የግዥ ዕቅድ መሠረት መመራቱን ይከታተላል፡፡

3) የልማት ድርጅቱን ልዩ የስራ ባህሪን ታሳቢ ያደረገና በአዋጁና በዚህ የአፈጻጸም መመሪያ መሠረት የግዥ አፈጻጸም ማንዋል በማዘጋጀት በባለስልጣኑ ያጸድቃል፡፡

4) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የግዥ ግምገማ የሚያከናውኑ፣ ከአቅራቢዎች ለሚቀርቡ አቤቱታዎች አጣርቶ ምላሽ የሚሰጡ፣ ግዥ የሚያጸድቁ፣ የግዥ ገምጋሚ ኮሚቴ፣ የቴክኒክ ኮሚቴ ወይም የዋጋ ድርድር የሚያደርጉ ቡድኖችን ያቋቁማል፡፡

5) በተለያዩ የግዥ ዘዴዎች ግዥ ለመፈጸም የሚቀርቡትን የግምገማ ውሳኔ ሀሳቦችን መርምሮ ማጽደቅ ወይም በየደረጃው ላሉ ለሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች እንዲያጸድቁ ውክልና ይሰጣል፡፡

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉና ከሶስት ያላነሱ አባላት ያሉት የልማት ድርጅቱን ከፍተኛ ግዥዎች መርምሮ የሚያጸድቅና ከ3 (ሦስት) ዓመት የማይበልጥ የአገልግሎት ዘመን የሚኖረው፣ እንደአስፈላጊነቱ ከአንድ በላይ የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፣ የሚቻል ሲሆን የኮሚቴው አባላት በተቻለ መጠን ከተለያየ የሙያ ዘርፍ የተውጣጡ፣ በልማት ድርጅቱ የተሻለ ዕውቀት እና የስራ ልምድ ያላቸው መሆኑን ያረጋግጣል፤

7) የልማት ድርጅቱ ባለው አደረጃጀት ምክንያት የተለያዩ ቅርንጫፍ፣ ፕሮጀክት ጽ/ቤቶች፣ ፋብሪካዎች ያለው ሲሆንና ስራዎችን በአግባቡ ለመወጣት ያመቻል

ብሎ ሲያምን ጽ/ቤቶቹን በበላይነት ለሚመሩ ኃላፊዎች ከግዥ ዕቅድ ዝግጅት ውጭ ያሉ የግዥ ስራዎችን እንዲመሩ፣ እንዲያስፈጽሙ ውክልና የመስጠት፤

8) እንደአስፈላጊነቱ ውስብስብ ለሆኑ እና ዝርዝር የቴክኒክ ግምገማ ለሚፈልጉ ግዥዎች ጊዜያዊ ወይም ቋሚ የቴክኒክ ገምጋሚ ኮሚቴ ያቋቁማል፡፡

9) የግዥ ዕቅዱን እና በበጀት ዓመቱ ከተያዘው እቅድ ውጪ የሆኑ ግዥዎችን ያጸድቃል፡፡

10) በዚህ የአፈጻጸም መመሪያ መሠረት ከተፈቀዱ የግዥ ዘዴዎች፣ ሰነዶች፣ አሰራሩን ከሚመሩ የጨረታ ሰነዶችና ቅጾች መሰረት ማድረግ ግዥ ለመመፈጸም በማይቻልበት ወቅት ግዥ ልዩ ፈቃድ ጥያቄዎችች አግባብነት አይቶ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

11) በግዥ ኦዲት ግኝቶች ላይ በተሰጡ አስተያቶች መሠረት ተገቢ ማስተካከያ መደረጉን ይከታተላል፡፡

12) በዚህ መመሪያ ለቀጥታ ግዥ ዘዴ የተቀመጡት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ ግዥው በዚህ ዘዴ እንዲፈጸም ይወስናል፤

13) የልማት ድርጅቱ በሚፈፅመው ግዥ ላይ ለሚቀርብ አቤቱታ አጣርቶ ምላሽ ይሰጣል፣

14) የውል ሰነድ ይፈርማል ወይም እንደአስፈላጊነቱ ውል የመፈረም ውክልና ይሰጣል፣ በውሉ መሠረትም ግዥው መፈፀሙን ይከታተላል፡፡

15) እንደአስፈላጊነቱ የግዥ ባለሙያዎች ወደ ስራ ከመግባታቸው በፊት ከሚመለከተው አካል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያላቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ፣ የሥራ እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ ይገመግማል፡፡ ማስተካከያ ሲያስፈልግ እንደ አስፈላጊነቱ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፡፡

## 8. የግዥ ሥራ ክፍል ተግባርና ኃላፊነት

የግዥ የስራ ክፍል ከዚህ በታች የተገለጹት ዝርዝር ተግባራት እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፣

1) የግዥ ፍላጎት በማሰባሰብ ዓመታዊው የግዥ ዕቅድ በወቅቱ በማዘጋጀት ለልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ያቀርባል፡፡

2) ከሌሎች የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ፍላጎት ጋር በጣምራ የሚፈፀሙ ግዥዎችን እና በሦስተኛ ወገን የሚከናወኑ ግዥዎችን ይለያል፣ ይከታተላል፣ ያስተባብራል፡፡

3) የጨረታ ሰነድ ያዘጋጃል፣ ጨረታ ይከፍታል፣ የጨረታ ማስከበሪያ ይቀበላል፣ በጨረታ ሰነዱ በተገለጹት ሁኔታዎች መሠረት የጨረታ ማስከበሪያውን ለልማት ድርጅቱ ገቢ ያደርጋል ወይም ተመላሽ ያደርጋል፡፡

4) ከተጫራቾች የሚቀርቡ የመጫረቻ ሰነዶችን ጨምሮ ሌሎች አስፈላጊ የግዥ ሰነዶችን ይይዛል፣ ከሚመለከታቸው ሕጋዊ አላካት ማብራሪያ ሲጠየቅ ተገቢውን ማብራሪያ ይሰጣል፡፡

5) የመጫረቻ ሰነዶችን ይገመግማል ወይም እንዲገመገም ያደርጋል፣ የጨረታው ውጤት እና የአሸናፊነት ማስታወቂያ ለተጫራቾች ያሳውቃል፡፡

6) የአቅራቢዎች ቅድመ ምዝና መስፈርቶችን ያዘጋጃል፣ የአቅራቢ ዝርዝር ምዝገባ ያከናውናል፣ ለበላይ ኃላፊ አቅርቦ ያጸድቃል፡፡

7) የግንባታ ሥራዎች፣ የዕቃ፣ እና አገልግሎት ግዥዎችን በተመለከተ የገበያ ጥናት ያደርጋል፣ የጥናቶቹን ውጤት በማጠናቀር ለቀጣይ ግዥዎች እንደ ግብዓት እንዲውሉ ያደርጋል፤

8) በተደጋጋሚ የሚፈጸሙ እና ዋጋቸው በቀላሉ ሊታወቁ የሚችሉ በዋጋ ማቅረቢያ ዘዴ የሚፈጸሙ ግዥዎችን ጨምሮ በልማት ድርጅቱ በሚፈጸሙ ግዥዎች በአሸናፊነት የሚመረጡት የአቅራቢዎች ዋጋ የገበያ ዋጋ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

9) የተለየ የውል አስተዳደር የሥራ ክፍል ከሌለ በስተቀር፣ የውል አፈጻጸም መከታተያ ሠነድ በማዘጋጀት የዋጋ ማቅረቢያን ጨምሮ ከልማት ድርጅቱ ጋር ውል የገቡ አቅራቢዎች ያላቸውን አፈጻጸም መገምገምና መረጃዎችን አደራጅቶ በመያዝ ለልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ያሳውቃል፡፡

## 9. የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

ግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ከዚህ በታች የተገለጹት ዝርዝር ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፣

1) የሚቀርብለትን የግዥ ግምገማ ሪፖርቶችን መርምሮ ያፀድቃል፣እንዲስተካከል ወይም እንዲሰረዝ ያደርጋል፡፡
2) በቀረበው የግዥ ግምገማ ሪፓርት ላይ የሚሰጥ ማንኛውም ዓይነት የኮሚቴው ውሳኔ ምክንያታዊ መሆን አለበት፡፡
3) የአፈጻጸም መመሪያውን እና ሌሎች የአፈጻጸም ሥርዓቶች በተሻለ ሁኔታ ሊፈጸሙ የሚችሉበትን አሰራር የልማት ድርጅቱን የበላይ ኃላፊ ያማክራል፡፡
4) በኮሚቴው ስለተከናወኑ የግዥ ተግባራት፣ ስለአጋጠሙ ችግሮች እና የመፍትሔ ሀሳቦች የሚገልጽ ሪፖርት ለልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ያቀርባል፡፡
5) በአጽዳቂ በኮሚቴው ስለተወሰኑ ውሳኔዎች በሚመለከተው አካል ሲጠየቅ ማብራሪያ ይሰጣል፡፡
6) እንደአስፈላጊነቱ ግዥውን ለማፅደቅ ከሌሎች ተቋማት የሙያ ድጋፍ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

## 10. የቴክኒክ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

በልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ የሚቋቋመው የቴክኒክ ኮሚቴ ከዚህ በታች የተገለጹት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡፡

1) ኮሚቴው ሊኖረው የሚገባው የአባላት ቁጥር እንደ ግዥው ግምታዊ የገንዘብ መጠን እና ውስብስብነት በበላይ ኃላፊው የሚወሰን ሆኖ ከሶስት ያላነሰ መሆን አለበት፡፡
2) የቴክኒክ ዶክመንት ተቀብሎ በጨረታ ሰነዱ በተቀመጠው ዝርዝር መግለጫ መሠረት ግምገማ ያከናውናል፡፡
3) የቴክኒክ ግምገማውን ውጤት ለግዥ የሥራ ክፍል ወይም ለግዥ ኮሚቴዉ ያቀርባል፡፡
4) እንዳስፈላጊነቱ የቴክኒክ መስፈርት ማዘጋጀት እንዲሁም የግዥው ርክክብ ሲካሄድ በቴክኒክ መስፈርቱ መሠረት መሆኑን ሊያረጋገጥ ይችላል፡፡
5) በቴክኒክ ግምገማው ዙሪያ ማብራሪያ ሲጠየቅ ተገቢውን ማብራሪያ ይሰጣል፡፡

## 11. ተጠያቂነት

የመንግሥት የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ፣ የግዥ የሥራ ክፍሎችን የሚመሩ ኃላፊዎች፣ ለግዥ ሥራ የተመደቡ ሠራተኞች፣ ባለሙያዎች፣ እንዲሁም የግዥ አጽዳቂ እና ሌሎች ኮሚቴዎች አባላት ስለሚወስዷቸው ይህንን መመሪያ እና ሕግን ያልጠበቁ እርምጃዎች ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

# ምዕራፍ ሶስት
# መሠረታዊ የግዥ ድንጋጌዎች
# ክፍል አንድ
# የግዥ ዕቅድ

## 12. የግዥ ዕቅድ ማዘጋጀት

1) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ያላቸውን የግዥ ፍላጎት ከሥራ ፕሮግራም፣ ጊዜ እና በጀት አንጻር ዓመታዊ የግዥ ዕቅዳቸውን ማዘጋጀት አለባቸው፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚዘጋጀው የግዥ ዕቅድ እስከተቻለ ድረስ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፡፡

   ሀ/ የግዥውን ዓይነትና ዘዴ፣

   ለ/ የግዥውን መጠን፣

   ሐ/ የግዥውን መግለጫ፣

   መ/ ለግዥው የሚያስፈልገውን ግምታዊ ዋጋ፣ በጀት እና የፋይናንስ ምንጭ፣

   ሠ/ ለግዥው ተስማሚ የሆነ የውል ዓይነት፣

   ረ/ ዋና ዋና የግዥ አፈጻጸም ተግባራት የሚከናወኑበትን ጊዜ የሚያመለክት መርሐ- ግብር፣ እና

   ሰ/ ሌሎች እንደ የልማት ድርጅቱ ባህሪ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን፣

3) የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ እስከ ሐምሌ 30 ባለው ጊዜ ውስጥ የልማት ድርጅቱን የግዥ ዕቅድ ማጽደቅ ይኖርበታል፡፡
4) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የግዥ ዕቅዳቸውን በማንኛውም ጊዜ ሊያሻሽሉ ይችላሉ፡፡

## 13. የፕሮጀክት ግዥ ስትራቴጂ

1) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች  ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ የሚሆን የፕሮጀክት ግዥ ስትራቴጂ ማዘጋጀት አለባቸው፡፡

2) የፕሮጀክት ግዥ ስትራቴጂው ቢያንስ ፕሮጀክቱን ለማሳካት የሚያስችሉ የግዥ ፍላጎትና ዓይነት፣ የገንዘብ መጠን፣ በግዥው ወቅት ሊያጋጥም የሚችለውን ስጋትና ማቅለያ መንገዶች፣ የገበያ ጥናት፣ አማራጭ የግዥ ዘዴ እና የውል ዓይነት ያካተተ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

# የኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓት፣ የግዥ ሠነዶችና መረጃዎች

## 14. የኤሌክትሮኒክ ግዥ ስርዓት

1) የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ልዩ የስራ ባህሪ፣የመፈፀም አቅም እንዲሁም የቴክኖሎጂውን ዝግጁነት መሠረት በማድረግ የግዥ ሂደታቸውን የኤሌክትሮኒክ ዘዴን በመጠቀም ሊያከናውኑ ይችላሉ፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የግዥ ሂደታቸውን ሙሉ በሙሉ በኤሌክትሮኒክ ስርዓት እስኪፈጽሙ ድረስ ከግልጽ ጨረታ ማስታወቂያዎች በስተቀር በልማት ድርጅቶች እና በአቅራቢዎች መካከል የሚደረጉ የመረጃ ልውውጦችና ግንኙነቶች በኢሜል ወይም በቀጥታ የመረጃ መረብ ወይም በሌሎች ኤሌክትሮኒክ ዘዴዎች ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡

## 15. የግዥ ሰነዶችን ስለመያዝ

1) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ከዚህ በታች የተገለጹትን የግዥ ሰነዶች መያዝ አለባቸው፡፡

ሀ/ የግዥ መጠየቂያዎች፣

ለ/ የጨረታ ስነዶችና ማስታወቂያዎች፣

ሐ/ የመጫረቻ ሰነዶች፣

መ/ የግምገማ ሪፖርቶች እና ቃለ-ጉባኤዎች፣

ሠ/ የግምገማ የውስጥ ግንኙነት እና ውይይቶች፣

ረ/ የሂሳብ ስሌት ማስተካከያዎች፣

ሰ/ በልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ እና በገምጋሚ ኮሚቴ ወይም አጽዳቂ ኮሚቴዎች የተሰጡት የውሳኔ ሀሳብ እና ቃለ ጉባኤዎች፣

ሸ/ የውል መረጃዎች፣

ቀ/ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች አስፈላጊ ናቸው ብለው የሚያስቧቸውን ሌሎች የግዥ ሰነዶች፣

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ክፍያ ለመፈፀም እና ሌሎች ግዴታዎችን ለመወጣት አስፈላጊ የሆኑ ዋና የግዥ ሰነዶችን በፋይናስ ስራ ክፍል እንዲሁም ቅጂ ሰነዶችን ደግሞ በግዥ የሥራ ክፍሎች ይያዛሉ፡፡

## 16. የግዥ መረጃዎችን ለሕዝብ ይፋ ስለማድረግ

በደህንነት ምክንያት ከሚያዙ ሚስጥራዊ መረጃዎች በስተቀር በልማት ድርጅቶች የሚፈፀሙ ግዥዎች በጨረታው አሸናፊ ከተመረጠና የግዥ ውል ከተፈረመ በኂላ ዋና ዋና መረጃዎች በአምስት (5) የስራ ቀናት ውስጥ እንደ አስፈላጊነቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቱ ድረ ገጽ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ለሕዝብ ይፋ መደረግ አለባቸው፡፡

# ክፍል ሦስት

# የተወዳዳሪዎች ቅድመ ብቃት መስፈርቶች

## 17. ተወዳዳሪዎች ማሟላት ያለባቸው የቅድመ ብቃት መስፈርቶች

1) በአዋጁ አንቀጽ 24(1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በሚፈጽሙት ግዥ የሚወዳደሩ ድርጅቶች ወደ ዝርዝር ግምገማ ከማለፋቸው በፊት ከዚህ በታች የተገለጹትን የቅድመ ብቃት መስፈርቶችን ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ሀ/ በዘርፉ የታደሰ የንግድ ፈቃድ እና ተጫራቹ የውጭ ሀገር ከሆነ በሀገሩ የተሰጠ ህጋዊ ንግድ ፈቃድ መኖሩን፣

ለ/ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ወይም እንደአስፈላጊነቱ ለኤክሳይዝ ታክስ የተመዘገቡ መሆናቸውን የሚያሳይ ሰርተፊኬት ማቅረብ፣

ሐ/ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና፣

መ/ ተጫራቹ የተሰጠውን የጨረታ ቅጽ በአግባቡ መሙላት፤

ሠ/ በጨረታ እንዳይሳተፍ በባለስልጣኑ ያልታገደ መሆን፣

ረ/ የታክስ ክሊራንስ፣

ሰ/ እንዳስፈላጊነቱ የብቃት ማረጋገጫ ሰነዶች፣ ከአምራች ወይም ከአከፋፋዮች የሚሰጥ ውክልና ወይም የእሽሙር ማህበር መመስረቻ ሰነድ እንዲሁም ሌሎች በጨረታ ሰነዱ ውስጥ የተካተቱ ሰነዶች ተካተው መቅረብ፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ለ) የተደነገገው ቢኖርም የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ጠቅላላ ዋጋቸው ከብር 500,000 (አምስት መቶ ሺህ) ለማይበልጡ የአንድ ጊዜ ግዥዎች ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገቡ አቅራቢዎች እንዲወዳደሩ ሊፈቅዱ ይችላሉ፡፡

3) ተጫራቹ በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ላይ የተመዘገበ ካልሆነ በስተቀር የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ግዥ ላይ የሚሳተፉ ማናቸውም የሕግ ሰውነት ያላቸው ተቋማት፣ የሽርክና፣ የጥምረት ወይም የእሽሙር ማህበራት እንደ አንድ የቅድመ ብቃት መስፈርት በነዚሁ ተቋማት ላይ የተጠቃሚ ባለቤትነት መብት ያላቸውን ሰዎች የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው፡፡

4) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 አፈፃፀም የተጠቃሚ ባለቤትነት መብት በሚከተሉት ሁኔታዎች ይገለፃል፤

ሀ/ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ቢያንስ አስር በመቶ [10%] የሚሆነውን የድርጅቱን አክሲዮኖች ወይም የመምረጥ መብቶችን በባለቤትነት የያዙ ወይም የተቆጣጥሩ ሰዎች ፤

ለ/ በሌሎች መንገዶች በድርጅቱ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ወይም የሚቆጣጠሩ ሰዎችን ወይም

ሐ/ በባለቤትነት የተመዘገቡም ሆነ ያልተመዘገቡ ሆነው በድርጅቱ ላይ የመጨረሻ እና ውጤታማ ቁጥጥር ያላቸው ሰዎች፡፡

5) በተጫራቾች የሚቀርቡ የተጠቃሚ ባለቤትነት መብትን የሚገልጹ መረጃዎች ሀሰተኛ ያልተሟሉና ትክክለኛነት የሚጎላቸው መሆናቸው በመንግስት መ/ቤቶች ከተረጋገጠ፣ የቀረበውን የመጫረቻ ሰነድ በቅድሚያ ውድቅ በማድረግ በተጫራቹ ላይ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ለሚመለከተው አካል ሊያቀርቡ ይችላል፡፡

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 በተገለጸው መሠረት የቅድመ ብቃት መስፈርቶችን ያላሟሉ ተጫራቾች ወደሚቀጥለው ዝርዝር የግምገማ ደረጃ አያልፉም፡፡

7) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ተጫራቾች ከጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ውጪ ያሉ በተለያዩ ምክንያቶች የተጠየቁትን የህጋዊነት ሰነዶች ከመጫረቻ ሰነዳቸው ጋር አካተው ባያቀርቡም ተፈላጊ ሰነዶችን በቅድመ ግምገማ ወቅት እንዲያቀርቡ ተጠይቀው ካሟሉ ጨረታው ከመዘጋቱ በፊት የተሰጡ መሆናቸውን በማረጋገጥ በጨረታው እንዲቀጥሉ መደረግ አለበት፡፡

8) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተገለጸው መሠረት የቅድመ ብቃት መስፈርቶችን ያላሟሉ ተጫራቾች ወደ ቀጣይ ዝርዝር ግምገማ አያልፉም፡፡

9) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ቢኖርም ተወዳዳሪዎች በተለያዩ ምክንያቶች የተጠየቁትን የህጋዊነት ሰነዶች ከመጫረቻ ሰነዳቸው ጋር አካተው ባያቀርቡም ተጫራቾች ተፈላጊ ሰነዶችን በቅድመ ግምገማ ወቅት እንዲያቀርቡ ተጠይቀው የህጋዊነት ሰነዶች ጨረታው ከመዘጋቱ በፊት የተሰጡ ወይም ህጋዊ መሆናቸውን በማረጋገጥ በጨረታው እንዲቀጥሉ መደረግ አለበት፡፡

## 18. የጥቅም ግጭት

1) ዝርዝሩ እንደ ግዥው ዓይነት በመደበኛ የጨረታ ሰነዶች የሚቀመጥ ሆኖ፣ ማናቸውም ተወዳዳሪዎች የጥቅም ግጭት ሊኖራቸው አይገባም፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የጥቅም ግጭት ያላቸው መሆኑ የተደረሰባቸው ተጫራቾች ወደዝርዝር ግምገማ ሳይገቡ በቅድመ ብቃት መስፈርቶች ግምገማ ወቅት ውድቅ መደረግ አለባቸው::

3) ዝርዝሩ እንደ ግዥው ዓይነት በመደበኛ የጨረታ ሰነዶች የሚገለጽ ሆኖ ተጫራቾች በጨረታ ሂደት ውስጥ ከአንድ ወይም ከሌሎች አካላት ጋር የጥቅም ግጭት አለው ተብሎ የሚወሰደው፣

ሀ/ በወጣው ጨረታ ለሚገዙ ዕቃዎች፣ የግንባታ ሥራዎች እና አገልግሎቶች በሰነድ ዝግጅት ወይም በማማከር አገልግሎት ወይም ግንባታዎች ላይ ከተሳተፉ ድርጅቶች ጋር የጥቅም ግንኙነት ካለው፣

ለ/ ከሦስተኛ ወገን ጋር ባለው ግንኙነት ምክንያት መረጃዎችን በመስጠት በሌሎች ተጫራቾች እና በግዥ ፈፃሚው አካል የግዥ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ተፅዕኖ በማሳደር የጨረታውን ሂደት ሊያዛባ የሚችል ከሆነ፣

ሐ/ በጨረታ ሂደት ወቅት ከአንድ በላይ የመጫረቻ ሰነድ ያቀረበ እንደሆነ፣

መ/ ከአንድ በላይ የሆኑ ተጫራቾች ለአንድ የጨረታ ዓላማ አንድ ተወካይ ያላቸው ከሆነ፤

ሠ/ አንድ ተጫራች ተሳትፎ ከሚያደርግ የልማት ድርጅቱ ሰራተኛ ጋር የስራ ወይም የቤተሰብ ግንኙነት ያለው ከሆነ፤

ነው፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የጥቅም ግጭቶች ሲፈጠሩ ተጫራቹ ያላሳወቀ ከሆነ ወይም በማንኛውም ጊዜ የልማት ድርጅቱ ችግሩን ማወቅ ከቻለ ወይም በሚመለከተው አካል ማረጋገጥ ከተቻለ ተጫራቹን ከውድድር ውድቅ ወይም ውሉ እንዲቋረጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 19. የቀድሞ ሰራተኞች በጨረታ ስለሚሳተፉበት አግባብ

1) ጨረታ ከመውጣቱ በፊት በልማት ድርጅቱ ሰራተኛ ወይም ኃላፊ የነበረ ሰው ወይም የቤተሰብ አባሉ በጨረታ ሊሳተፍ የሚችለው የመጫረቻ ሰነድ ባቀረበበት ቀን የልማት ድርጅቱን ከለቀቀ ከአንድ ዓመት በላይ ከሆነው ብቻ ነው፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 1 በተቀመጠው ገደብ በግዥው ዋጋ እና ባህሪ ላይ ሳይወሰኑ የጥቅም ግጭትን ለመከላከል እና በግዥ ሂደት ውስጥ ፍትሃዊ ውድድርን ለማረጋገጥ በልማት ድርጅቱ በሚወጡት ሁሉም ጨረታዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

3) የቀድሞ ሰራተኛ ጨረታዎች ላይ በሚሳተፍበት ወቅት ሊፈጠር የሚችለውን የጥቅም ግጭት በዚህ መመሪያ አባሪ 1 ላይ የተገለጸውን ቅጽ በመሙላት አስቀድሞ መግለፅ አለበት፡፡

4) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና ለአንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 3(ሠ) ዓላማ “የቤተሰብ ግንኙነት” የሚከተሉትን ያጠቃልላል፤

ሀ/ የትዳር ጓደኛ፣

ለ/ ልጆች ፣

ሐ/ ወላጆች እና አሳዳጊ ወላጆች፣

መ/ ወንድሞች እና እህቶች፣ እና

ሠ/ የቀድሞ ሰራተኛው የገንዘብ ፍላጎቶችን ወይም ጉልህ የንግድ ግንኙነቶችን የሚጋራው ማንኛውም ግለሰብ፡፡

## ክፍል አራት

## ዘላቂነት ያለው የግዥ ሥርዓት ተፈጻሚ ስለማድረግ

### 20. የሕይወት ዘመን ወጪ ትንተና

1) በሕይወት ዘመን ወጪ ትንተና መሰረት ተገምግመው የሚፈጸሙ ግዥዎች ዝርዝር የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ልዩ ባህሪ ከግምት በማስገባት በባለስልጣኑ ይወሰናል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ በተገለጸው መሠረት የሚፈፀሙ ግዥዎች ላይ የመገምገሚያ መስፈርት፣ የሰነድ ዝግጅት እና የጨረታ ግምገማ በሚካሄድበት ወቅት የሕይወት ዘመን ወጪ ትንተናን ከግምት ያስገባ መሆን አለበት፡፡

3) ተገቢውን የሕይወት ዘመን ወጪ ትንተና አስቀድሞ መዘጋጀት ያለበት ሲሆን የተዘጋጀው ትንተና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 ተጫራቾች የሚያቀርቡትን የሕይወት ዘመን ወጪ ትንተና ለመመዘን ጥቅም ላይ ማዋል አለበት፡፡

4) የሚዘጋጀው የጨረታ ሠነድ ተጫራቾች ለሚወዳደሩባቸው ዕቃዎች እና የግንባታ ሥራዎች ከመጫረቻ ዋጋው በተጨማሪ የሕይወት ዘመን ጠቅላላ ወጪዎችን ለይተው እንዲያቀርቡ የሚያስገድድ መሆን አለበት፡፡

5) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 አፈፃፀም የአንድ ዕቃ ወይም የግንባታ ሥራ የሕይወት ዘመን የሚወሰነው የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ንብረት አስተዳደር መመሪያ መሠረት ነው፡፡

6) የሕይወት ዘመን ትንተና ተግባራዊ የሚደረገው፣

**የሕይወት ዘመን ወጪ = የመጫረቻ ዋጋ + የሕይወት ዘመን ወጪዎች ድምር (ማለትም የስራ ማስኬጃ ወጪ+ የጥገና እና የመለዋወጫ ወጪ+ የማስወገጃ ወጪ) - የንብረቱ ቀሪ ዋጋ**

7) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 አፈፃፀም፣

ሀ/ ***"የመጫረቻ ዋጋ"*** *ማለት የዕቃዎች እና የግንባታ ሥራዎች የመጀመሪያ ግዥ ዋጋ ነው::*

ለ/ ***"የሕይወት ዘመን ወጪዎች ድምር"*** *ማለት ዕቃው እና የግንባታ ሥራው አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት እስከ ንብረቱ የመጨረሻ ዓመት ያለውን የስራ ማስኬጅ ወጪ፣የጥገና እና መለዋወጫ ወጪ፣የማስወገጃ ወጪን ያካትታል::*

ሐ/ ***"የሥራ ማስኬጃ ወጪ"*** *ማለት ለዕቃው ወይም ለሥራው የሕይወት ዘመን አስፈላጊ የሆኑ የጥገና፣የኃይል ፍጆታ እና ሌሎች ንብረቱን ከመጠቀም ጋር የተያያዙ ወጪዎችን ያካትታል::*

መ/ ***"የጥገና/ መለዋወጫ"*** *ማለት በየወቅቱ የሚከሰቱትን ዋና ዋና ወጪዎች ሲሆን እንደ ምትክ ወይም ጥገናን ያካትታል::*

ሠ/ ***"የማስወገጃ ወጪ"*** *ማለት በንብረቱ የሕይወት ዘመን መጨረሻ ላይ ለማስወገድ የሚወጣ ወጪ ሲሆን የንብረቱ ቀሪ ዋጋ ተቀናሽ መደረግ አለበት::*

ረ/ ***"ቀሪ ዋጋ"*** *ማለት ንብረቱ የሕይወት ዘመኑ ሲያልቅ ሊሸጥ የሚችለው የተገመተው ዋጋ ነው::*

8) ተወዳዳሪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ 6 መሠረት የሕይወት ዘመን የሥራ ማስኬጃ፣ የጥገና፣ የመለዋወጫ እና የማስወገጃ ወጪዎች የሚያቀርበው የልማት ድርጅቱ የሚገዛው ዕቃ ወይም የግንባታ ሥራ በሕይወት ዘመኑ የሚያስወጣውን ወጪ ለግምገማ ዓላማ ብቻ ሲሆን ተወዳዳሪው እነዚህን ወጪዎች በማቅረቡ ብቻ የድህረ ሽያጭ የሥራ ማስኬጃ፣ ጥገና እና የማስወገድ ሥራን ለማከናወን እንደተወዳደረ ተደርጎ አይቆጠርም::

9) የሚቀርበው የሕይወት ዘመን ወጪ ተዓማኒነት ያለው እና በአምራች ወይም በሌሎች በሚመለከታቸው ተቋማት የተረጋገጠ መሆን አለበት::

10) በተወዳዳሪዎች የሚቀርቡ የሕይወት ዘመን ትንተና ወጪዎችን የሚያሳዩ ሰነዶች ስለ ትክክለኝነታቸው በልማት ድርጅቱ ሊጠየቅ ይችላል፡፡

## 21. የአካባቢ ጥበቃን ታሳቢ ያደረገ ግዥ

1) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የሚፈጽሟቸው ግዥዎች ከአካባቢ ብክለት የጸዳ፣ መልሶ መጠቀምን እና የማህበረሰብ ተጠቃሚነትን ታሳቢ ያደረገ ሊሆን ይገባል፡፡
2) ከአካባቢ ጋር ተስማሚ የሆኑ ቴክሎጂዎችን፣ የታዳሽ ኃይል ምንጮችን በመጠቀም ወይም የተመረቱ ምርቶችን ሊያበረታቱ የሚችሉ መስፈርቶችን በሚያዘጋጁት የጨረታ ሰነዶች ውስጥ በማካተት ነው፡፡

## 22. የማህበረሰብ ተጠቃሚነትን ታሳቢ ያደረገ ግዥ

የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የሚፈጽሟቸው ግዥዎች ለአካባቢው ማህበረሰብ ያላቸውን አዎንታዊ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና አካባቢያዊ ተጽዕኖዎችን ታሳቢ ያደረገ መሆን አለበት፡፡

# ክፍል አምስት

# የግዥ ስነ ምግባር

## 23. ጠቅላላ ድንጋጌ

በልማት ድርጅቱ የግዥ ሂደት የሚሳተፉ ሰራተኞች፣የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ፣የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ፣ የግዥ ገምጋሚ ኮሚቴ እና ተጫራቾች በአዋጁ እና በዚህ አፈጻጸም መመሪያ የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት በሚወጡበት ወቅት በዚህ ክፍል የተደነገጉትን የሥነ ምግባር ድንጋጌዎች ማክበር አለባቸው፡፡

## 24. ሚስጥርን መጠበቅ

1) በግዥ ሂደት ላይ የሚሳተፉ ማናቸውም የልማት ድርጅቱ ሰራተኞች እና ሌሎች አካላት በሥራቸው የሚያገኙትን መረጃ ሚስጥርና ደህንነት የመጠበቅ ህጋዊ እና ሙያዊ ግዴታ አለባቸው፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ሚስጢራዊነታቸው እንዲጠበቅ የተደረጉት መረጃዎች ጥቅም ላይ በሚውሉበት ወቅት የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ተገቢውን የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት አለበት፡፡

3) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 አፈፃፀም የልማት ድርጅቱ ሰራተኛ ወይም ኃላፊ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማከናወን አለበት፡፡

ሀ) ውድድርን ሊገድብ የሚችል ወይም ለተወዳዳሪዎች ፍትሐዊ ያልሆነ ጥቅም የሚያሰጥ ወይም የልማት ድርጅቱን ጥቅም ሊጎዳ የሚችል መረጃ ለማንኛውም አካል አለመስጠት፤

ለ) የልማት ድርጅቱ በውል አፈፃፀም ወቅት ከአቅራቢዎች ጋር በሚያደርገው ግንኙነት የየልማት ድርጅቱን ውሳኔ እና መረጃ መጠበቅ፤

ሐ) በተለየ ሁኔታ በሕግ የተፈቀደለት አካል ካልተጠየቀ በስተቀር፣ ተወዳዳሪዎችን መረጃ እና የግምገማ ሂደት እና ሌሎች በሚስጢር መያዝ ያለባቸውን መረጃዎች ውጤቱ ከመገለጹ በፊት ለማንኛውም አካል አለማሳወቅ፡፡

## 25. የጥቅም ግጭትን በተመለከተ

1) በግዥ ሂደት ላይ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የተሰማሩ ሰራተኞች ወይም ኃላፊ ከሚሰራው ሥራ ጋር በተገናኘ የሚሰጠው ውሳኔ ከስራው ጋር የተገናኘ የጥቅም ግጭት መኖሩን በዚህ መመሪያ አባሪ 2 መሠረት በጽሁፍ በማሳወቅ ከግዥ ሂደቱ ራሳቸውን ማግለል አለባቸው፡፡

2) በልማት ድርጅቱ ግዥ ሥራ ላይ የተሳተፈ ሰራተኛ ወይም ኃላፊ ወይም ከግዥ ጋር ግንኙነት ያለው የኮሚቴ አባል ከሚሰራው ሥራ ጋር በተያያዘ የጥቅም ግጭት እንዳለው የልማት ድርጅቱ ከማንኛውም አካል መረጃ ሲደርሰው፤

ሀ/ ሠራተኛው ወይም ኃላፊው በቀረበው የጥቅም ግጭት ጉዳይ ላይ አስተያየቱን በጽሁፍ እንዲሰጥ ያደርጋል፤

ለ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 (ሀ) በተሰጠው የጽሁፍ አስተያየት እና ተገቢ ነው ብሎ ባመነባቸው መንገዶች ተጨማሪ መረጃ በማሰባሰብ ሰራተኛው ወይም

ኃላፊው ከያዘው የግዥ ሥራ ጋር በተያያዘ የጥቅም ግጭት እንዳለው ወይም እንደሌለው ይወስናል፤ እና

ሐ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 (ለ) በተቀመጠው መሠረት የልማት ድርጅቱ ሠራተኛው ወይም ኃላፊው ከሚሰራው የግዥ ሥራ ጋር በተያያዘ የጥቅም ግጭት መኖሩን ሲያረጋግጥ ሠራተኛውን ወይም ኃላፊውን ከሂደቱ እንዲገለል፣ በሂደቱ ተሳትፎባቸው ውሳኔ የተሰጠባቸው ጉዳዮች ከእንደገና እንዲታዩ ያደርጋል፣ እንዲሁም የጥቅም ግጭቱን ያላሳወቀው ከግንዛቤ ጉድለት ነው ብሎ ካላመነ በስተቀር በሰራተኛው ወይም በልማት ድርጅቱ ኃላፊ ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡

3) በልማት ድርጅቱ ግዥ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ተሳትፎ ያላቸው ሠራተኞች እና ኃላፊዎች በግዥ ሥራቸው ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር ወይም ሊያሳድር የሚችል ማናቸውም ዓይነት ስጦታን ከሶስተኛ ወገን መቀበል የለባቸውም፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የልማት ድርጅቱ ሠራተኞች ወይም ኃላፊዎች የሚከተሉትን እና ሌሎች ተያያዥ የጥንቃቄ እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው፡፡

ሀ/ የገንዘብ ዋጋ ያለውን ሥጦታ በተለይ ለልማት ድርጅቱ ተጫራች ከሆነ አካል አለመቀበል፣

ለ/ የሥራ ዕድል ለራሱ ወይም ለቤተሰቡ አለመቀበል፣

ሐ/ በግል በሚደረግ ግዥ ላይ ለልማት ድርጅቱ አቅራቢ/ ተጫራች ከሆነ አካል የተለየ የዋጋ ቅናሽ ወይም አገልግሎት አለመቀበል፣

መ/ በሥራው ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል የግብዣ ፕሮግራም አለመቀበል፡፡

## 26. ፍትሐዊነት

1) በግዥ ሂደት የሚሳተፉ ማናቸውም የልማት ድርጅቱ ሰራተኞች እና ሌሎች አካላት ከማንኛውም ተጽዕኖ ነፃ ሆነው ተወዳዳሪዎችን በእኩልነት ማገልገል አለባቸው፡፡

2) በልማት ድርጅቱ ግዥ ሥራ ላይ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የሚሳተፍ ማንኛውም የመንግሥት የልማት ድርጅትሰራተኛ ወይም ኃላፊ ተወዳዳሪዎች ወይም አቅራቢዎች እኩል የመወዳደርና ውል የመፈፀም ዕድል እንዳይኖራቸው የሚያደርግ ማንኛውንም ተግባር መፈፀም የለበትም፡፡

## 27. ግልጽነት

1) በልማት ድርጅቱ የሚፈጸሙ ሁሉም የግዥ ሂደቶች ፍትሃዊነትንና ግልጽነት በተከተለ መንገድ መከናወን አለባቸው፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን በተመለከተ አስፈላጊ መረጃዎችን ማሳወቅ፣ ግልጽ ውድድር እንዲኖር ማድረግ እና ማንኛውንም አድሎአዊ አሰራርን ማስወገድን ይጨምራል፡፡

# ምዕራፍ አራት
# የግዥ ዘዴዎች እና አፈጻጸማቸው

## 28. የግዥ ዘዴዎች

የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ለየግዥ ዘዴዎች የተቀመጡት ቅድመ ሁኔታዎች -መሟላታቸው በማረጋገጥ የሚከተሉትን የግዥ ዘዴዎች ተጠቅመው ግዥ መፈጸም ይችላሉ፡፡

1) ግልጽ ጨረታ፣
2) በማጣሪያ የሚከናወን ጨረታ፣
   ሀ/ የሁለት ደረጃ ጨረታ ግዥ፣
   ለ/ የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ፣
   ሐ/ የፍላጎት መጠየቂያ ጨረታ፡፡
3) ውስን ጨረታ፣እና
   ሀ/ የተገደበ ጨረታ፣
   ለ/ በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈፀም ግዥ
4) በቀጥታ የሚፈጸም ግዥ፡፡

# ክፍል አንድ
# ብሔራዊ ግልጽ ጨረታ

## 29. ብሔራዊ ግልጽ ጨረታ አፈጻጸም

የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በግልፅ ጨረታ ግዥ ዘዴ ግዥ መፈጸም የሚችሉት ከሚከተሉት ቢያንስ አንዱ ሲሟላ ነው፡፡

1) የሚፈለገው ግዥ በሀገር ውስጥ ተጫራቾች ሊያሟላ የሚችል እና ከሚከተለው የገንዘብ መጠን ያልበለጠ ሲሆን፣

ሀ/ ለግንባታ ዘርፍ ሥራ…………........…ብር 3,000,000,000.00 (ሦስት ቢልየን ብር)

ለ/ ለዕቃ ግዥ……………………….....ብር 1,000, 000,000.00 (አንድ ቢልየን ብር)

ሐ/ ለምክር አገልግሎት ግዥ………… ብር 90, 000,000.00 (ዘጠና ሚሊዮን ብር)

መ/ አገልግሎት ግዥ….................……… ብር 250, 000,000.00 (ሁለት መቶ ሃምሳ ሚሊዮን ብር)

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ቢኖርም የግንባታ ዕቃዎችን የማቅረብ ኃላፊነት የግዥ ፈጻሚው የመንግሥት የልማት ድርጅትከሆነ ለግንባታ ዕቃዎች ግዥ ተግባራዊ የሚሆነው ለግንባታ ስራ ግዥ የተፈቀደው የገንዘብ ጣሪያ ይሆናል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የተቀመጠውን የገንዘብ ጣሪያ የወቅቱን ነባራዊ ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ የገንዘብ ሚኒስቴር ሊያሻሽል ይችላል፡፡

4) የግዥው መጠን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ቢኖርም የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በሚከተሉት አንዱ ምክንያት ያለ ገንዘብ ጣሪያ በብሔራዊ ግልጽ ጨረታ መፈጸም ይችላሉ፡፡

ሀ/ ዕቃው ወይም አገልግሎቱ ወይም የግንባታ ሥራው በሀገር ውስጥ ብቻ የሚገኝ መሆኑ ሲረጋገጥ፣ ወይም

ለ/ ግዥው በብሔራዊ ግልፅ ጨረታ ቢፈፀም በተሻለ ጥራትና ፍጥነት እንዲሁም በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርብ መሆኑ በዝርዝር ተገምግሞ በልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ሲፈቀድ፣

ሐ/ ግዥውን ለመፈጸም ዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ ቢያንስ ለአንድ ጊዜ ወጥቶ ጨረታው ካልተሳካ፣ ወይም

መ/ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ውል በመፈፀም ለሦስተኛ ወገን ለሚሰሩት የግንባታ ሥራ ለሚያስፈልጉ የግንባታ ግብዓቶችን፣፡

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው የገንዘብ ጣሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 50 መሰረት በስትራቴጂክ የግዥ ስልት የቅድመ ብቃት ግምገማ ተወዳድረው በልማት ድርጅቶች የአቅራቢ ዝርዝር ውስጥ የተመዘገቡ ድርጅቶችን የቁጥር ገደብ ሳይደረግ በጽሁፍ ወይም ኤሌክትሮኒክ ዘዴ በመጠቀም በመጋበዝ ግዥ መፈጸም ይችላሉ፡፡

## 30. ዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ አፈጻጸም

የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታን በመጠቀም ግዥ መፈጸም የሚችሉት ከሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች ውስጥ ቢያንስ አንዱ ሲሟላ ነው፡፡

1) የግዥው ግምታዊ ዋጋ ከሚከተለው የገንዘብ መጠን በላይ ሲሆን፣

ሀ/ ለግንባታ ዘርፍ ሥራ………….......…ብር 3,000,000,000.00 00 (ሦስት ቢልየን ብር)

ለ/ ለዕቃ ግዥ…………………………....ብር 1,000, 000,000.00 (አንድ ቢሊዮን)

ሐ/ ለምክር አገልግሎት ግዥ………… ብር 90, 000,000.00 (ዘጠና ሚሊዮን)

መ/ አገልግሎት ግዥ…...................……… ብር 250, 000,000.00 (ሁለት መቶ ሃምሳ ሚሊዮን)

2) የግዥው ግምታዊ የገንዘብ መጠን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተቀመጠው የገንዘብ ገደብ በታች ቢሆንም የውጭ ሀገር ተጫራቾች ካልተሳተፉ ግዥው ውጤታማ እንደማይሆን ሲረጋገጥ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በአለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ ግዥ ሊፈጽም ይችላል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የተቀመጠውን የገንዘብ ጣሪያ የወቅቱን ነባራዊ ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ የገንዘብ ሚኒስቴር ሊያሻሽል ይችላል፡፡

4) በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ በሚፈጸም የዕቃ ግዥ ተሳታፊ የሚሆኑ ተጫራቾች ራሳቸው የዕቃው አምራቾች ካልሆኑ የሚቀርበው ዕቃ ከአምራቹ የሚመጣ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ ሊጠየቁ ይችላሉ፡፡

5) በዓለም አቀፍ ጨረታ ሂደት የውጭ ሀገር ተጫራች የሀገር ውስጥ ወኪል ያለው ከሆነ ውክልና የተሰጠው መሆኑን የሚያሳይ ሕጋዊ የውክልና ማስረጃ እንዲያቀርቡ ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡

6) በዓለም አቀፍ ግዥ ተፈጻሚ የሚሆኑት የንግድ ቃላትና ሁኔታዎች በልማት ድርጅቱ ይወሰናል፡፡

7) በዚህ መመሪያ ለብሔራዊ ግልጽ ጨረታ ከተገለፀው ዝርዝር የጨረታ ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም በተጨማሪ በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ የሚፈፀም ግዥ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡፡

ሀ/ የጨረታ ጥሪ ማስታወቂያ እና የጨረታ ሠነዱ የሚዘጋጀው በእንግሊዝኛ ቋንቋ መሆን አለበት፤

ለ/ የጨረታ ጥሪው በቂ የሥርጭት ሽፋን ያለውና የውጭ ተጫራቾችን ለውድድር ሊጋብዝ በሚችል ጋዜጣ ወይም በሌሎች የኤሌክትሮኒክ ዘዴዎች በመጠቀም ይፋ ማድረግ አለበት፤

ሐ/ ተጫራቾች ተገቢ የመጫረቻ ሰነድ ማዘጋጀት እንዲችሉ በዚህ መመሪያ የተሰጠው የጨረታ መቆያ ጊዜ መሠረት በቂ ጊዜ መሰጠት አለበት፤

መ/ የሚዘጋጀው የፍላጎት መግለጫ የሀገር ውስጥ ደረጃ የሚያሟላና እስከተቻለ ድረስ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው መሆን አለበት፤

ሠ/ የውጭ ሀገር ተጫራቾች የሚያቀርቡት የመጫረቻ ዋጋ እና የጨረታ ማስከበሪያ በቀላሉ ሊመነዘር በሚችልና በአለም አቀፍ ንግድ በሚሠራበት የገንዘብ ዓይነት ወይም በኢትዮጵያ ብር ሊሆን ይቻላል፡፡

ረ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 (ሠ) የተገለፀው እና የተመረጠው የንግድ ቃል እንደተጠበቀ ሆኖ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር ተጫራቾች በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ ሲወዳደሩ ዕቃው ከሚያርፍበት ወደብ አንስቶ እስከ ግዥ ፈፃሚ የልማት ድርጅቱ ለማድረስ የሚከፈሉ የታክስ እና ቀረጥ፣ ኢንሹራንስ እና የማጓጓዣ ወጭዎችን እና ሌሎች ተያያዥ ክፍያዎችን እና ወጪዎችን እንደ አስፈላጊነቱ በማካተት ውድድሩ ይደረጋል፡፡

ሰ/ የግዥ ፍላጎቱን ለማሟላት የውጭ ሀገር ተጫራቾች ከሀገር ውስጥ የሚጠቀሙት ግብዓት በሚኖርበት ጊዜ ከአጠቃላይ የውሉ ክፍያ በብር

ሊከፈል የሚገባው መጠን በዋጋ ማቅረቢያው ሠንጠረዥ ላይ ማመልከት ይኖርበታል፡፡

ሸ/ በውሉ በተለየ ሁኔታ ካልተመለከተ በስተቀር በውል አፈፃፀም ወቅት የሚነሱ አለመግባባቶች በኢትዮጵያ ሕግ ሊዳኙ ይገባል፡፡

### 31. ዓለም አቀፍ ግዥዎች

የውጭ ሀገር ተጫራቾች ካልተሳተፉበት በስተቀር በቂና ውጤታማ ውድድር ሊኖር እንደማቻል ሲረጋገጥ እና በልማት ድርጅቱ በላይ ኃላፊ ሲፈቀድ በዚህ መመሪያ በዓለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ የተገለጹት ሌሎች አሠራሮች እንደተጠበቁ ሆነው በተገደበ ጨረታ፣ በዋጋ ማቅረቢያ እና በቀጥታ የሚፈጸም የግዥ ዘዴዎችን በመጠቀም ዓለም አቀፍ ግዥ መፈጸም ይቻላል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ

### 32. የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ አፈጻጸም

1) የልማት ድርጅቱ ግዥው ከሚኖረው የተለየ ባህሪ አንፃር በቅድሚያ የተወዳዳሪዎችን ብቃት መሠረት ያደረገ ግምገማ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እንደግዥው ዓይነት ብሔራዊ ወይም ዓለም አቀፍ የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ ሊያወጣ ይችላል፡፡

2) የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ የሚያስፈልጋቸው ግዥዎች ከሚከተሉት ሁኔታዎች ቢያንስ አንዱን የሚያሟሉ መሆን አለባቸው፡፡

ሀ/ በጣም ከፍተኛ ዋጋ ያለው ወይም በባህሪው ውስብስብ የሆነ የዲዛይን፣ የማምረትና የተከላ ሥራ በአንድ ድርጅት መጠናቀቅ ያለበት የግንባታ፣ የማምረቻ መሳሪያ ወይም የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ግዥ ሲሆን፣ ወይም

ለ/ የሚቀርበው ዕቃ ወይም መሳሪያ ጥራትና ጠቀሜታ ከፍተኛ ተፈላጊነት ያለው እና የተከላ አገልግሎትን ያካተተ ሲሆን፣ ወይም

ሐ/ የመጫረቻ ሰነድ ለማዘጋጀት ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ ግዥ በመሆኑ ብቃታቸው በቅድመ ብቃት ምዘና የሚረጋገጡ ተጫራቾች ብቻ በውድድሩ ተካፋይ መሆን እንደሚገባቸው ሲታመንበት፣

3) ጨረታው የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ ጥሪ መሆኑ በማስታወቂያው ላይ መገለጽ አለበት፡፡

4) የቅድመ ብቃት ግምገማ ለማድረግ የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ለቅድመ ብቃት ጨረታ የተዘጋጀውን የቅደመ ብቃት ጨረታ መደበኛ የጨረታ ሰነድ መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡

5) የቅድመ ብቃት መምረጫ መስፈርት እንደግዥው ባህሪና ዓይነት ሊለያይ የሚችል ቢሆንም ተወዳዳሪ ድርጅቶች እንዲያቀርቡ የሚጠየቁት ማስረጃ ቢያንስ የሚከተሉትን መስፈርቶች ወይም መረጃዎች ማካተት ይኖርባቸዋል፡፡

   ሀ/ በተመሳሳይ የግንባታ ሥራ ወይም ዕቃ ማምረት ላይ ድርጅቱ ያለው ልምድ፣

   ለ/ ድርጅቱ የግንባታ ሥራውን ለማከናወን ወይም ዕቃውን ለማምረት የሚያስችል በቂ የሰው ኃይል፣ ማሽኖች፣ የማምረቻ ብዛት እና የተሟላ መሰረተ ልማት ያለው መሆኑን፣

   ሐ/ ድርጅቱ አሁን በመስራት ላይ ያለው የግንባታ ሥራ ወይም በማምረት ላይ ያለው ዕቃ ብዛት ወይም መጠን፣

   መ/ ድርጅቱ የውል ግዴታውን ለማጠናቀቅ የሚያስችል በቂ የገንዘብ አቅም እና መልካም ዝና ያለው መሆኑን በሚቀርብ ሰነድ የተረጋገጠ፣

6) የተጫራቾች ግምገማ የሚከናወነው ለቅድመ ብቃት ማረጋገጫ በልማት ድርጅቱ የተዘጋጀውን መስፈርት መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡

7) ለቅድመ ብቃት ውድድሩ ያመለከቱ ተጫራቾች በሙሉ የግምገማ መስፈርቱን እስካሟሉ ድረስ ምንም ዓይነት የቁጥር ገደብ ሳይደረግ በሚቀጥለው ውድድር እንዲሳተፉ መደረግ አለበት፡፡

8) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በቅድመ ብቃት ውድድር የሚሳተፉ ድርጅቶች በሽርክና ወይም በጋራ መወዳደር እንዲችሉ ሊፈቅዱ ይችላሉ፡፡ ሆኖም የቅድመ ብቃት ውድድሩን በግል ያለፉ ተወዳዳሪዎች በግዥው ሂደት የሚኖራቸውን ውድድር እንደማያጠብ በልማት ድርጅቱ ካልታመነ በስተቀር በጋራ ወይም በሽርክና የመጫረቻ ሰነዱን እንዲያቀርቡ መፈቀድ የለበትም፡፡

9) በጋራ ወይም በሽርክና ለቅድመ ብቃቱ ውድድር ቀርበው ይህንኑ መሠረት በማድረግ በተካሄደ ግምገማ ለሚቀጥለው ጨረታ ያለፉና የተመረጡ ተጫራቾች በጨረታው በግል እንዲወዳደሩ አይፈቀድላቸውም፡፡

10) የቅድመ ብቃቱ ግምገማ ውጤት እንደታወቀና በልማት ድርጅቱ ተቀባይነት እንዳገኘ ውጤቱ በጨረታው እንዲሳተፉ ለተመረጡትና ላልተመረጡት ተጫራቾች ሊገለጽላቸው ይገባል፡፡

11) አንድ ተጫራች የቅድመ ብቃት ጨረታን ተከትሎ በወጣ ጨረታ ላይ በተደረገ ግምገማ አሸናፊ ለመሆን ቢችልም በቅድመ ብቃት ውድድር ወቅት የሰጠው መረጃ የተሳሳተ ከሆነ ወይም በቅድመ ብቃት ውድድሩ ወቅት የነበረው ብቃት ባለመኖሩ ውሉን በሚጠበቅበት ሁኔታ ለመፈጸም አለመቻሉ በድህረ ግምገማ በበቂ ሁኔታ ከተረጋገጠ የልማት ድርጅቱ ተጫራቹ ውሉን እንዲፈርም ላይፈቅድ ይችላል፡፡

12) የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ በቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ውድድር ተቀባይነት ላገኙት ተጫራቾች በየአድራሻቸው እንዲላክላቸው የሚደረግ ሲሆን፣ ቀሪው የግዥ አፈፃፀም በዚህ መመሪያ ለብሔራዊ ግልጽ ጨረታ የተቀመጠውን ሥርዓት ተከትሎ ይፈጸማል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የሁለት ደረጃ ጨረታ

### 33. የሁለት ደረጃ ጨረታ ግዥ አፈጻጸም

1) በሁለት ደረጃ የሚፈፀም ግዥ በዚህ መመሪያ እንደግዥው ዓይነት ለብሔራዊ ወይም ለዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ የተዘረጋውን ሥርዓት ተከትሎ ይከናወናል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በመጀመሪያ ዙር የሚደረገው የጨረታ አፈጻጸም የሚከተሉትን ሁኔታዎች መሠረት በማድረግ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ሀ/ የጨረታ ጥሪ ማስታወቂያ ላይ ግዥው በሁለት ደረጃ ጨረታ የሚፈፀም መሆኑ መገለፅ ይኖርበታል፡፡

ለ/ በመጀመሪያው ዙር ጨረታ የሚሳተፉ ተወዳዳሪዎች የጨረታ ዋስትና እና ዋጋ እንዲያቀርቡ አይጠየቁም፡፡

ሐ/ ለግዥው የሚዘጋጀው ሰነድ የልማት ድርጅቱ አጠቃላይ ፍላጎት የሚገልፅ ሆኖ አላማው ከ ተወዳዳሪዎች በሚቀርቡ ሐሳቦች መሠረት ዝርዝር የፍላጎት መግለጫ ማዘጋጀት የሚያስችሉ አስፈላጊ መጠይቆችን እና መግለጫዎችን እንዲሁም ወደ ሁለተኛው ዙር ጨረታ የሚያልፉ ተጫራቾችን ለመለየት የሚያስችሉ መስፈርቶችን በማካተት መውጣት ይኖርበታል፡፡

መ/ በ ተወዳዳሪዎች የቀረበው የቴክኒክ ሀሳብ ማቅረቢያ ሰነድ በጨረታ ጥሪው በተገለፀው ቀንና ሰዓት እንዲከፈት ይደረጋል፡፡

ሠ/ ከ ተወዳዳሪዎች የቀረበውን ሀሳብ በመመርመር ለሁለተኛው ዙር ጨረታ የሚያገለግለውን የፍላጎት መግለጫ እና በጨረታው ሊሳተፉ የሚገባቸውን ተጫራቾች መለየት የሚያስችል መሆን ይኖርበታል፡፡

ረ/ የልማት ድርጅቱ በግምገማው ወቅት እንደአስፈላጊነቱ ከሁሉም ወይም ከተወሰኑ ወይም ከአንድ ከተለየ ተወዳዳሪ ጋር ውይይት ሊያደርግ ይችላል፡፡

ሰ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ 2 (ረ) በተገለፀው መሠረት የሚደረገው ውይይት ተወዳዳሪዎች የሰጡትን ሐሳብ ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ እና በተሻለ የዳበረ ሐሳብ ለማመንጨት ያለመ ሊሆን ይገባል፡፡

3) በሁለተኛው ዙር የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ በመጠቀም በውድድሩ ለተጋበዙ በአድራሻቸው ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አሰራሮች ተከትሎ ይከናወናል፡፡

ሀ/ በመጀመሪያው ዙር ተቀባይነት ያገኙ ተጫራቾች በሁለተኛው ዙር ውድድር በሚሳተፉበት ወቅት የጨረታ ዋስትና እና ዋጋን ጨምሮ የመወዳደሪያ ኃሳብ እንዲያቀርቡ ይደረጋል፡፡

ለ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 (ሀ) በተገለፀው መሠረት ለተመረጡ ተወዳዳሪዎች የሚተላለፈው ግብዣ የጨረታ ማቅረቢያ ጊዜ እና የጨረታ መክፈቻ ጊዜ ጨምሮ ሌሎች ሊያሟሉ የሚገባቸውን ሁኔታዎች በግልፅ ሊያመለክት ይገባል፡፡

# ክፍል አራት

# የፍላጎት መግለጫ መጠየቂያ ጨረታ

## 34. የፍላጎት መግለጫ መጠየቂያ ጨረታ አፈጻጸም

1) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የሚፈጸመው የምክር አገልግሎት ግዥ ግምታዊ ዋጋ ከብር 25,000,000.00 (ሃያ አምስት ሚሊዮን) የሚበልጥ ሲሆን በምክር አገልግሎቱ ግዥ ላይ ፍላጎት ያላቸው ተወዳዳሪዎች የፍላጎት መጠየቂያ ጥሪ ሊያደርግ ይችላል፡፡

2) ተጫራቾች ፍላጎታቸውን ሊያቀርቡ የሚያስችላቸውን መረጃ እንዲያገኙ የምክር አገልግሎት ስራውን ዳራ፣ ዓላማ፣ ግብ እና የማማከር አገልግሎቱ ወሰን እና ሌሎች ለአገልግሎቱ አስፈላጊ የሆኑትን መግለጫዎች የሚዘረዝር ቢጋር መዘጋጀት አለበት፡፡

3) ለፍላጎት መግለጫው የሚደረገው ጥሪ የሚከተሉትን ታሳቢ ያደረገ በመሆን አለበት፡፡

   ሀ/ የፍላጎት መግለጫ ጥሪው የሚፈለገውን የምክር አገልግሎት ዓይነት፣ የሚጠበቀውን ውጤት፣ ጊዜውን፣ አማካሪው ሊኖረው የሚገባውን ብቃት፣ የስራ ልምድ እና የመሳሰሉትን የያዘ እና ተወዳዳሪዎች ሊያቀርቡት የሚገባውን መረጃ ዝርዝር እንዲሁም የሚያቀርቡበትን ቦታና ጊዜ የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡

   ለ/ በፍላጎት መግለጫ መጠየቂያው ላይ በተቀመጠው መገምገሚያ መስፈርት መሠረት ፍላጎታቸውን ከገለፁ አማካሪዎች ውስጥ የተሻለ ብቃት ያላቸውን በመምረጥና በጨረታ ሰነዱ የተዘረዘሩትን ቅድመ ሁኔታዎችና ተፈላጊ ነጥቦች መሠረት ፍላጎታቸውን ላቀረቡ ተጫራቾች ማሳወቅ፣

   ሐ/ ፍላጎታቸውን ያሳወቁ ተወዳዳሪዎች ያቀረቡት መረጃ ተገምግሞ የተፈለገውን የምክር አገልግሎት ለመስጠት ከፍተኛ ብቃት ያላቸው በቅደም ተከተላቸው መሠረት እስከተቻለ ድረስ ከሶስት ያላነሱ እና ከሰባት ያልበለጡ

ተወዳዳሪዎች ተመርጠው በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ጨረታ አፈጻጸም መሠረት የመወዳደሪያ ሀሳባቸውን እንዲያቀርቡ መደረግ አለበት፡፡

መ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3(ሐ) የተጠቀሰው ቢኖርም የፍላጎት መጠየቂያ መግለጫውን የሚያሟሉ አማካሪዎች ከ3 የሚያንሱ ከሆነ በልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ፍቃድ የመወዳደሪያ ሀሳብ እንዲቀርብ ሊያደርግ ይችላል፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 (ሐ) መሠረት በአማካሪዎች ብቃት ላይ ተመስርቶ የሚደረግ መረጣ ግዥ እስከተቻለ ድረስ ለልማት ድርጅቱ ተፈላጊውን ጥራት እና ኢኮኖሚያዊ ጠቃሚታ በሚያስገኝና ውድድርን በሚያበረታታ መልኩ የፍላጎት መግለጫ መጠየቂያን ጨረታ አፈጻጸምን ተከትሎ መፈጸም አለበት፡፡

5) የልማት ድርጅቱ የመወዳደሪያ ኃሳብ እንዲያቀርቡ ለተመረጡ አማካሪዎች በተመሳሳይ ጊዜ ጥሪ በአድራሻቸው መላክ አለበት፡፡ ለግዥው የተዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ተወዳዳሪዎች ያለ ክፍያ ሊሰጥ እንደሚገባ የልማት ድርጅቱ ሲያምን ከጥሪው ጋር መላክ ይችላል፡፡

6) ልማት ድርጅቱ ከተመረጠው አማካሪ ጋር የሚያደርገው ድርድር መሠረታዊውን የጨረታ ይዘትና የሥራ ጥራት የማይቀይር ሆኖ ስለስራው ይዘት፣ ስለአሰራር ዘዴው፣ በስራው ስለሚሰራው የሰው ኃይል እና መሳሪያ፣ ስለ ሪፖርት አቀራረብ እና ይዘት እና እንደአስፈላጊነቱ ዋጋ እና በመሳሰሉት ላይ ያተኮረ ሊሆን ይገባል፡፡

7) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት የሚደረገው ድርድር የልማት ድርጅቱን ጥቅም የሚጎዳ ወይም ለተመረጠው አማካሪ ከሌሎች ተጫራቾች አንፃር ፍትሐዊ ያልሆነ ጥቅም የሚያሳጣው መሆን የለበትም፡፡

8) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 9 በተገለጹት የመምረጫ ዘዴዎች ለሚፈፀሙ ግዥዎች የሚቀርበው የመጫረቻ ሰነድ በቴክኒክ እና በዋጋ ማቅረቢያ ተለያይቶ መቅረብ ያለበት ሲሆን ለምክር አገልግሎቱ የሚዘጋጀው የመምረጫ መስፈርት፣ የሚደረገው ግምገማ ሌሎች የጨረታ አፈጻጸም ሂደቶች በዚህ መመሪያ የተገለጹትን የግልፅ ጨረታ አሠራሮች በመከተል የሚፈጸሙ ይሆናል፡፡

9) የምክር አገልግሎት ግዥ ለመምረጥ እንደ አግባብነቱ በጥራት እና በዋጋ ላይ፣ በሚከናወን የሥራ ጥራት ላይ፣ በቁርጥ በጀት ላይ፣ በዝቅተኛ ዋጋ ላይ፣

በአማካሪዎች ብቃት ላይ የተመሠረተ መረጣ እና አንድ አማካሪ የሚመረጥበት አሠራር ተከትሎ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡

## 35. በጥራት እና በዋጋ ላይ የተመሰረተ መረጣ

1) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በጥራት እና በዋጋ ላይ የተመሰረተ የመረጣ ዘዴ ጥቅም ላይ የሚያውሉት የጨረታ ሰነድ በሚያዘጋጁበት ወቅት የሚከተሉትን መስፈርቶች ከግምት በማስገባት እና በ ተወዳዳሪዎች የሚቀርበውን እያንዳንዱን የቴክኒክ ሐሳብ በሚገመግሙበት እና በሚያወዳድሩበት ወቅት የሚከተሉትን ነጥቦች ከ100 (መቶ) የያዘ መሆን አለበት፡፡

ሀ/ የአማካሪው ልዩ ልምድ..................................................ከ5 እስከ 10 ነጥብ

ለ/ በሥራ ላይ እንዲውል የቀረበውን ምክር ዘዴ ደረጃ..........ከ20 እስከ 50 ነጥብ

ሐ/ በምክር አገልግሎቱ ለሚሳተፉ ቁልፍ ባለሙያዎች................ከ30 እስከ 60 ነጥብ

መ/ የምክር አገልግሎቱ ለልማት ድርጅቱ የሚያስገኘው ዕውቀት...ከ5 እስከ 10 ነጥብ

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (መ) የተቀመጠው መስፈርት እና ነጥብ ከግንባታ ሥራዎች ጋር ለተያያዙ የምክር አገልግሎቶች ተፈፃሚ አይሆንም፡፡ ሆኖም የልማት ድርጅቱ በዚህ መልኩ የሚሰጡ የምክር አገልግሎቶች ለልማት ድርጅቱ የሚያስገኘው ዕውቀት እንደ መስፈርት መታየት አለበት ብሎ ሲያምን መስፈርቱ እና መመዘኛ ነጥብን ጥቅም ላይ ማዋል ይቻላል፡፡

3) በጥራት እና ዋጋ ላይ በተመሰረተ መረጣ በመጠቀም የቀረቡትን አማካሪዎች ለመምረጥ የሚከተለውን የመገምገሚያ ሂደት መከተል አለባቸው፡፡

ሀ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በቴክኒክ ብቃት ምዘና ከመቶ ከተያዘው ውጤት 70% (ሰባ ከመቶ) በታች ያገኙ ተወዳዳሪዎች ውድቅ ተደርገው 70% እና ከዚያ በላይ የሚያገኙት ተወዳዳሪዎች የዋጋ ማቅረቢያ ይከፈታል፡፡

ለ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ) መሰረት በቴክኒክ ግምገማ ሰባ ከመቶ (70%) እና ከዚያ በላይ ያመጡ ተወዳዳሪዎች ውጤት ወደ 80% /ከሰማኒያ ከመቶ/ ተቀይሮ የዋጋ ግምገማ የነጥብ ድርሻ ደግሞ ወደ ሃያ በመቶ (20%) በመቀየር በድምር ከመቶ ይያዛል፡፡ በቴክኒክ ብቃት

ግምገማ ለዋጋ ውድድር የሚያበቃቸውን ውጤት ያላመጡ ተጫራቾች ዋጋ ሳይከፈት እንዲመለስ መደረግ አለበት፡፡

ሐ/ የምክር አገልግሎቱ የሚገኘው ከውጭ ሀገር አማካሪዎች ካልሆነ በስተቀር የሀገር ውስጥ አማካሪዎች የሚያቀርቡት ዋጋ ለግምገማ ዓላማ ሲባል የሀገር ውስጥ ታክስን ይጨምራል፡፡ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር አማካሪዎች የሚያቀርቡት ዋጋ የመጓጓዣ፣ የትርጉም፣ የጽሕፈት ሥራ ወጪን እና የመሳሰሉትን ሊጨምር ይችላል፡፡

መ/ ዝቅተኛ የመጨረሻ ዋጋ ላቀረበው ተወዳዳሪ ሙሉ ነጥብ የሚሰጠው ሲሆን፣ በተነፃፃሪ ከፍተኛ ዋጋ ላቀረበው ተወዳዳሪ አነስተኛ ነጥብ ይሰጣል፤ ሌሎች ተወዳዳሪዎችም የሚያገኙት ነጥብ ባቀረቡት ዋጋ ላይ በመመስረት ተሰልቶ የሚወሰን ይሆናል፡፡

ሠ/ ለቴክኒክ ብቃት ደረጃ እና ለዋጋ የተሰጡትን ነጥቦች በመደመር በአጠቃላይ ውጤት ከፍተኛ ነጥብ ያገኘው ተወዳዳሪ የጨረታው አሸናፊ ሆኖ ይመረጣል፡፡

## 36. በጥራት ላይ የተመሠረተ መረጣ

1) በጥራት ላይ የተመሠረተ መረጣ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው የምክር አግልገሎት ግዥው የሚከተሉትን ሁኔታዎች ሲያሟላ ይሆናል፡፡

ሀ/ የምክር አገልግሎቱ ውስብስብና የተለየ የሙያ ብቃት የሚጠይቅ በመሆኑ ለዚሁ ግዥ የተሟላ ማጣቀሻ ሰነድ ወይም ቢጋር ማዘጋጀት የማይቻል ሲሆን ወይም ከአማካሪው የሚገኘውን የምክር አገልግሎት ዓይነት ለይቶ ማወቅ የማይቻል ሲሆን ወይም አማካሪው የራሱን የፈጠራ ችሎታ ተጠቅሞ የመወዳደሪያ ሀሳብ ማቅረብ የሚኖርበት ሲሆን፣

ለ/ ከፍተኛ ችሎታ ያላቸውን አማካሪዎች ማግኘት አስፈላጊ በሚሆንባቸው እና የወደፊት ውጤታቸው አሳሳቢ የሚሆን ከፍተኛ ጉዳዮች ሲሆኑ፣

ሐ/ የምክር አገልግሎቱ በተለያዩ አማራጭ መንገዶች ሊቀርብ የሚችል በመሆኑ ምክንያት የሚቀርቡትን ሀሳቦች በተመሳሳይ ሁኔታ ማወዳደር አስቸጋሪ እንደሚሆን በልማት ድርጅቱ ሲታመን፣

2) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ 1 ለተመለከቱት መስፈርቶች የልማት ድርጅቱ የቀረቡትን አማካሪዎች ለመምረጥ የሚከተለውን የመገምገሚያ ሂደት መከተል አለበት፡፡

ሀ/ ተጫራቾች የቴክኒክ እና የዋጋ የመወዳደሪያ ሀሳባቸውን ለየብቻ እንዲያቀርቡ ተደርጎ የቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳባቸው በመጀመሪያ እንዲከፈት ይደረጋል፡፡

ለ/ በቴክኒክ ግምገማ ከፍተኛ ውጤት ያገኘው ተጫራች የጨረታው አሸናፊ ሆኖ ይመረጣል፡፡

ሐ/ በቴክኒክ ግምገማው አሸናፊ የሆነው ተጫራች ያቀረበውን ዋጋ በመክፈት የልማት ድርጅቱ ለስራው ከያዘው በጀት የማይበልጥ ከሆነ ውል ይፈርማል፡፡

መ/ በውድድሩ አሸናፊ የሆነው ተጫራች ያቀረበውን ዋጋ የልማት ድርጅቱ ለስራው ከያዘው በጀት የሚበልጥ ከሆነ ከአማካሪው ድርጅት ጋር በድርድር በሚደረስበት ዋጋ ወይም ተጫራቹ ያቀረበውን ዋጋ በድርድር መቀነስ ካልቻለና በቴክኒክ ግምገማው ውጤት ሁለተኛ የወጣው ተጫራች ያቀረበው ዋጋ የልማት ድርጅቱ ለግዥው የያዘው በጀት ጋር የሚመጣጠን ከሆነ ወይም ድርድር በማድረግ ግዥውን ሁለተኛ ከወጣው አማካሪ ድርጅት መፈፀም ይችላል፡፡

ሠ/ በጨረታው አሸናፊ ከሆነው ተጫራች ጋር የውል ስምምነት እንደተፈረመ በቴክኒክ ግምገማ የወደቁ ተወዳዳሪዎች የዋጋ ማቅረቢያ ፖስታ ሳይከፈት ለተጫራቾች ተመላሽ መደረግ አለበት፡፡

## 37. በቁርጥ በጀት ላይ የተመሰረተ መረጣ

የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በቁርጥ በጀት ላይ ተመስርቶ የሚከናወን መረጣ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው የምክር አግልገሎቱ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ሲያሟላ ነው፡፡

1) የሚፈለገው የምክር አገልግሎት ውስብስብነት የሌለው፣ በትክክል ሊገለፅ የሚችል ሲሆን እና ለዚሁ ተግባር የተፈቀደው በጀት ጣሪያ ያለው ከሆነ፤
2) የቴክኒክ ግምገማው የሚከናወነው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 37 በተደነገጉት ሥርዓቶች መሰረት የሚፈፀም ይሆናል፤
3) ለጨረታው ከተያዘው በጀት በላይ ያቀረቡ ተጫራቾ ከጨረታው ውጭ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡
4) ለጨረታው ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን ያልበለጠ ዋጋ ያቀረበና በአጠቃላይ የቴክኒክ እና ፋይናንስ ድምር ውጤት ከፍተኛ ነጥብ በማግኘት የውድድሩ አሸናፊ ከሆነው ድርጅት ጋር  እንደአስፈላጊነቱ ድርድር ሊያደረግ ይችላል፡፡

## 38. በዝቅተኛ ዋጋ ላይ የተመሠረተ መረጣ

በዝቅተኛ ዋጋ ላይ የተመሠረተ መረጣ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው የምክር አግልገሎቱ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ሲያሟላ  ይሆናል፡፡

1) የሚገዛው የምክር አገልግሎት የባለሙያውን ልዩ ችሎታ የማይጠይቅ አነስተኛ የገንዘብ መጠን ያላቸው፣ ውስብስብ ያልሆነና ስታንዳርድ ያለው ወይም በተመሳሳይና ወጥ በሆነ አሠራር ሊከናወን የሚችል ሲሆን ነው፡፡
2) በዚህ የመረጣ ዘዴ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ዝቀተኛውን የቴክኒክ መመዘኛ ነጥብ መጠን በመወሰን ለተመረጡ ተጫራቾች በሚሰጠው የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ሰነድ ላይ ይህንኑ ነጥብ በግልፅ ማመልከት አለባቸው፡፡
3) የቴክኒክ ሀሳቦችን የያዙ የመወዳደሪያ ሰነዶች እንዲከፈቱ በማድረግ የቴክኒክ ግምገማ መከናወን ይኖርበታል፡፡
4) በግምገማው ውጤት ለቴክኒክ ብቃት የተቀመጠውን ዝቅተኛ መሥፈርት ያላሟሉ ተወዳዳሪዎች ከጨረታው ውጭ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡
5) በቴክኒክ ብቃት ግምገማ ለዋጋ ውድድር የሚያበቃቸውን ዝቅተኛ ውጤት ያላመጡ ተጫራቾ የዋጋ መወዳደሪያ ሰነድ ሳይከፈት እንዲመለስ መደረግ አለበት፡
:
6) በቴክኒክ ግምገማ ውጤታቸው ለዋጋ ወድድር ያለፉት ተወዳዳሪዎች የዋጋ መወዳደሪያ እንዲከፈት ይደረጋል፡፡

7) በተጫራቾች የቀረበው ዋጋ በመክፈቻው ሥነ-ሥርዓት ላይ የተገኙ ተጫራቾች እንዲያውቁት መደረግ አለበት፡፡

8) በቴክኒክ ግምገማ ለብቃት ማረጋገጫ የተቀመጠውን ዝቅተኛ መሥፈርት ካሟሉት ተወዳደሪዎች መካከል አነስተኛ ዋጋ የሰጠው ተጫራች የውድድሩ አሸናፊ ሆኖ ይመረጣል፡፡

## 39. በአማካሪዎች ብቃት ላይ የተመሠረተ መረጣ

በአማካሪዎች ብቃት ላይ የተመሠረተ መረጣ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው የምክር አግልገሎቱ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ሲያሟላ ይሆናል፡፡

1) ይህ ዘዴ የስራ ልምድ በማቅረብ የሚፈጸም የሙያ ግዥ ሲሆን ለአማካሪው የሚሰጠው ሥራ የተለየ የሙያ ዕውቀትን የሚጠይቅ በመሆኑ ምክንያት ወይም የመወዳደሪያ ሀሳቦችን ለማዘጋጀት እና ለመገምገም የሚያስፈልገው ጊዜና ወጪ ከሥራው ጋር የማይመጣጠን ወይም አስቸኳይ ሁኔታ በመፈጠሩ ምክንያት ግዥውን በውድድር መፈፀም አሳማኝ ሳይሆን ሲቀር ነው፡፡

2) ይህ ዘዴ ጥቅም ላይ የሚውለው የምክር አገልግሎቱ ግምታዊ ዋጋ ከብር 5,000,000.00 (አምስት ሚሊዮን) የማይበልጥ በሚሆንበት ጊዜ ብቻ ነው፡፡

3) ባለሙያው ያለውን የሥራ ልምድ እና የብቃት ደረጃ እንዲገልጽ የሚጠይቅ ማጣቀሻ ወይም ቢጋር በማዘጋጀት ለተወዳዳሪዎች የፍላጎት መግለጫ መጠየቂያ ተደራሽ መደረግ አለበት፡፡

4) ተወዳዳሪዎች የቀረበውን የፍላጎት መግለጫ መረጃ መሠረት በማድረግ በሚከናወን ግምገማ የተሻለ ሆኖ የተመረጠው ተወዳዳሪ የቴክኒክና የዋጋ ማቅረቢያ ሀሳቡን በአንድ ላይ እንዲያቀርብ በማድረግና በመደራደር በሚደረስ ስምምነት መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል አምስት
# የተገደበ ጨረታ

## 40. በተገደበ ጨረታ የግዥ አፈጻጸም

1) በተገደበ ጨረታ የግዥ ዘዴ የሚፈጸም ግዥ የጨረታ ማስታወቂያ ማውጣት ሳያስፈልግ ቁጥራቸው ለተገደቡ ተሳታፊዎች በአድራሻቸው በጽሁፍ ወይም

በማንኛውም የኤሌክትሮኒክ ዘዴ በሚላክ ግብዣ መሠረት የሚቀርቡ ድርጅቶችን በማወዳደር የጨረታው አሸናፊ የሚመረጥበት የግዥ ዘዴ ነው፡፡

2) የተገደበ ጨረታ አፈጻጸም በዚህ መመሪያ እንደግዥው ዓይነት ለብሔራዊ ወይም ለዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ የተዘረጋውን ሥርዓት ተከትሎ የሚከናወን ይሆናል፡፡

3) የተገደበ ጨረታ የግዥ ዘዴን ለመጠቀም ከሚከተሉት አንዱ መሟላት አለበት፡፡

ሀ/ ዕቃው፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራው፣ የምክር አገልግሎቱ ወይም አገልግሎቶቹ ከተወሰኑ አቅራቢዎች ብቻ የሚገኝ መሆኑ ሲረጋገጥ ያለ ገንዘብ ገደብ ሁሉንም አቅራቢዎች በመጋበዝ፣

ለ/ ግዥውን ለመፈጸም በብሔራዊ ግልፅ ጨረታ ቢያንስ ለአንድ ጊዜ ወጥቶ ጨረታው ካልተሳካ ያለ ገንዘብ ገደብ፣

ሐ/ በተመረጡ ቦታዎች ወይም አከባቢዎች የሚፈጸሙ የሆቴል፣የቢሮ እና መጋዘን አገልግሎቶችን ግዥዎችን በመጋበዝ በተገደበ ጨረታ መፈጸሙ አስፈላጊ መሆኑ ሲታመንበት እና በልማት ድርጅቱ ኃላፊ ሲፈቀድ ያለ ገንዘብ ገደብ፣

መ/ በልማት ድርጅቱ የሚገዙት እንደ የክትባት ምርት ግብዓቶች፣ለምርት ሥራ የሚያስፈልጉ አላቂ ዕቃዎች፣ ለምርምር ሥራ የሚውሉ የተለያዩ ኪቶች፣ የክትባት ማሸጊያ ዕቃዎች፣የመድሐኒት ምርት ግብአቶች እና የመድሐኒት ምርት ማሸጊያዎች የጥራት ደረጃቸው መለያየት ምክንያት ከተወሰኑ አቅራቢዎች የሚገኙ ከመሆናቸው ምክንያት በጨረታ ቢፈጸሙ ውጤታማ ውድድር አይኖርም ተብሎ ሲታመንና በልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ሲፈቀድ ያለ ገንዘብ ገደብ፣

ሠ/ በጨረታው ተሳታፊ ሊሆኑ የሚችሉ አቅራቢዎች ቁጥር በርካታ ቢሆኑም የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ግዥው በብሔራዊ ወይም አለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ ቢፈጸም ብዛት ያላቸውን ተወዳዳሪዎች የመጫረቻ ሰነድ ለመገምገም በቂ ጊዜ የማይኖር ከሆነ ወይም በብሔራዊ የተገደበ ጨረታ ቢፈጸም የተሻለ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎ ሲረጋገጥና

በልማት ድርጅቱ ሲፈቀድ ከዚህ በታች ከተቀመጠው የገንዘብ ገደብ ያልበለጠ ሲሆን፣

i. ለግንባታ ሥራ ዘርፍ ግዥ .... ከብር 100,000,000.00 (አንድ መቶ ሚሊዮን ብር)

ii. ለዕቃ ግዥ ......................... ከብር 25,000,000.00 (ሃያ አምስት ሚሊዮን)

iii. ለምክር አገልግሎት ግዥ...... ከብር 15,000,000.00 (አስራ አምስት ሚሊዮን)

iv. ለምክር ውጭ አገልግሎት ግዥ ........... ከብር 20,000,000.00 (ሃያ ሚሊዮን ብር)

ሠ/ የውጭ ሀገር ተጫራቾች ካልተሳተፉበት በስተቀር ውጤታማ ውድድር ሊኖር አይችልም ተብሎ ሲታመንና በጨረታው ተሳታፊ ሊሆኑ የሚችሉ አቅራቢዎች ቁጥር በርካታ ቢሆኑም የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ግዥው በአለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ ቢፈጸም ብዛት ያላቸውን ተወዳዳሪዎች የመጫረቻ ሰነድ ለመገምገም በቂ ጊዜ የማይኖር ከሆነ በዓለም አቀፍ የተገደበ ጨረታ ከዚህ በታች ከተቀመጠው የገንዘብ ጣሪያ ያልበለጠ ግዥ የሚፈጸም ይሆናል፡፡

ሀ/ ለግንባታ ዘርፍ ሥራ……………… …. ብር 1,500,000,000.00(አንድ ቢሊዮን አምስት መቶ ሚሊዮን ብር)

ለ/ ለዕቃ ግዥ ………………………… ….ብር 500, 000,000.00(አምስት መቶ ሚሊዮን ብር)

ሐ/ ለምክር አገልግሎት ግዥ ……………....ብር 80, 000,000.00 (ሰማኒያ ሚሊዮን ብር)

መ/ ለምክር ውጭ አገልግሎት ግዥ ................ብር 100, 00,000.00 (አንድ መቶ ሚሊዮን ብር)

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 ድንጋጌ ቢኖርም የግንባታ ዕቃዎችን የማቅረብ ኃላፊነት የግዥ ፈጻሚው የመንግሥት የልማት ድርጅትከሆነ የግንባታ

ስራ ዕቃዎች ግዥ ተግባራዊ የሚሆነው ለግንባታ ስራ ግዥ የተፈቀደው የገንዘብ ጣሪያ ይሆናል፡፡

5) በዚህ አንቀጽ መሠረት የተቀመጠውን ጣሪያ የወቅቱን ነባራዊ ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ የገንዘብ ሚኒስቴር ሊያሻሽል ይችላል፡፡

6) የጨረታ ግብዣው እና ለግዥው የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ በውድድሩ ለተጋበዙ ተጫራቾች በጽሁፍ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ እንዲደርስ ማድረግ አለበት፡፡

7) በተገደበ ጨረታ ግዥ ለመፈጸም እስከተቻለ ድረስ በልማት ድርጅቱ ወይም በባለስልጣኑ በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ከተመዘገቡት መካከል ቢያንስ አምስት ተወዳዳሪዎች መመረጥ አለባቸው፡፡

8) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 የተገለጸው ቢኖርም በተገደበ ጨረታ የሚወዳደሩ አምስት አቅራቢዎች ለማግኘት አስቸጋሪ መሆኑ ሲረጋገጥ ከሦስት ያላነሱ ተወዳዳሪዎችን በመጋበዝ ግዥውን መፈጸም ይቻላል፡፡

9) የልማት ድርጅቱ በተገደበ ጨረታ የሚጋበዙ ተጫራቾችን ማንነት ለሌሎች ተወዳዳሪዎች ማሳወቅ የለበትም፡፡

10) በተገደበ ጨረታ የተጋበዙት ተወዳዳሪዎች በሙሉ ከጨረታ መቆያ ጊዜ ገደቡ በፊት የመጫረቻ ሰነዳቸውን ካቀረቡ ወይም ቢያንስ አንድ ተወዳዳሪ የመጫረቻ ሰነድ አቅርቦ ቀሪዎቹ ደግሞ በጨረታው መሳተፍ እንደማይችሉ ካሳወቁ የጊዜ ገደቡ እስከሚጠናቀቅ መጠበቅ ሳያስፈልግ የጨረታ መክፈቻ ጊዜ ለሁሉም ተጫራቾች በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ወይም በጽሁፍ በማሳወቅ እና እንዲገኙ በመጋበዝ ጨረታው እንዲከፈት ሊያደርግ ይችላል፡፡

11) የልማት ድርጅቱ የጨረታ ማስከበሪያ እንዲያስይዙ ማድረጉ የጨረታ ውድድርን ሊገድብ እንደሚችል ሲታመንበት የጨረታ ማስከበሪያ ማስያዝ ሳያስፈልግ ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ሳያሲዙ የመጫረቻ ሰነዳቸውን እንዲያቀርቡ ሊያደርግ ይችላል፡፡

12) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 43 በተገደበ ጨረታ የግዥ ዘዴ ለመፈጸም የተገለጸው ቅድመ ሁኔታና የገንዘብ ጣሪያ ድንጋጌ ቢኖርም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 50 መሰረት በስትራቴጂክ የግዥ ስልት በቅድመ ብቃት ተወዳድረው በልማት ድርጅቶች በአቅራቢነት ከተመዘገቡ ድርጅቶች መካከል የተሻለ ብቃት ያላቸውን ድርጅቶች

በመጋበዝ ከዚህ በታች ከተቀመጠው የገንዘብ ገደብ ያልበለጠ ግዥ መፈጸም ይችላሉ፡፡

ሀ/ ለግንባታ ሥራ ዘርፍ ግዥ .................ብር 750,000,000.00
(ሰባት መቶ ሃምሳ ሚሊዮን ብር)

ለ/ ለዕቃ ግዥ ..... ............ ..................ብር 500,000,000.00
(አምስት መቶ ሚሊዮን ብር)

ሐ/ ለአገልግሎት ግዥ .............................ብር 250,000,000.00
(ሁለት መቶ ሃምሳ ሚሊዮን ብር)

13) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 11 ድንጋጌ ቢኖርም የግንባታ ዕቃዎችን የማቅረብ ኃላፊነት የግዥ ፈጻሚው የመንግሥት የልማት ድርጅት ከሆነ የግንባታ ስራ ዕቃዎች ግዥ ተግባራዊ የሚሆነው ለግንባታ ስራ ግዥ የተፈቀደው የገንዘብ ጣሪያ ይሆናል፡፡

14) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 11 ድንጋጌ ቢኖርም የመንግስት የልማት ድርጅቶች በጨረታ ግብዣ ግዥ ለመፈጸም በቂ ጊዜ የሌለ እና በተገደበ ጨረታ ግዥ መፈጸም የተሻለ ኢኮኖሚ ጠቀሜታ እንዳለው ሲታመንና በልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ሲፈቀድ ያለገንዘብ ጣሪያ በዚህ የግዥ ዘዴ ግዥ መፈጸም ይችላሉ፡፡

## ክፍል ስድስት
## በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈጸም ግዥ

### 41. በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ አፈጻጸም

1) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ወዲያውኑ ጥቅም ላይ የሚውሉ ወይም በጅምላ ሊገዙ ያልቻሉ እና ግምታዊ ዋጋቸው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ከተገለጹት የማይበልጡ ዕቃዎችን፣ የግንባታ ስራዎችን ወይም አገልግሎቶችን በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ ግዥ መፈፀም ይችላሉ፡፡

2) ለአንድ ጊዜ በሀገር ውስጥ በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ የሚፈጸመው ግዥ ከዚህ በታች ከተቀመጠው የገንዘብ ጣሪያ ያልበለጠ ይሆናል፡፡

ሀ/ ለግንባታ ሥራ ዘርፍ ግዥ .......... ከብር 8,000,000.00
(ስምንት ሚሊዮን ብር)

ለ/ ለዕቃ ግዥ ................................. ከብር 4,000, 000.00

(አራት ሚሊዮን ብር)

ሐ/ ለምክር አገልግሎት ግዥ............. ከብር 2,000,000.00

(ሁለት ሚሊዮን ብር)

መ/ ለአገልግሎት ግዥ........................ ከብር 3,000,000.00

(ሁለት ሚሊዮን ብር)

3) የውጭ ሀገር ተጫራቾች ካልተሳተፉበት በስተቀር ውጤታማ ውድድር ሊኖር እንደማይቻል ሲታመን በዓለም አቀፍ ዋጋ ማቅረቢያ ለሚፈጸም ግዥ ከዚህ በታች ከተቀመጠው የገንዘብ ጣሪያ ያልበለጠ ይሆናል፡፡

ሀ/ ለግንባታ ሥራ ዘርፍ ግዥ ...................... ብር 120,000,000.00

(አንድ መቶ ሃያ ሚሊዮን ብር)

ለ/ ለዕቃ ግዥ ............................................... ብር 40,000,000.00

(አርባ ሚሊዮን ብር)

ሐ/ ለምክር አገልግሎት ግዥ............................ ብር 15,000,000.00

(አስራ አምስት ሚሊዮን ብር)

መ/ ለአገልግሎት ግዥ.......................................ብር 20,000,000.00

(ሃያ ሚሊዮን ብር)

4) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 ድንጋጌ ቢኖርም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 50 መሰረት በስትራቴጂክ የግዥ ስልት በቅድመ ብቃት ተወዳድረው በአቅራቢነት ከተመዘገቡ ድርጅቶች መካከል የተሻለ ብቃት ያላቸውን ድርጅቶች በዋጋ ማቅረቢያ በማወዳደር ከዚህ በታች ከተቀመጠው የገንዘብ ገደብ ያልበለጠ ግዥ መፈጸም ይችላሉ፡፡

ሀ/ ለግንባታ ሥራ ዘርፍ ግዥ ............. ብር 50,000,000.00

(ሃምሳ ሚሊዮን ብር)

ለ/ ለዕቃ ግዥ ............................... ብር 30,000,000.00

(ሰላሳ ሚሊዮን ብር)

ሐ/ ለአገልግሎት ግዥ ...........................ብር 20,000,000.00

(ሃያ ሚሊዮን ብር)

5) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2፣ 3 እና 4 ድንጋጌዎች ቢኖርም የግንባታ ዕቃዎችን የማቅረብ ኃላፊነት የልማት ድርጅቱ ከሆነ የግንባታ ግብዓቶችን ግዥ ተግባራዊ የሚሆነው ለግንባታ ሥራ ግዥ የተፈቀደው የገንዘብ ጣሪያ ይሆናል።

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2፣ 3 እና 4 መሠረት የተቀመጠውን ገንዘብ ጣሪያ የወቅቱን ነባራዊ ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ የገንዘብ ሚኒስቴር ሊያሻሽል ይችላል።

7) በዚህ አንቀጽ የተደነገገው የገንዘብ ጣሪያ ቢኖርም የልማት ድርጅቱ የግንባታ ሥራን ለማከናወን ውል የገባ ከሆነ እና የግንባታ ሥራውን ለማከናወን ጥቅም ላይ የሚውሉት የግንባታ ግብአቶች የተወሰኑ አቅራቢዎች ያሉት ሲሆን፣ ለልማት ድርጅቱ አስተማማኝ አቅርቦት ማስገኘቱ በልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ሲታመንበት እንደ አርማታ ብረቶች፣ ሲሚንቶ፣ የተዘጋጀ አርማታ፣ የሴራሚክና ሳኒታሪ፣ የኤሌክትሪክ ኬብሎች፣ አሉሚኒየምና የአሉሚኒየም ውጤቶች፣ የተለያዩ ዓይነትና መጠን ያላቸው ብረቶችን እስከ 100,000 (አንድ መቶ ሚልየን) ብር ድረስ በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ ግዥውን መፈጸም ይቻላል።

8) የልማት ድርጅቱ በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ ሲፈጽም በውድድሩ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚመረጡት በልማት ድርጅቱ ወይም በባለስልጣኑ በተመዘገቡ ከአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የሚመረጡ ሆነው እስከተቻለ ድረስ ቁጥራቸው ከሶስት ማነስ አይኖርበትም። ሆኖም የተመዘገበ ተወዳዳሪ ከሌለ የመንግሥት የልማት ድርጅቶቹ ካልተመዘገቡ ተወዳዳሪዎች ግዥ መፈጸም ይችላሉ።

9) የልማት ድርጅቱ የተጋበዙ አቅራቢዎች ማንነትን ለሌሎች ለተጋበዙት አቅራቢዎች ማሳወቅ የለበትም።

10) እያንዳንዱ ተወዳዳሪ እንዲያቀርብ የሚፈቀድለት አንድ የመወዳደሪያ ዋጋ ብቻ ሆኖ ያቀረበውን ዋጋም መለወጥ አይፈቀድለትም።

11) የተለየ ሁኔታ ከሌለ በስተቀር የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የሚፈልገውን የጥራት ደረጃ የሚያሟሉ አቅርቦቶችን በማወዳደር ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበውን ተጫራች አሸናፊ አድርገው መምረጥ አለባቸው።

12) በዋጋ ማቅረቢያ ለሚፈፀም ግዥ የሚደረገው የዋጋ ውድድር በ ተወዳዳሪዎች መካከል ተመሳሳይ ይዘት ያለው የዋጋ ስሌት መሆን ያለበት ሲሆን ውድድሩ ታክስን ያካተተ መሆን ይኖርበታል።

13) የዋጋ ማቅረቢያ የሚሰበስቡ የግዥ ክፍሎች የተሰበሰበው የዋጋ ማቅረቢያ በስፔስፊኬሽኑ መሠረት ስለመሆኑ እና ከተለያዩ ድርጅቶች የተሰበሰበ ስለመሆኑ ማረጋገጥ አለባቸው::

## ክፍል ሰባት
## በቀጥታ የሚፈጸም ግዥ

### 42. በቀጥታ የሚፈጸም ግዥ አፈጻጸም

ከሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች ቢያንስ አንዱ መሟላቱ ሲረጋገጥ እና በልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ሲፈቀድ በቀጥታ ግዥ መፈጸም ይቻላል፡፡

1) በዓይነት እና በዋጋ አንድ የሆኑ ዕቃዎችን፣ የምክር እና ሌሎች አገልግሎቶችን ቀደም ሲል እነዚህን ካቀረበ አቅራቢ መግዛት ጠቃሚ መሆኑ ሲታመን በአቅራቢው ፈቃደኝነት ላይ በመመስረትና የሚከተሉትን አሠራሮች በመከተል ተጨማሪ ግዥ ለመፈፀም ይቻላል፡፡

   ሀ/ በተጨማሪነት የሚታዘዘው ዕቃ፣ የምክር ወይም ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎቶች ግዥ መጠን ከመጀመሪያው ውል ያልበለጠ፣

   ለ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ) መሠረት ተጨማሪ ግዥ ለማዘዝ የቀድሞው ግዥ ውል ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ወይም ውሉ ከተጠናቀቀበት ቀን አንስቶ በሚቀጥሉት 12 (አስራ ሁለት) ወራት ጊዜ ውስጥ መሆን አለበት፡፡

   ሐ/ በዚህ መሠረት ግዥ ሲፈጸም በመጀመሪያው ውል ከነበረው የነጠላ ዋጋ የበለጠ የዋጋ ጭማሪ ማድረግ አይፈቀድም፣

   መ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሐ) የተቀመጠው ቢኖርም የመጀመሪያው ውል የዋጋ ማስተካከያ የሚፈቅድ ከሆነ እና የዋጋ ማስተካከያ የተደረገ ከሆነ ግዥው የሚፈጸመው በተስተካከለው ዋጋ መሠረት ይሆናል፡፡

2) የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን አረጋግጠው ያልታሰቡና በመጀመሪያው ውል ውስጥ ያልተካተቱ ተጨማሪ እና ተመሳሳይ የግንባታ ሥራዎችን ማሠራት ይችላሉ፡፡

ሀ/ የልማት ድርጅቱ በተጨማሪነት እንዲሰሩ የታሰቡት ስራዎች በመጀመሪያው ውል ውስጥ መካተት ይገባቸው የነበሩ ወይም ከዋናው ስራ ጋር ቢካተቱ የተሻለ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚኖራቸው እና ስራዎቹን ነጣጥሎ ማሰራት ለአፈፃፀም አስቸጋሪ ወይም የልማት ድርጅተቱን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የሚጎዳ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ለ/ በዓይነትና በዋጋ ተመሳሳይ የሆኑ ወይም በዋናው ሥራ ውስጥ ያልተካተቱ አዲስ የግንባታ ሥራዎች የገንዘብ መጠን ከመጀመሪያው ውል ጠቅላላ ዋጋ ከአርባ በመቶ (40%) የበለጠ መሆን የለበትም፣

ሐ/ በተጨማሪነት የሚታዘዙት የግንባታ ሥራዎች የነጠላ ዋጋ በውል ውስጥ ሊገኝ የሚችል ከሆነ የተጨማሪው ስራ በውል ውስጥ ባለው ነጠላ ዋጋ መሠረት ወይም የዋጋ ማስተካከያ የተደረገ ከሆነ በተስተካከለው ዋጋ መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ የነጠላ ዋጋው ውል ውስጥ የማይገኝ ከሆነ በድርድር ስምምነት ላይ የሚደረስበት ዋጋ የገበያ ዋጋ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

3) አስቀድሞ ለተገዙ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ተንዳኝ ወይም መለዋወጫ ዕቃዎችን ወይም ተጨማሪ አገልግሎቶችን መግዛት ሲያስፈልግ እና እነዚህን ተንዳኝ ወይም መለዋወጫ ዕቃዎችን ወይም ተጨማሪ አገልግሎቶችን ከሌላተወዳዳሪ መግዛት የልማት ድርጅቱ ከሚጠቀምበት ዕቃ ወይም አገልግሎት ጋር የማይጣጣም በመሆኑ ምክንያት ከመጀመሪያው አቅራቢ መግዛት የግድ ሲሆን በቀጥታ ግዥ መፈጸም ይቻላል፡፡

4) ዋጋቸው በመንግስት የሚወሰን ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ሲሆኑ፣ መንግስት በወሰነው ዋጋ መሠረት ግዥ መፈጸም የተሻለ ጠቀሜታ የሚያስገኝ መሆኑ ሲረጋገጥ በቀጥታ ግዥ መፈጸም ይቻላል፡፡

5) ግዥው አስቸኳይ ከመሆኑ የተነሣ የምርት፣ የንግድና አገልግሎት ወይም የግንባታ ስራ እንዲቆም የሚያደርግ እና በልማት ደርጅቱ የሥራ አፈጻጸም ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር መሆኑ ሲረጋገጥ በቀጥታ ግዥ መፈጸም ይቻላል፡፡

6) ያገለገሉ መሣሪያዎችን እና መለዋወጫዎችን ግዥ መፈጸሙ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ በቀጥታ ግዥ መፈጸም ይቻላል፡፡

7) ከመደበኛ አቅራቢዎች የማይገኙ ወይም በለቀማ ቢገዙ ለልማት ድርጅቱ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የሚኖራቸው መሆኑ ሲረጋገጥ የለቀማ ግዥ መፈፀም ይቻላል፡፡ የግዥውን መጠን ታሳቢ በማድረግ በዚህ አግባብ ግዥውን ለመፈጸም እንደ አስፈላጊነቱ ብዛታቸው ከሦስት ያላነሱ ጊዜያዊ ኮሚቴ ሊቋቋም ይችላል፡፡ በዚህ አንቀጽ የሚቋቋመው ኮሚቴ ከዚህ በታች የተቀመጠውን የአሰራር ሥርዓት በመከተል ግዥውን መፈጸም አለበት፡

ሀ) ኮሚቴው በጋራ በመሆን በገበያው ውስጥ ካለው አቅርቦት የተሻለ ጥራት እና ዋጋ ያለውን ወይም ያላቸውን ሻጮች በመምረጥ ዋጋ ተደራድሮ ግዥውን ይፈፅማል::

ለ) በግዥው አፈፃፀም ሂደት የተፈፀሙትን ግዥዎች ብዛትና ዓይነት፣ ግብይቱ የተፈፀመበትን ቦታ፣ የተከፈለውን የገንዘብ መጠን፣ የሻጮችን ሙሉ ስምና አድራሻ የሚገልፅ ሠነድ ተዘጋጅቶ ሻጮች በፊርማቸው እንዲያረጋግጡ መደረግ ይኖርበታል::

ሐ) በለቀማ የተገዙ ግዥዎች በሚጓጓዙበት ወቅት እንዳይበላሹ እና እንዳይጠፉ በጥንቃቄ መያዝ እና በተቻለ ፍጥነት የሚመለከተው ክፍል እንዲረከባቸው መደረግ አለበት::

መ) ኮሚቴ አጠቃላይ የለቀማ ግዥ አፈፃፀሙን የሚገልፅ ቃለ-ጉባኤ በማዘጋጀት ተፈራርሞ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል:: ሪፖርቱም ኮሚቴውን ባቋቋመው የሥራ ኃላፊ መፅደቅ ይኖርበታል::

8) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በግዥ ዕቅድ ውስጥ ያልተካተቱ እና አነስተኛ የገንዘብ መጠን ያላቸውን ወይም ዋጋቸው ከብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ) ያልበለጡ ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ወይም በጉዞ ወቅት የሚያጋጥሙ ወይም ግዥው በአስቸኳይ በመፈጸም ችግሮችን ከመፍታት ጋር የተያዙ ጥቃቅን ግዥዎችን ከማናቸውም ሻጭ ድርጅት መፈፀም ይችላሉ፡፡ ሆኖም በዚህ ዓይነት የሚፈፀሙ ጥቃቅን ግዥዎች ድምር በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ ከብር 3,000,000.00 (ሶስት ሚሊዮን ብር) መብለጥ አይኖርበትም፤

9) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ለሚኖራቸው የዕቃ እና አገልግሎት ግዥ ፍላጎት ከሌላ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ወይም በሥራችው ከሚገኙ ተቀጽላ ኩባንያዎች ግዥ ለመፈጸም ሲፈለግና ከወቅታዊ የገበያ ዋጋ ወይም ሌሎች ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አኳያ የተሻለ ሲሆን በቀጥታ ግዥ መፈጸም ይቻላል፡፡

10) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባላቸው የተለየ የስራ ባህሪ ምክንያት በውድድር ሊገኙ የማይችሉ ለጥናትና ምርምር እንዲሁም ሚስጥራዊነታቸው ተጠብቆ ሊፈጸሙ የሚገባቸው ግዥዎችን መሆናቸው ሲረጋገጥ በቀጥታ ግዥ መፈጸም ይቻላል፡፡

11) የልማት ድርጅቱ የሚፈልገውን ዕቃ፣ የሶፍት ዌር ፍቃድ፣ የኢንፎርሜሽን ሲስተም፣ የዲጂታል መገልገያዎችና የመሰረተ ልማት ጥገናና ድጋፍ፣ የምርት ዲዛይን ሰነዶችን፣ የአዕምሯዊ ንብረቶችን፣ የማሽነሪ ኢንስታሌሽን፣ ኮሚሽኒንግ፣ የዲዛይን፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር እና የፈጠራ ባለቤትነትን ጨምሮ የቴክኖሎጂ መፍትሄዎችን እና የመሳሰሉትን በቀጥታ ግዥ መፈጸሙ ከጊዜ፣ ከጥራት እና ከዋጋ አንጻር የተሻለ ጠቀሜታ የሚያስገኝ መሆኑ ሲረጋገጥ በቀጥታ ግዥ መፈጸም ይቻላል፡፡

12) በአጭር ጊዜ የሚቆይ፣ ለልማት ድርጅቱ ልዩ ጥቅም በሚያስገኝ ሁኔታ የሚፈጸም እና ከመደበኛ አቅራቢነት ከተሰማሩ ተወዳዳሪዎች ለመፈጸም አስቸጋሪ የሆነ ዕቃ ወይም አገልግሎት ግዥ መፈጸም የሚቻለው፤

ሀ/ ከመደበኛ ጊዜ ውጭ በተለያዩ መርሐ ግብሮች በተዘጋጁ የንግድ ትርዒት፣ በዓላትና ዐውደ ርዕይ ላይ ለሽያጭ የሚቀርቡት ዕቃና አገልግሎቶች፣

ለ/ የተለያዩ ድርጅቶች ምርትና አገልግሎቶቻቸውን በማስተዋወቂያ ዋጋ ሲያቀርቡ ወይም ንብረቶቻቸውን ለማስወገድ የሚያቀርቡት ሽያጭ ላይ መሳተፍ ለልማት ድርጅቱ የሚፈለግና አዋጭ ሆኖ ሲገኝ፣

13) የልማት ድርጅቱ ቀደም ሲል በሌላ የመንግሥት የልማት ድርጅትበግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ ከተገዙ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ጋር በዓይነትና በዋጋ አንድ ዓይነት የሆኑ ግዥዎችን የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው፡፡

ሀ/ ቀደም ሲል ከተፈጸመው የውል ዋጋ፣ በዓይነትና በዋጋ አንድ ዓይነት የሆነና ከወቅታዊ የገበያ ዋጋ አንጻር አዋጭ ሲሆን፣

ለ/ የሚፈጸመው ግዥ ቀደም ሲል ውል ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ወይም ውሉ ከተጠናቀቀ ከአንድ ዓመት በላይ ያልሆነው ሲሆን፣

14) የልማት ድርጅቱ የዲጅታል፣ የብራንዲንግ፣ የማርኬቲንግ፣ የትምህርትና ሥልጠና፣ የዕቃ ግዥ እና የምክር አገልግሎት የሚሰጡና የአገልግሎታቸው ደረጃ ዓለም አቀፍ እውቅና ያላቸው ከሆኑና የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች ሲሟሉ በቀጥታ ግዥ መፈጸም ይቻላል፣

ሀ/ የልማት ድርጅቱ ቀደም ብሎ ባለው ልምድና መረጃ መሠረት ጠቃሜታ እንዳላቸው ሲረጋገጥ፣ ወይም

ለ/ እነዚህን አገልግሎቶች በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ለመፈጸም አስቸጋሪ መሆናቸው ሲሆን፣ ወይም

ሐ/ ከጥራት፣ ከጊዜ እና ከዋጋ አንጻር እነዚህን ግዥዎችን በቀጥታ መፈጸም ጠቀሜታ እንዳለው ሲረጋገጥ፡፡

15) ለእንስሳት መድሀኒት ምርት ሥራ የሚያስፈልጉ አላቂ ዕቃዎች ፣በበቂ መጠን የማግኘት በተመሳሳይ የጥራት ደረጃ የማግኘት ችግሮች፣ ከእነዚህ የተወሰኑት ከሀገር ውስጥ እንዲሁም ውጭ በተወሰኑ አቅራቢዎች እጅ ብቻ የሚገኙ፣ ረጅም የማምረቻ ጊዜ የሚጠይቁ መሆናቸው ሲረጋገጥ፣

16) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የኢትዮጵያ መንግሥት ከተለያዩ አምራች አገራት ወይም ተዛማጅ አገልግሎት ሰጪዎች ጋር በሚኖረው መልካም ዲፕሎማሲያዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ላይ ተመስርቶ ከአገራት ጋር በሚደረጉ የሁለትዮሽ ስምምነት መሰረት የአገሪቱንና የድርጅቱን ጥቅም በሚያስጠብቅ መልኩ የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች ቢያንስ አንዱ ሲሟላ በቀጥታ ግዥ መፈጸም ይችላሉ፡፡

ሀ/ በአቅርቦት አስተማማኝነት፣በዋጋ እና በክፍያ የእፎይታ ጊዜ ብሔራዊ ጠቀሜታ የሚያስገኝ መሆኑ ሲታመንበት፣ወይም

ለ/ ለልማት ድርጅቱ ከሚሰጠው ጥቅም አንጻር ሊታዩ የሚችሉ አማራጭ አቅራቢዎችን የማጥናትና የማፈላለግ ሥራውል የሚከናወን ሲሆን፣ የተመረጠው አማራጭ ከዋጋ፣ከክፍያ የእፎይታ ጊዜ እና ከአቅርቦት አስተማማኝነት አንጻር ተገምግም ጠቀሜታ ሲኖረው፣ወይም

ሐ/ ከጥራት፣ከጊዜ እና ከዋጋ አንጻር እነዚህን ግዥዎችን በቀጥታ መፈጸም ጠቀሜታ እንዳለው ሲረጋገጥ፣

## 43. ልዩ የቀጥታ ግዥ አፈጻጸም

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 45 መሠረት በቀጥታ ግዥ ለመፈጸም የተቀመጡት ቅድመ ሁኔታዎች ቢኖሩም ከዚህ በታች ከተቀመጡት ውስጥ አንዱ ከተሟላ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 50 መሰረት በስትራቴጂክ የግዥ ስልት የቅድመ ብቃት ግምገማውን ተወዳደድረው በአቅራቢነት ከተመዘገቡት ድርጅቶች ውስጥ ወይም ከሌሎች አቅራቢዎች (ገበሬዎች፣ አምራቾች፣ አከፋፋዮች፣ እና ከሌሎች ተመሳሳይ የዕቃ እና አገልግሎት አቅራቢዎች) በቀጥታ ግዥ መፈጸም ይችላል፡ -

1) ለግንባታ ፕሮጀክቶች የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በተመለከተ፡

ሀ/ የሚሰራው የግንባታ ስራ በአጭር ጊዜ የሚጠናቀቅ ከሆነና በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ግዥ ለመፈጸም በቂ ጊዜ የሌለ ሲሆን፣

ለ/ የግንባታ ስራውን የሚያሰራው አካል ወይም ደንበኛው ለግንባታ ስራው የሚያስፈልገው ግብዓት የተለየ ብራንድ ወይም የአንድ ወይም የተወሰኑ አምራቾች ምርት በሚፈልጉበት ወቅት ወይም በሚያሰራው አካል ወይም ደንበኛው የተመረጠ ንዑስ ስራ ተቋራጭ ወይም አማካሪ ሲሆን፣

ሐ/ የኮንስትራክሽን መሣሪያዎችና ማሽነሪዎች፣ የግንባታ ሥራዎች በተናጠል ወይም በጥቅል፣ በፕሮጀክቶች ቀጥተኛ ሥራ ላይ የሚሳተፉ የግንባታ ላይ የሚሳተፉ የግንባታ ሙያተኞች፣ የቀን ሠራተኞች እንዲሁም ልዩ ልዩ የምህንድስና አገልግሎቶች በተጨማሪም የተዘጋጀ

የአርማታና የአስፋልት ውህድ፣ ኮንክሪት ፓይፕ፣ የግንብ ድንጋይ፣ አሸዋ፣ ጠጠር፣ ቤዝኮርስ፣ ሰብቤዝ በቁርጥ ዋጋ ላይ ተመስርቶ ግዥውን መፈጸም ሲቻል እና ይህም ለድርጅቱ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንደሚያስገኝ በድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ሲረጋገጥ በቁርጥ ዋጋ ያለገደብ ግዥ ሊፈፀም ይችላል፤

2) ለምርትና አገልግሎት የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በተመለከተ፡

ሀ/ የሚፈለገው ምርት ወይም ማሽነሪ ወይም ተሽከርካሪ በአጭር ጊዜ የሚጠናቀቅ ከሆነና በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ግዥ ለመፈጸም በቂ ጊዜ የሌለ በመሆኑ ምክንያት፣

ለ/ የምርቱ ወይም አገልግሎቱ ተጠቃሚ አካል ወይም ደንበኛው ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ለማምረት ወይም ለማከናወን የተለየ የንግድ ምልክት ወይም የአንድ ወይም የተወሰኑ አምራቾች ምርት በሚፈልጉበት ወቅት፣

ሐ/ ለምርቱ አካል የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን እና አገልግሎቶችን ምርት በማስረከቢያው ጊዜ ውስጥ ግዥ በመፈጸም በአስቸኳይ ማሟላት አስፈላጊ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

መ/ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ወይም ለምርምር እና ልማት ላይ የሚያግዙ አገልግሎቶችን ወይም ምርቶችን ለማግኘት፣

ሠ/ በቴክኖሎጂ አተገባበር፣ በንድፍ ስልቶች እና በአመራረት ዘዴዎች ላይ ምክር ለማግኘት የውጭ ባለሙያዎችን በማሳተፍ የሚፈጸም ግዥ፣

ረ/ ከአንድ ወይም ከጥቂት አምራቾች፣ አቅራቢዎች ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ጋር በመደራደርና የረጅም ጊዜ የማዕቀፍ ውል በመፈራረም የሚፈፀም ግዥ ሲሆን ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ቢያንስ አንዱ ሲሟላ ይሆናል፡፡

i. የቴክኖሎጂ ችግርን ለመቋቋም እና የአቅርቦት አስተማማኝነትን ለማረጋገጥ፣

ii. በሌሎች አማራጭ የግዥ ሥልቶች ከመጠቀም ይልቅ በማዕቀፍ ውል ግዥ ዘለቄታ ያለው የዋጋ ጠቀሜታ ሊገኝ መቻሉ ሲረጋገጥ፣

iii. የልማት ድርጅቱን የተወዳዳሪነት ብቃት ለማረጋገጥ፤

3) ለንግድ ዘርፍ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በተመለከተ፡

ሀ/ ለንግድ ዘርፍ የሚፈለገው ግብዓት በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚፈለግ ከሆነና በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ግዥ ለመፈጸም በቂ ጊዜ የሌለ በመሆኑ ምክንያት፣

ለ/ በሀገሪቱ ከፍተኛ የሆነ የምርት እጥረትና አቅርቦት ችግር ሲያጋጥም ወይም አጣዳፊና ጊዜ የማይሰጡ ሁኔታዎች ሲፈጠሩና ፍላጎቱን ለማሟላት በውድድር ግዥ መፈጸም የማይቻልበት ሁኔታ መኖሩ በገበያ ጥናት ሲረጋገጥ፣

ሐ/ ግዥ የሚፈጸምለት አካል ወይም ደንበኛ ፍላጎት የተለየ ምርት ወይም አገልግሎቱ የንግድ ምልክት የተለየ ፍላጎት ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ፣

መ/ አምራቾችን ከማበረታታት ወይም ለሸማቹ ማህበረሰብ ዋጋ ለማረጋጋት ጠቃሚ ሆኖ ሲገኝ፣

ሠ/ ከአንድ ወይም ከጥቂት አምራቾች፣ አቅራቢዎች ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ጋር በመደራደርና የረጅም ጊዜ የማዕቀፍ ውል በመፈራረም የሚፈፀም ግዥ ሲሆን ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ቢያንስ አንዱ ሲሟላ ይሆናል፡፡

i. በሌሎች አማራጭ የግዥ ዘዴዎች ከመጠቀም ይልቅ የተረጋገጠ ዘለቄታ ያለው የዋጋ፣ የጥራት እና የጊዜ ጠቀሜታ ሊገኝ መቻሉ ሲረጋገጥ፤

ii. ዓመቱን ሙሉ ለማይመረቱ ወቅታዊ ምርቶች የአቅርቦቱን አስተማማኝነት ለማረጋገጥ፣

ረ/ በተፈለገው የምርት ጥራት ደረጃ መሰረት በሚወሰነው የመግዣ ዋጋ መሠረት ከምርት ሰብሳቢዎች ወይም ከአምራቾች በቀጥታ ምርት ለመግዛት፣

ሰ/ የውጭም ሆነ የሀገር ውስጥ አምራቾች ከሚያስቀምጡት ዝቅተኛ የግዥ መጠን በታች ዕቃዎቻቸውን ለመሸጥ ፈቃደኛ ካልሆኑ ወይም በመረጧቸው ወኪል አከፋፋዮችና አስመጪዎች በኩል እንዲገዛ ሲያስገድዱ እና በዋጋ፣ በጥራትና በጊዜ የተሻለ ጥቅም እንደሚያስገኝ ሲታመንበት፣

ሸ/ ዓለም አቀፍ ወይም ከሀገር ውስጥ የደንበኛው ፍላጎትና ጥያቄ ላይ በመመስረት በሚደረግ የውል ስምምነት መሠረት በቀጥታ ከአምራቾች፣ ከአቅራቢዎች፣ ከኮሚሽን ኤጀንቶች፣ ከወኪል አከፋፋዮችና አስመጪዎች በቀጥታ የሚፈጸም ግዥ፣

ቀ/ የዓለም አቀፍ ወይም የሀገር ውስጥ ግዥ ፈጻሚዎችን ፍላጎት የሚያሟሉ የተለያዩ የግብርና ምርቶች ግዥ እንዲፈጸምላቸው ለድርጅቱ ፍላጎታቸውን ሲያቀርቡ ወይም የልማት ድርጅቱ የግዥ ፍላጎት ከሆነ ዱካውን በመከተል ምንጩ የታወቀ ወይም በገዥው ምርጫ መሠረት በቀጥታ ትስስር ፍላጎቱ ከሚገኝበት አቅራቢዎችና አምራቾች የሚፈጸም ግዥ፣

በ/ ከልማት ድርጅቱ ባለው አደረጃጀትና ባሉት የግዥ አውታሮች በተለያዩ ምክንያቶች መድረስ በማይችልባቸው አካባቢዎች ግዥውን ለማጉልበትና አምራቹንም ለማበረታታት ድርጅቱ በመረጠው ወኪል ኮሚሽን በመክፈል የሚፈጸም የዕቃ ወይም የአገልግሎት ግዥ፣

ተ/ የልማት ድርጅቱ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ (ECX) ያለውን ወንበር ተጠቅሞ የምርት ገበያው የሚያቀርባቸውን ምርቶች ለራሱና ወንበር ለሌላቸው ደንበኞች በኮሚሽን የሚፈጽም ግዥ፣

ቸ/ በአርሶ አደሩ ከፍተኛ ምርት በሚመረትበትና የነፃ ገበያው ዋጋ ከአምራቹ የማምረቻ ዋጋ በታች በሚሆንበት ወቅት አርሶ አደሩን ለማበረታታት ከተከናወነው የወቅቱ ምርት ግምገማ በመነሳት የልማት ድርጅቱ ለመንግስት አቅርቦ በሚያስወስነው የወለል ዋጋ መሠረት የሚፈጸም ግዥ፣

ነ/ የልማት ድርጅቱ ኢንዱስትሪ ግብዓቶችን የሚያቀርቡ እና የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን ተጠቅመው የኢንዱስትሪ ውጤቶችን የሚያመርቱ

ድርጅቶች በሚያደርጉት ስምምነት የጥራት፣ የማቅረቢያ ጊዜ፣ የመጠንና ዋጋ መሠረት ግብዓቱን ከአቅራቢው በቀጥታ መግዛት ይችላል፣

ኘ/ የልማት ድርጅቱ ከአቅራቢዎች ጋር በቀጥታ በመደራደር እና በተወሰነ ጊዜ ገደብ ውስጥ ክፍያ መፈጸም የሚያስችል ስምምነት በማድረግ በቅድሚያ ዕቃዎች እና አገልግሎቶች በመረከብ የዱቤ ውል በመፈራረም ግዥ ሲፈጸም ከዚህ በታች የተገለጹትን አሰራሮች ተከትለው ነው፡፡

i. አቅርቦቱን አስተማማኝ፣ ትርፋማና ዘላቂ ለማድረግ፣
ii. አስቀድሞ በተሰበሰበው የገበያ መረጃ መሠረት የመግዣና የመሸጫ ዋጋ በመወሰን ይሆናል፣
iii. የሚፈፀመው ግዥ ያለውን የፋይናንስ አቅም ጥንካሬ መገምገም አለበት፣

አ/ የሀገር ውስጥና የአለም ገበያ ዋጋን መሠረት በማድረግ ከአቅራቢዎች ድርጅቶች፣ ከአምራቾች፣ ከማህበራትና ከኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዮኖች እና አርሶ አደሮች ምርቱን ሲያቀርቡ እንደ ጥራት ደረጃው ግዥ በሚወሰን ቁርጥ ዋጋ መሠረት የሚፈጸም ሲሆን የሚከተሉት ሁኔታዎች ታሳቢ አድርጎ ይከናወናል፡፡

i. የምርት የጥራት ደረጃ አስቀድሞ ወጥቶ ለየደረጃቸው ቁርጥ የመግዣ ዋጋ መተመን አለበት፣
ii. ተለዋዋጭ ዋጋ ሊኖራቸው ይችላል ተብለው ለተለዩ ምርቶች ዋጋቸው እንደ አስፈላጊነቱ በየጊዜው መከለስ ይኖርበታል፣

## ክፍል ስምንት

## በልዩ ፈቃድ የሚፈጸም ግዥ

### 44. በልዩ ፈቃድ የሚፈጸም ግዥ አጠቃላይ ድንጋጌ

1) በአዋጁ አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት በግዥ አዋጁና በዚህ የአፈጻጸም መመሪያ መሠረት በተፈቀዱ የግዥ ዘዴዎች፣ ሰነዶች፣ አሰራሩን ከሚመሩ የጨረታ ሰነዶችና ቅጾች፣ ሌሎች ለግዥ አፈጻጸም አግባብነት ባላቸው ሰነዶች መሠረት ግዥን ለመፈጸም ወይም ውልን ተፈጻሚ ለማድረግ በማይቻልበት ወቅት በሚቀርብ የልዩ ፈቃድ ጥያቄ መሠረት የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ በልዩ ሁኔታ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በልማት ድርጅቶች ሥር የተቋቋሙ ተቀጽላ ድርጅቶች ለሚኖራቸው የልዩ ሁኔታ ግዥ ጥያቄ የልዩ ሁኔታ ፈቃድ ሊሰጥ የሚገባው ደርጅቱን የሚመራው የበላይ ኃላፊ ነው፡፡

### 45. የልዩ ሁኔታ ፈቃድ አቀራረብና ምላሽ አሰጣጥ ላይ መከተል የሚገባቸው መርሆዎች

1) የልዩ ፈቃድ ጥያቄ ሲቀርብ ግዥ ሂደቶችን ወይም መደበኛ የግዥ አሠራርን መከተል የማይቻልበትን ምክንያቶች በመዘርዘር በልዩ ሁኔታ ግዥውን ለመፈጸም ለምን እንዳስፈለገ ግልጽ እና አሳማኝ ማብራሪያ መሰጠት እና በቂ ደጋፊ ሰነድ መቅረብ አለበት፡፡

2) የሚጠየቁ የልዩ ፈቃድ ጥያቄዎች መደበኛውን የግዥ ስርዓት ተከትሎ ለመፈጸም የማይቻል መሆኑን መረጋገጥ አለበት፡፡

3) የሚጠየቁ የልዩ ፈቃድ ጥያቄዎችና ምላሾች ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጠቀሜታ እንዲገኝ፣ ግዥው በተያዘለት ጊዜ እንዲፈጸም ወይም ውሳኔ እንዲያገኝ በሚያስችል መልኩ በወቅቱ ምላሽ መስጠትን ያካትታል፡፡

4) በልዩ ፈቃድ የሚፈጸሙ ግዥዎችን አፈጻጸም መገምገም ለሚጠየቁ የልዩ ፈቃድ ጥያቄዎች ከሚሰጡ ምላሾች በስተቀር ሌሎች መደበኛ አሰራሮችን ጠብቀው መከናወናቸውን የማረጋገጥ፣

5) የሚሰጡ ምላሾች ሚዛናዊ እና መረጃን መሠረት ያደረጉ መሆናቸውን ማረጋገጥ እና ለተሰጡ ምላሾችና የተሰጡ ውሳኔዎች በተቻለ መጠን ምክንያቶችን መግለጽን ይጠይቃል፡፡

## 46. የልዩ ፈቃድ አቀራረብና ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት

1) የሚቀርቡ የልዩ ፈቃድ ጥያቄዎች ግዥ ህጉን እና የአሰራር ሥርዓቱን ተከትሎ ሊፈፀም ያልተቻለበትን ምክንያት ማብራሪያዎች እና ደጋፊ ሠነዶችን በማያያዝ ግዥውን ከሚመራው የስራ ክፍል ኃላፊ ተረጋግጠውና እና ተፈርመው ለልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ መቅረብ አለበት፡፡
2) የሚቀርቡ የልዩ ፈቃድ ጥያቄዎች የአቅርቦት ወይም የአገልግሎት ጊዜ፣ ሊያወጣ የሚችለው ግምታዊ ዋጋ፣ የተጨማሪ የግንባታ ሥራዎች መጠን፣ የግንባታ ሥራዎቹ የፊዚካል አፈጻጸም እና ሌሎች መረጃዎችን በግልጽ ማረጋገጥ አለባቸው፡፡
3) ግዥውን በልዩ ሁኔታ ለመፈጸም በቀረበው አማራጭ ቢፈፀም ከጥራት፣ ከወጪና ከጊዜ አንፃር የሚያስገኘውን ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጠቀሜታ ማረጋገጥ አለባቸው፡፡
4) በልዩ ሁኔታ ለማስፈቀድ የሚቀርቡ ማብራሪያዎች እና ማስረጃዎች እንደተጠበቁ ሆነው የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ተጨማሪ ማብራሪያዎች እና የሰነድ ማስረጃዎች ሊጠየቅ ይችላል፡፡
5) የቀረቡትን ማስረጃዎች እና ማብራሪያዎችን በመመርመር ከጊዜ፣ ከጥራትና ከዋጋ አንጻር ግዥው በልዩ ሁኔታ ቢፈጸም የሚያስገኘውን ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጠቀሜታ ግምት ውስጥ በማስገባት የልዩ ፈቃድ ጥያቄው በልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ይወሰናል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# የግዥ ስልቶች

## 47. የግዥ ስልት ዓይነቶች

የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የግዥ ስልቶች በመጠቀም ግዥ ሊፈጽሙ ይችላሉ፡፡

1) በስትራቴጂክ አጋርነት የሚፈጸም ግዥ
2) በማዕቀፍ የሚፈጸም ግዥ፣
3) በጋራ የሚፈጸም ግዥ፣
4) በሊዝ ስምምነት የሚፈጸም ግዥ፣

5) በራስ ኃይል የሚፈጸም ግዥ፣

6) የተርንኪ ግዥ፣

7) በኤሌክትሮኒክ ልውጥ ሀራጅ ጨረታ የሚፈጸም ግዥ፣

## 48. በስትራቴጂክ አጋርነት የሚፈጸም ግዥ

1) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባላቸው የተለየ ባህሪ ምክንያት የተቋቋሙበትን ዓላማ ለማሳካት እና አስተማማኝ የሆነ አቅርቦት እንዲኖር ለማድረግ በቅድመ ብቃት ማረጋገጫ መስፈርትን የሚያሟሉ ድርጅቶችን በአቅራቢነት በመመዝገብ በተወሰነ ጊዜ እነዚህን አቅራቢዎች በመጋበዝ ወይም በቀጥታ ግዥ የሚፈጸምበት የግዥ ስልት ነው፡፡

2) የልማት ድርጅቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሰረት የሚፈጽሙት ግዥ፣

ሀ/ በግንባታ ዘርፍ ላይ የተሰማሩ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ለግንባታ ሥራ አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶችን፣ ዕቃዎች፣ አገልግሎቶችን የማማከር አገልግሎቶች፣ የስራ ተቋራጮችንና ንዑስ ስራ ተቋራጮች፣ ለዲዛይንና ግንባታ ወይም ለተርንኪ ፕሮጀክቶች እና ሌሎች ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን፣

ለ/ በማምረት ዘርፍ የተሰማሩ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ለምርት ስራ የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች፣ መገልገያዎች፣ ግብዓቶችን እና አገልግሎቶችን፣

ሐ/ በንግድና አገልግሎት ዘርፍ የተሰማሩ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተገዝተው ለሚሸጡ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችንና ውጤቶችን፣ መሣሪያዎች፣ መገልገያዎች፣ ምርቶችን ሌሎች ግብዓቶችንና አገልግሎቶችን፣

መ/ በፋይናንስ ዘርፍ የተሰማሩ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ለዘርፉ አገልግሎት የሚሰጡ አቅርቦቶችንና አገልግሎቶችን፣

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን ስልት በመጠቀም ግዥ መፈጸም የሚቻለው የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው፡፡

ሀ/ በዚህ ስልት መፈጸሙ ከጊዜ፣ ከዋጋ እና ከጥራት የተሻለ ጠቀሜታ ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ፣ እና

ለ/ ቀደም ብለው ተለይተው በልማት ድርጅቱ የግዥ ዕቅድ ውስጥ የጸደቁ ወይም አዲስ ፍላጎት በሚኖርበት ወቅት በልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ የተፈቀዱ መሆን አለባቸው፡፡

## 49. አቅራቢዎች የሚመረጡበት ሂደት

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 50 መሰረት ለሚፈጸም የግዥ ስልት የአቅራቢዎች ምዝገባ እና የቅድመ ብቃት ምዘና ስራ የሚመራው በግዥ የስራ ክፍል ወይም በሚመለከታቸው ክፍሎች ይሆናል፡፡

2) የልማት ድርጅቱ ብቃት ያላቸውን አቅራቢዎች በመምረጥ በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ለመመዝገብ ለሁሉም አቅራቢዎች የመወዳደር ዕድል ለመስጠት ግልጽ የሆነ የመወዳደሪያ መስፈርት በማዘጋጀት የግዥውን ዓይነት፣ ባህሪ፣ የአቅራቢዎችን ብዛት መሰረት በማድረግ የገንዘብ ጣሪያ ከግምት ሳይገባ ቢያንስ አንድ ጊዜ በብሔራዊ ወይም በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ በመውጣት ይሆናል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የልማት ድርጅቱ አቅም ያላቸውን ድርጅቶች በመጋበዝ ተወዳዳሪዎች የሚመዘገቡበትን አሰራር በመዘርጋት የቅድመ ብቃት መስፈርቱን የሚያሟሉ ተጨማሪ አቅም ያላቸውን ድርጅቶች ሊመዘግብ ይችላል፡፡

4) አቅራቢዎች የቅድመ ብቃት የመወዳደሪያ ሀሳባቸውን ለማቅረብ በቂ ጊዜ እንዲኖራቸው እንደግዥው ዓይነት ጨረታው በአየር ላይ የሚቆየው ለብሔራዊ ወይም ለዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ ከተቀመጠው ዝቅተኛው ጊዜ ማነስ ለበትም፡፡

5) በቅድመ ብቃት ማረጋገጫው ከተወዳደሩት አቅራቢዎች መካከል የልማት ድርጅቱ ለቅድመ ብቃት መወዳደሪያ የወጣውን መስፈርት የሚያሟሉ በየዘርፋቸው እና የአቅም ደረጃ በቀጣይ ሁለት ዓመት በሚፈጸሙ ግዥዎች ውስጥ ለመሳተፍ በልማት ድርጅቱ አቅራቢዎች ዝርዝር ተመዝግበው ይያዛሉ፡፡

6) የልማት ድርጅቱ ቀድም ሲል የቅድመ ብቃት መስፈርቱን አሟልተው በአቅራቢነት የተመዘገቡትን ጨምሮ ሌሎች አዳዲስ አቅራቢዎችንም ለማሳተፍ በሁለት ዓመት አንድ ጊዜ የቅድመ ብቃት ማስታወቂያ ያወጣል፡፡

7) እንደአስፈላጊነቱ የልማት ድርጅቱ የቅድመ ብቃት መስፈርቱን አሟልተው በልማት ድርጅቱ በአቅራቢነት የተመዘገቡ ድርጅቶችን በቅድመ ብቃት በተወዳደሩበት ወቅት የነበራቸውን አቅም ጠብቀው መቆየታቸውን ለማረጋገጥ በውድድር ወይም በቀጥታ ግዥ ከመፈጸሙ በፊት የድርጅቶችን አቅም እንደገና ሊያረጋግጥ ይችላል፡፡

8) የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ማስታወቂያው ቢያንስ የሚከተሉት መረጃዎች መያዝ አለበት፡፡

ሀ) የግዥ ፈጻሚ የልማት ድርጅቱን ስምና አድራሻ፣

ለ) የሚፈጸመውን ግዥ ዓይነት፣

ሐ) የቅድመ ግምገማ መስፈርቶችን፣

መ) የመወዳደሪያ ሀሳብ የሚቀርብበት ጊዜ፣

ሠ) ሌሎች ለተወዳዳሪዎች ግልጽ መሆን ያለባቸው መረጃዎች፣

## 50. የቅድመ ብቃት ሰነዶች ምዘናና ግምገማ

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 50 መሰረት ለሚፈጸም የግዥ ስልት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች አቅም ያላቸው ድርጅቶችን በአቅራቢነት ለመመዝገብ የቅድመ ብቃት ግምገማ በሚያደርጉበት ወቅት የሚከተሉትን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡፡

ሀ/ በዘርፉ የታደሰ የንግድ ፈቃድ እና ተጫራቹ የውጭ ሀገር ከሆነ በሀገሩ የተሰጠ ህጋዊ ንግድ ፈቃድ መኖሩን፣

ለ/ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ምስክር ወረቀት መኖሩን፣

ሐ/ የማጣቀሻ ዝርዝር እና ደንቦች፣

መ/ የጥራት፣ የጤና እና የደህንነት መረጃዎች፣

ሠ/ እንዳስፈላጊነቱ የተወዳዳሪው የፋይናንስ አቅም፣ የሰው ኃይል፣ የሥራ ልምድ እና ለሥራው የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች፣

ረ/ እንዳስፈላጊነቱ የብቃት ማረጋገጫ ሰነዶች፣ ከአምራች ወይም ከአከፋፋዮች የሚሰጥ ውክልና ወይም የእሽሙር ማህበር መመስረቻ ሰነድ እንዲሁም ሌሎችም አስፈላጊ ሰነዶች ተካተው መቅረባቸውን፣

2) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 1 የተዘረዘሩት ቢኖሩም ከአዲስ አበባ ውጪ ለሚሰሩ ፕሮጀክቶች የመመዘኛ መስፈርቶች በህጋዊ ሰነዶቻቸው ላይ ብቻ ያተኮሩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

3) የልማት ድርጅቱ የአቅራቢዎችን ወቅታዊ ብቃት ለመገምገም በዓመት አንድ ጊዜ የአቅራቢ አፈፃፀም ግምገማ ቅጽ በመጠቀም ይገመገማሉ፡፡

## 51. የግዥ አፈጻጸም ዘዴዎች

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የቅድመ ብቃት መመዘኛ መስፈርት መሠረት በልማት ድርጅቶች የአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የተመዘገቡ አቅራቢዎችን በመጠቀም የቁጥር ገደብ ሳይደረግ ለሁሉም የተመዘገቡ አቅራቢዎችን በመጋበዝ፣ በሁለት ደረጃ ጨረታ፣ በፍላጎት መግለጫ ጨረታ፣ በተገደበ ጨረታ፣ በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ እና በቀጥታ ግዥ ለመፈጸም ለየግዥ ዘዴዎች የተቀመጡትን አሰራሮች ተከትለው ግዥ መፈጸም ይችላሉ፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው ቢኖርም ለልማት ድርጅቱ ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎ ሲታመን በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ያልተመዘገቡ ድርጅቶችም በተገደበ ጨረታ፣በዋጋ ማቅረቢያ እና በቀጥታ ግዥ እንዲሳተፉ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

3) በስትራቴጂክ የግዥ ስልት በቅድመ ብቃት ግምገማው ተወዳድረው በልማት ድርጅቶች የአቅራቢ ዝርዝር ውስጥ የተመዘገቡ ድርጅቶችን በጽሁፍ ወይም ኤሌክትሮኒክ ዘዴ በመጠቀም በመጋበዝ የሚፈጸምበት የግዥ ዘዴ ነው፡፡

4) የሚጋበዙ ተጫራቾች የዋጋ፣ የቴክኒክ ሰነዶችንና ሌሎች የመጫረቻ ሰነዶችን ለማዘጋጀት የሚያስችል እንደግዥው ውስብሰብነት ለዓለም አቀፍ ወይም ብሄራዊ ጨረታ የተቀመጠው አነስተኛ ቀናት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

5) ከግብዣ ዘዴው በስተቀር የገንዘብ ጣሪያው፣ ጨረታ መክፈቻ ስነ-ስርዓት፣ ጨረታ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ፣ የግምገማ ዘዴዎች፣ የድርድር ስርዓቶች፣ የውል አፈጻጸም እና ሌሎች ስነ-ስርዓቶች የብሔራዊ ወይም ዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ የግዥ ሂደትን ተከትሎ የሚከናወን ይሆናል፡፡

## 52. የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ አፈጻጸም

1) በልማት ድርጅቶች በተደጋጋሚ የሚፈለጉና በጥቅል ሊፈጸሙ የሚችሉ በተደጋጋሚ የሚቀርቡ ዕቃዎችና አገልግሎቶችን ከጥቅል ግዥ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ከግምት ውስጥ በማስገባት እስከ 5 (አምስት) ዓመት የሚደርስ የማዕቀፍ ስምምነት ውል በመግባት ግዥ የሚፈጸምበት የግዥ ስልት ነው፡፡
2) በግልጽና በተገደበ ጨረታ የግዥ ዘዴ እንዲሁም ተከታታይነት ያለውን ፍላጎቱን ለማሟላት አግባብነት ያላቸውን ሌሎች የግዥ ዘዴዎችን በመጠቀም የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ ሊፈጽም ይችላል፡፡
3) የልማት ድርጅቱ ለዕቃዎች እና ተያያዥ አገልግሎቶች በማዕቀፍ ስምምነት ግዥ አፈጻጸም ለዚሁ ዓላማ የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ እንዲሁም የማዕቀፍ ስምምነትን መሠረት በማድረግ መፈጸም አለበት፡፡
4) የልማት ድርጅቱ የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ ለመፈጸም የሚከተሉት ተጨማሪ ዝርዝሮች በጨረታ ማስታወቂያ ማውጣት አለበት፡፡

   ሀ/ የማስታወቂያው ጥሪ የተደረገው የማዕቀፍ ግዥ ለመፈፀም እንዲቻል መሆኑን

   ለ/ በማዕቀፍ ስምምነቱ የሚፈፀመው ግዥ አይነት፣ የርክክብ ሁኔታ፣

   ሐ/ የማዕቀፍ ውል ስምምነቱ የሚቆይበት ጊዜ፣

   መ/ በማዕቀፍ ስምምነቱ የሚጠቀሙትን ዘርፎች፣ ቅርንጫፎችና ፕሮጀክቶች ዝርዝር፣

   ሠ/ የማስረከቢያ ቦታ እና እስከተቻለ ጊዜ ግምታዊ የማስረከቢያ ጊዜ፣

5) የልማት ድርጅቱ ለማዕቀፍ ስምምነቱ ውጤታማነት ሲባል እንደ አግባብነቱ በጨረታ ማስታወቂያው ላይ የቅድመ ጨረታ ስብሰባ የሚደረግበትን ቀንና ሰዓት ሊያሳውቅ ይችላል፡፡
6) የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ የጨረታ መቆያ ጊዜ እና ዝርዝር አፈጻጸም በዚህ መመሪያ ለየግዥ ዘዴዎች የተገለጸውን ተከትሎ ይሆናል፡፡

## 53. የማዕቀፍ ስምምነት ውል አፈጻጸም

1) የልማት ድርጅቱ በማዕቀፍ ስምምነት በወጣ ጨረታ አሸናፊ ከሆኑ አቅራቢዎች ጋር የማዕቀፍ ውል ስምምነት መግባት የሚችል ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ ከአንድ በላይ

ከሆኑ ፈቃደኛ ተወዳዳሪዎች ጋር በደረጃቸው ቅደም ተከተል መሠረት ተመሳሳይ የሆነ የማዕቀፍ ስምምነት ውል ሊፈርም ይችላል፡፡

2) በአሸናፊው ዋጋ እንዲያቀርቡ በደረጃቸው ቅደም ተከተል ሌሎች ተጫራቾችን ለውል ስምምነት ሲጋብዝ የሚጋብዛቸውን አቅራቢዎች ቁጥር እና የሚያቀርቡት ድርሻ እንደ ግዥው ሁኔታ ከዚህ በታች በተመለከተው አግባብ መሰረት ይወስናል፡፡

 ሀ/ የሚፈለገው የግዥ መጠን እና የተመረጠው አቅራቢ አቅም ከሚፈለገው አቅርቦት ጋር የማይመጣጠን ከሆነ፣

 ለ/ በገበያው ላይ ያሉ ተመሳሳይ አቅራቢዎች ብዛት ያላቸው ሲሆኑና የግዥ ዕድሉን ለብዙ አቅራቢዎች መስጠት ሲያስፈልግ፣

 ሐ/ የገበያው ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ ተለዋዋጭ በመሆኑ ምክንያት ግዥውን በቀረበው ዋጋ በቶሎ ማጠናቀቅ ሲያስፈልግ፣

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የልማት ድረጅቶች በዚህ አንቀጽ ከአንድ በላይ ከሆኑ ፈቃደኛ ተወዳዳሪዎች ጋር የውል ስምምነት የሚፈጽሙት ከዚህ በታች በተገለጸው መሰረት ይሆናል፡፡

 ሀ/ ከሁለት አቅራቢዎች ጋር የማዕቀፍ ስምምነት ውል መፈጸም አስፈላጊ ነዉ ብሎ ሲያምን ለዋናው አሸናፊ ከጠቅላላው የውሉ መጠን 60% ለሁለተኛዉ አቅራቢ በአሸናፊዉ ዋጋ እንዲያቀርብ ተጠይቆ ፈቃደኛ ከሆነ ከጠቅላላው የውሉ መጠን 40% ይሰጠዋል፡፡

 ለ/ ከሶስት አቅራቢዎች ጋር የማዕቀፍ ስምምነት ውል መፈጸም አስፈላጊ ነዉ ብሎ ሲያምን ለዋናው አሸናፊ ከጠቅላላው የውሉ መጠን 50% ለሁለተኛዉ እና ሶስተኛ አቅራቢዎች በአሸናፊዉ ዋጋ እንዲያቀርቡ ተጠይቀው ፈቃደኛ ከሆኑ ከጠቅላላው የውሉ መጠን ለሁለተኛዉ አቅራቢ 30% እና ለሶስተኛዉ አቅራቢ 20% በቅደም ተከተል ይሰጣቸዋል፡፡

4) የማዕቀፍ ስምምነት የሚፈጽሙት አቅራቢዎች የሚያስይዙት የውል ማስከበሪያ ዋስትና ከጠቅላው ግምታዊ ውል መጠን ላይ የአንድ ዓመቱ የውል መጠን ከ10% ያላነሰ ይሆናል፡፡
5) በማዕቀፍ ስምምነት ግዥ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 105 መሠረት ያሉትን አሰራሮችን ተከትሎ የሚፈጸም ይሆናል፡፡
6) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ከሚከተሉት በአንዱ ምክንያት የማዕቀፍ ስምምነቱን ሊሰርዙ ይችላል፡፡
    ሀ/ የማዕቀፍ ስምምነቱ አቅራቢ በውሉ መሠረት ግዴታውን አለመወጣቱ ሲታወቅ፣
    ለ/ የልማት ድርጅቱ የግዥ ፍላጎት በግልጽና በታወቀ ምክንያት ሲለወጥ፣
    ሐ/ የተደረገው የማዕቀፍ ስምምነት ዋጋ፣ ሌሎች ሁኔታዎች እንዲሁም የገበያው ነባራዊ ሁኔታ ሲታይ የልማት ድርጅቱን ሊጎዳ የሚችል ሰፊ ልዩነት መኖሩ ሲረጋገጥ፣
    መ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 6 (ለ እና ሐ) መሠረት የማዕቀፍ ስምምነት እንዲቋረጥ ሲወሰን፣ የማዕቀፍ ስምምነቱ የሚቋረጥበትን ምክንያት እና ተፈፃሚ የሚሆንበትን የአንድ ወር የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ለማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው ማሳወቅ አለበት፡

## 54. በጋራ የሚፈጸም ግዥ አፈጻጸም

1) ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በጋራ በመሆን አግባብነት ባለው የግዥ ዘዴ በማውጣት የሚፈጸምበት የግዥ ስልት ሲሆን በዚህ አንቀጽ የተመላከቱትን አሰራሮች ተከትሎ የሚፈጸም ይሆናል፡፡
2) ግዥውን በጋራ ለመፈጸም የሚፈልጉት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በመጀመሪያ ሁሉንም ወክሎ ግዥውን ሊፈጽም የሚችለውን የመንግሥት የልማት ድርጅትበመምረጥ የጋራ የስምምነት ሰነድ አዘጋጅተው መፈራረም አለባቸው፡፡
3) ከጋራ ግዥው አሸናፊ ተጫራች ጋር ውል እያንዳንዱ የመንግሥት የልማት ድርጅትበተናጠል መፈጸም የሚችል መሆን አለበት፡፡

4) የጨረታ ሂደቱ ለብሔራዊ ወይም ዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ የተፈቀደውን አካሄድ ተከትሎ ይከናወናል፡፡

5) የጨረታ ማስከበሪያ፣ የውል ማስከበሪያ እና ከውል ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ቀደም ተብለው በጋራ ስምምነቱ ላይ በአጣማሪ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በተስማሙበት አግባብ ይመራል፡፡

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተገለጸው ቢኖርም አሸናፊው ከተለየ በኋላ የልማት ድርጅቶቹ ከአሸናፊው ድርጅት ጋር የተናጠል ውል ስምምነት መግባት ይችላሉ፡፡

## 55. በሊዝ ስምምነት የሚፈፀም ግዥ አፈፃፀም

1) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በሊዝ ስምምነት የሚፈጽሟቸው የኪራይ ውሎች ወጪ ሊቆጥቡ የሚችሉ፣ ተለዋዋጭነት እና የቅርብ ጊዜ ቴክኖሎጂን ጠቀሜታ ሊያስገኙ የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

2) በሊዝ ስምምነት የሚፈጽሟቸው ግዥዎች ንብረቱን በግዥ ከማሟላት፣ ከወጪ ቆጠቢነት፣ ከአሰራር መስፈርትና ከቴክኖሎጂ ዕድገቶች አንጻር ጠቀሜታ እንደሚያስገኝ በግልጽ ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

3) በሊዝ ስምምነት ውድድሩ የሚሳተፉ ተጫራቾችን ብቃት፣ ልምድ፣ የገበያ ዋጋ እና የጨረታ ሂደት በፍትሀዊነት ጠንካራ የቴክኒካል ኮሚቴ በማቋቋም ይገመግማል፡፡

4) የሊዝ ውሉ ጊዜ፣ የሊዝ ክፍያ፣ የጥገና ሥራው በማን እንደሚከናወን፣ የጥገና ኃላፊነቶች፣ የኢንሹራንስ ሽፋን፣ አለመግባባት የሚፈታበት ዘዴን እንዲሁም ውሉ ስለሚቋረጥበት አጠቃላይ ሁኔታ ያካተተ መሆን አለበት፡፡

5) የሊዝ ስምምነት ግዥ አግባብነት ላለው የግዥ ዘዴ የተቀመጡትን የአሰራር ስርዓቶችንና ለእያንዳንዱ የግዥ ዘዴ የተቀመጠውን የገንዘብ ጣሪያ ገደብ ተከትሎ የሚፈጸም ይሆናል፡፡

## 56. በራስ ኃይል የሚከናወን ግዥ አፈፃፀም

በግንባታ እና በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማሩ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ሳይጨምር፤ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የራስ ኃይል በመጠቀም ያለ ጨረታ ሂደት በራሳቸው እስከ ብር 50,000,000.00 (ሃምሳ ሚሊዮን) የሚያወጡ ግንባታን ወይም አገልግሎቶችን

የሚያከናውንበት የግዥ ስልት ሲሆን በዚህ ስልት ግዥ መፈፀም የሚቻለው ከሚከተሉት ሁኔታዎች አንዱ ሲሟላ ነው፡፡

ሀ/ ሊሰሩ የታሰቡት የግንባታ ሥራዎች ወይም ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎቶች ትንንሽና ተበታትነው የሚገኙ ወይም ሩቅ ቦታ ላይ የሚገኙ በመሆናቸው ድርጅቶች በውድድሩ ሊሳተፉ አይችሉም ተብሎ ሲገመት፣

ለ/ በራስ ኃይል በመሰራታቸው ምክንያት በግንባታ ሥራው ወይም ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎቶች ላይ የጥራት ችግር ሊያጋጥም እንደማይችል ሲረጋገጥ፣

ሐ/ አስቸኳይ የግንባታ ስራና እና የጥገና ሥራዎችን የሚሹ ድንገተኛ አደጋዎች ሲከሰቱ፣

መ/ ለስራው ከሚያስፈልገው ግብዓቶች ውጭ የግንባታ ስራውን ወይም ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎቶችን የሚሰራው ባለሙያ ወይም ቡድን በልማት ድርጅቱ የዳይሬክተሮች ቦርድ በተለየ ሁኔታ ካልተፈቀደ በስተቀር በልማት ድርጅቱ ለተለያዩ ስራዎች በተፈቀደው የገንዘብ አከፋፈል ስርዓት መሠረት ይሆናል፡፡

## 57. የተርንኪ ግዥ አፈፃፀም

1) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የአንድ ፕሮጀክት አካል ሆነው ራሳቸውን የቻሉ የተለያዩ ጨረታዎች ሊወጡባቸው የሚችሉ ግዥዎችን አንድ ላይ በማቀናጀት በአንድ ጨረታ መፈፀሙ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ሲታመን የተለያዩ ግዥዎችን በአንድ ላይ በማስተሳሰር የሚፈጸምበት የግዥ ስልት ነው፡፡
2) ከግንባታ ሥራ ጋር የተያያዙ ግዥዎች በተርንኪ ደረጃ ሲፈጽሙ የግንባታ ቁጥጥር ሥራ የልማት ድርጅቱ በሚቀጥረው ወይም ተቋራጩ በሚያቀርበው አማካሪ የሚሰራ ሊሆን ይችላል፡፡
3) በተርንኪ የግዥ ስልት ግዥ ሲፈጽሙ በአዋጁና በዚህ መመሪያ የተፈቀዱ አግባብነት ያላቸውን የግዥ ዘዴዎችን በመጠቀም ይሆናል፡፡
4) ለተርንኪ ግዥ ሲፈጽም ለዚሁ ዓላማ እንዲውል የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡

## 58. የኤሌክትሮኒክ ልውጥ ሀራጅ ጨረታ አፈጻጸም

1) የልማት ድርጅቱ የኤሌክትሮኒክ ዘዴን በመጠቀም የሚጠየቀውን ዝቅተኛ ፍላጎት በማሟላት ብቃት ያላቸው ተወዳዳሪዎች በተቀመጠላቸው የተገደበ ጊዜ ውስጥ አዲስ ዋጋ ወይም የተሻሻለ ዋጋ እያቀረቡ የሚወዳደሩበትና የመጨረሻውን ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበው ተጫራች የጨረታው አሸናፊ ሆኖ የሚመረጥበት የግዥ ስልት ነው፡፡

2) ኤሌክትሮኒክ ልውጥ ሀራጅ ጨረታ የኤሌክትሮኒክ ዘዴ በመጠቀም ለተፈለገው ግዥ ተጫራቾች ዋጋቸውን እየሰጡ የሚወዳደሩበት ዘዴ ነው፡፡

3) የልማት ድርጅቱ የኤሌክትሮኒክ ልውጥ ሀራጅ ጨረታን በመጠቀም ግዥ መፈጸም የሚችለው ከሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ ሲሟላ ነው፡ :

   ሀ) ግልጽ መስፈርት ያለው እና ለገበያ ተብሎ የተዘጋጀ ዕቃ ወይም የአገልግሎት ግዥ፣

   ለ) በገበያ ላይ በቂ አቅራቢ ያለው ዕቃ ወይም የአገልግሎት ግዥ፣ እና

   ሐ) ዋጋ ብቸኛ የማወዳደሪያ መስፈርት ለሆነበት የዕቃ ወይም የአገልግሎት ግዥ ነው፡፡

4) በዚህ የግዥ ስልት የሚፈጸሙ ግዥዎች የገንዘብ መጠን ጣሪያ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 45 ለዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ ከተቀመጠው መብለጥ የለበትም፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

# ለግንባታ ሥራ ግዥ የብቃት መስፈርቶች

## 59. የግንባታ ሥራ አፈፃፀም ምዘና

1) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቋራጮች ከዚህ በፊት በያዟቸው ወይም ባስረከቧቸው ሥራዎች ላይ ያላቸውን የሥራ አፈፃፀም መረጃን እንዲያቀርቡ ማድረግ አለባቸው፡፡

2) እነዚህ መረጃዎች ከሦስተኛ ወገን የሚገኙ ከሆነ የልማት ድርጅቱ በጨረታው ግምገማ ወቅት የተጫራቹን የቀድሞ ሥራዎች በተመለከተ የውል ሰነድን ጨምሮ ሌሎች ሰነዶችን ወይም በአካል በመገኘት ተጨማሪ ማጣራትን ማከናወን እና ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

## 60. የግንባታ ስራ ግዥ አጠቃላይ ልምድ

1) የሚመለከተው የመንግስት ተቋም በሚሰጠው ደረጃ መሠረት ከደረጃ 6 እስከ 10 ካሉት በስተቀር ሌሎች የሀገር ውስጥ ስራ ተቋራጮች በስራ ተቋራጭ፣ በጥምረት፣ በእሽሙር እና በሽርክና ማህበር ወይም በንዑስ ስራ ተቋራጭነት በየዘርፉ ቢያንስ የ2 (ሁለት) ዓመት ልምድ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

2) የውጪ ሀገር ስራ ተቋራጮች በስራ ተቋራጭ፣ በሽርክና ማህበር ወይም በንዑስ ስራ ተቋራጭ ደረጃ በዘርፉ ቢያንስ የ4 (አራት) ዓመት ልምድ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

## 61. ግንባታ ሥራ ግዥ ተዛማጅ የስራ ልምድ

1) የሀገር ውስጥ ስራ ተቋራጮች ባለፉት አስር ዓመታት ውስጥ ሊሰራ ከታሰበው የግንባታ ስራ ጋር በተመሳሳይ ቢያንስ አንድ የግንባታ ስራ በስራ ተቋራጭነት፣ በሽርክና ማህበር አባልነት ወይም በንዑስ ስራ ተቋራጭነት የሰሩና ቢያንስ የስራውን ሰባ በመቶ (70%) በአስተማማኝ እና አጥጋቢ ሁኔታ ያጠናቀቁ መሆን አለባቸው፡፡

2) የግንባታ ሥራው ግምታዊ ዋጋ ከብር ሦስት ቢሊዮን በታች ሲሆንና ስራ ተቋራጮች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተጠየቀውን የተዛማጅ ስራ ልምድ ዋጋ በአንድ ኘሮጀክት በሰሩት የስራ ልምድ ብቻ ማሟላት ካልቻሉ በአጥጋቢ እና በአስተማማኝ ሁኔታ የተጠናቀቁና ሊሰራ ከተፈለገው ስራ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ሦስት ፕሮጀክቶች ዋጋ ድምር በልምድነት ሊያዝላቸው ይችላል፡፡ ሆኖም የሶስቱ ፕሮጀክቶች የተናጠል ዋጋ ማሟላት ከሚገባቸው የስራ ልምድ ዋጋ ከአንድ ሶስተኛ (1/3) በታች መሆን አይኖርበትም፡፡

3) የግንባታ ስራው ግምት ከብር ሦስት ቢሊዮን በላይ ሲሆንና ስራ ተቋራጮች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተጠየቀውን የተዛማጅ ስራ ልምድ ዋጋ በአንድ ኘሮጀክት በሰሩት የስራ ልምድ ብቻ ማሟላት ካልቻሉ በአጥጋቢ እና በአስተማማኝ ሁኔታ የተጠናቀቁ አራት ፕሮጀክቶች ድምር በልምድነት ሊያዝላቸው ይችላል፡፡

ሆኖም የአራቱ የተናጠል ዋጋ ማሟላት ከሚገባቸው የስራ ልምድ ዋጋ ከሩብ (1/4) በታች መሆን አይኖርበትም።

4) የውጭ ሀገር ሥራ ተቋራጮች ባለፉት አስር ዓመታት ውስጥ በጨረታ ሊሰራ ከታሰበው የግንባታ ስራ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ቢያንስ ሁለት የግንባታ ሥራዎችን በሥራ ተቋራጭነት፣በሽርክና ማህበር አባልነት ወይም በንዑስ ሥራ ተቋራጭነት የሰሩ እና ቢያንስ የሥራውን ሰማኒያ በመቶ (80%) በአስተማማኝ እና በአጥጋቢ ሁኔታ ያጠናቀቁ መሆን አለባቸው።

5) ተቋራጩ ያቀረበው የሥራ ልምድ በንዑስ ሥራ ተቋራጭነት ወይም በሽርክና ማህበር አባልነት የተገኘ ሲሆን፣በንዑስ የሥራ ተቋራጭነት የሰራው መጠን ብቻ ወይም በሽርክና ማህበሩ ካለው ድርሻ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ልምድ ብቻ በስራ ልምድነት እንዲያዝለት ይደረጋል።

6) በዚህ አንቀጽ መሠረት የተደነገገው የተዛማጅ የሥራ ልምድ መስፈርቶች ከደረጃ 6 እስከ 10 ላሉት ሥራ ተቋራጮች ተፈፃሚ አይሆኑም።

7) ለጨረታ ግምገማ ዓላማ የሥራ ተቋራጩ በሥራ ልምድነት እንዲያዝለት በሚያቀርበው የግንባታ ዋጋ ላይ ማስተካከያ የሚደረገው፣ ጨረታ ከሚቀርብበት የመጨረሻ ቀን ከሃያ ስምንት (28) ቀናት በፊት የነበረውን የምንዛሪ ምጣኔን ውሉ በተፈረመበት ጊዜ በነበረው የምንዛሪ ምጣኔ በማካፈል ከተሰላ በኋላ በሚገኘው ውጤት በማባዛት ነው።ማስተካከያው የሚሰላው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚሰጠውን የውጭ ሀገር ገንዘብ መሸጫ ዋጋ መረጃ መሠረት በማድረግ ይሆናል።

8) ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም፡

   ሀ/ "በአጥጋቢ ሁኔታ የተጠናቀቀ" ማለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 4 መሠረት የሥራው ሰባ በመቶ (70%) ወይም ሰማኒያ በመቶ (80%) እና ከዚያ በላይ የተጠናቀቀ የግንባታ ሥራ ፕሮጀክት ነው።

   ለ/ "በአስተማማኝ ሁኔታ የተጠናቀቀ" ማለት በሥራ ተቋራጩ የተሰራው ሰባ በመቶ (70% ) እና ከዚያ በላይ ሥራ በተቀመጠለት የጊዜ ሰሌዳና የጊዜ ማራዘሚያ እንዲሁም በተረጋገጠ የክፍያ ሰነድ በሚፈለገው የጥራት ደረጃ ለመሰራቱ ከአሰሪ የልማት ድርጅቱ የተሰጠ የማረጋገጫ ሰርተፊኬት ወይም የሥራ ልምድ ማስረጃ የቀረበበት የግንባታ ስራ ፕሮጀክት ነው፡

## 62. የግንባታ ስራ ግዥ የፋይናንስ አቋም

1) የስራ ተቋራጮች ቢያንስ ያለፉት አራት (4) ዓመት የፋይናንስ አቋማቸውን የሚያሳይ በተመሰከረለት ኦዲተር የተረጋገጠ የፋይናንስ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም የሀገር ውስጥ ስራ ተቋራጭ ከተመሰረተ ከአራት ዓመት በታች ከሆነው የሚያቀርበው የፋይናንስ ሪፖርት ከንግድ ምዝገባ ሰርተፊኬት ወይም ከንግድ ሥራ ፈቃዱ ጋር የሚናበብ ከሆነ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡
3) በስራ ተቋራጮቹ የሚቀርበው የፋይናንስ ሪፖርት ከሚመለከተው ግብር ሰብሳቢ መ/ቤት ወይም የሂሳብ አያያዝ እና ኦዲት ቦርድ ከሚገኝ ሪከርድ ጋር ተመሳክሮ ትክክለኛነቱ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

## 63. የግንባታ ስራ ግዥ ዓመታዊ የተርንኦቨር መጠን

1) የሀገር ውስጥ ስራ ተቋራጮችን በተመለከተ ለጨረታ ግምገማ ዓላማ የሚወስደው በግንባታ ላይ ካለና ከተጠናቀቀ የግንባታ ስራ ላይ የተሰበሰበ ክፍያ ዓመታዊ ተርንኦቨር መካከል ተቋራጩ ባለፉት አምስት ዓመት ውስጥ ካስመዘገበው የግንባታ ስራ ዓመታዊ ተርንኦቨር የተሻለውን በመምረጥ ሆኖ፣የስራ ተቋራጮች እንዲያሟሉ የሚጠየቁት የተርንኦቨር መጠን የሚሰላው ሊሰራ የታሰበውን የግንባታ ስራ ግምታዊ ዋጋ፣ ቀናትን ወደ ሚቀጥለው ሙሉ ወር በማጠጋጋት ግንባታው ይጠናቀቃል ተብሎ በሚገመትበት ወርሃዊ ጊዜ በማካፈልና ውጤቱን በ0.6 በማባዛት ነው፡፡
2) ለውጭ ሀገር የስራ ተቋራጮች እና በሽርክና ማህበር ደረጃ ጥምረት ፈጥረው የሚወዳደሩት ስራ ተቋራጮች የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር በሚሆኑበት ጊዜ የማባዣ ቁጥር እንደቅደም ተከተላቸው 2 እና 1.2 ይሆናል፡፡
3) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 አፈፃፀም፤
   ሀ/ የሀገር ውስጥ ስራ ተቋራጭ ተፈላጊ ዓመታዊ ተርን ኦቨር = ሊሰራ የታሰበው የግንባታ ሥራ ግምታዊ ዋጋ ሲካፈል ግንባታው ይጠናቀቃል ተብሎ የሚገመተው ወር ሲባዛ 12 ሲባዛ 0.6፣
   ለ/ ለውጭ ሀገር ስራ ተቋራጭ ተፈላጊ ዓመታዊ ተርን ኦቨር = ሊሰራ የታሰበው የግንባታ ሥራ ግምታዊ ዋጋ ሲካፈል ግንባታው ይጠናቀቃል ተብሎ የሚገመተው ወር ሲባዛ 12 ሲባዛ 2፣

ሐ/ በሽርክና ማህበር ደረጃ ጥምረት ፈጥረው የሚወዳደሩት ስራ ተቋራጮች የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር በሚሆኑበት ጊዜ ተፈላጊ ዓመታዊ ተርን ኦቨር= ሊሰራ የታሰበው የግንባታ ሥራ ግምታዊ ዋጋ ሲካፈል ግንባታው ይጠናቀቃል ተብሎ የሚገመተው ወር ሲባዛ 12 ሲባዛ 1.2፣

4) በጨረታ ግምገማ ጊዜ ለሚደረግ ማስተካከያ ዓላማ ለተርንኦቨር ስሌት የሚወሰደው ስራ ተቋራጩ ያቀረበው ዓመታዊ የግንባታ ስራ ተርንኦቨር መጠን፣ ጨረታ ከሚቀርብበት የመጨረሻ ቀን 28 ቀን በፊት የነበረውን የምንዛሪ ምጣኔን በእያንዳንዱ በጀት ዓመት የመጨረሻ ቀን ላይ ባለው የምንዛሪ ምጣኔ በማካፈል ነው፡፡ ማስተካከያው የሚሰላው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ የሚሰጠውን የውጭ ሀገር ገንዘብ መሸጫ ዋጋ መረጃ መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡

5) ስራ ተቋራጮቹ በሽርክና ማህበር ደረጃ ጥምረት የፈጠሩ ከሆኑ እያንዳንዳቸው የሽርክና ማህበሩ አጋር ድርጅቶች ማሟላት የሚገባቸው የተርንኦቨር መጠን ከተጠየቀው ከሃያ አምስት በመቶ (25%) እና የዋናው ስራ ተቋራጭ ደግሞ ከአርባ በመቶ (40%) ማነስ የለበትም፡፡

6) የምህንድስና ዋጋ ግምት እና የግንባታው ስራ የሚፈጀውን ጊዜ የመወሰን ኃላፊነት የተሰጠው ማንኛውም አካል የምህንድስና ዋጋውን ወይም ስራው የሚፈጀውን ጊዜ ከፍ ወይም ዝቅ በማድረግ ያዘጋጀ ስለመሆኑ ማረጋገጫ መስጠትና ግምቱም በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ መገምገምና በልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ተቀባይነት ያገኘ መሆን ይኖርበታል፡፡

## 64. የባለሙያዎች የትምህርት ዝግጅትና ብቃት

1) የሥራ ተቋራጮች የጨረታ ሰነዱ ላይ በሚገለፀው መሠረት እንደ ግንባታ ስራው ባህሪ ብቻ ለስራው የሚያስፈልጉ ብቁ ባለሙያዎችን በሚፈለገው መጠን እና ስብጥር እንደሚያቀርቡ ማሳየትና ባለሙያዎቹም ለስራው በሚያስፈልጉበት ጊዜ ሁሉ በተመደቡበት ቦታ ላይ ሊገኙ የሚችሉ መሆኑን የሚያመለክት አስተማማኝ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለፁት ባለሙያዎች የግንባታ ስራ ተቋራጩ ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ሰራተኞች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

3) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ከሥራ ተቋራጮች የቀረበላቸው በግንባታ ስራ ላይ የሚሰማሩ ባለሙያዎች የትምህርት ዝግጅትና ብቃትን የተመለከተው ማስረጃ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተገለፀው መሠረት መሆኑን በግንባታ ጊዜም ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

## 65. የግንባታ ስራ መሳሪያ ማሟላት

1) በስራ ተቋራጮች የጨረታ ሰነዱ ላይ በሚገለፀው መሠረት እንደ ግንባታ ስራው ባህሪ ለስራው የሚያስፈልጉ መሳሪያዎችን ዓይነትና መጠን በሚፈለጉበት ጊዜ ሁሉ ማቅረብ እንደሚችሉ የሚያሳይ ማረጋገጫ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

2) የሚቀርቡት መሳሪያዎችም በስራ ተቋራጮች ባለቤትነት ስር የሚገኙ ወይም በኪራይ የተገኙ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

## 66. ከአንድ በላይ በሆኑ የግንባታ ስራዎች ላይ የልምድ አያያዝ

1) በአንድ የጨረታ ማስታወቂያ የሚወጡ ንዑስ የግንባታ ስራዎች ቁጥር ከአንድ በላይ በሚሆንበት ጊዜ ማንኛውም ተጫራች መሳተፍ የሚፈልግባቸውን ንዑስ የግንባታ ስራዎች ዓመታዊ ተርንኦቨር፣የገንዘብ አቅምና ተዛማጅ የስራ ልምድ መስፈርት በድምር ማሟላት አለበት፡፡

2) አንድ ተጫራች ለእያንዳንዱ ንዑስ የግንባታ ስራ የተጠየቀውን መስፈርት አሟልቶ ነገር ግን ለተሳተፈባቸው ንዑስ የግንባታ ስራዎች በድምር የሚጠየቀውን መስፈርት በማያሟላበት ጊዜ ምንም እንኳን በተናጠል ሲታይ ለንዑስ የግንባታ ስራዎቹ የተሻለ ዋጋ ቢያቀርብም ውል ሊፈጽም የሚችለው መስፈርቶቹን ማሟላት በቻለበት ልክ ብቻ ነው፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የልማት ድርጅቱ የተሻለ ጠቀሜታ ከማስገኘት አንፃር ሥራ ተቋራጩ በሰጠው ዋጋ ውል የሚገባበትን ንዑስ የግንባታ ስራ ወይም የግንባታ ስራዎች የመወሰን ስልጣን የልማት ድርጅቱ ይሆናል፡፡

## 67. ለህንፃ ግንባታ ስራ የሚጠየቅ ዝቅተኛ መስፈርት

1) ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም የህንፃ ደረጃ የሚከተሉትን ይይዛል፤

   ሀ) **ደረጃ "ሀ" " አነስተኛ ህንጻ** (Low-Rise Building)" ማለት ምንም ዓይነት አሳንሰር ወይም አሳንሰርን የሚተካ ከምድር ወደ ፎቅ እንዲሁም ከፎቅ ወደ ምድር የሚያመላልስ መሳሪያ የሌለው ሆኖ ከምድር በላይ ከአምስት ያነሱ ፎቆች ያለው ነው፡፡

   ለ) **ደረጃ "ለ" "መካከለኛ ህንጻ** (Mid-Rise Building)"ማለት ከምድር በላይ ቢያንስ አምስት ፎቆች ያለው ሆኖ ከአሥራ አምስት ፎቆች በላይ የሌለው ነው፡፡

   ሐ) **ደረጃ "ሐ" "ከፍተኛህንጻ** (High-Rise Building)" ማለት ከምድር በላይ ቢያንስ አሥራ አምስት ፎቆች ያለው ሆኖ ከአርባ አምስት ፎቆች በላይ የሌለው ነው፡፡

   መ) **ደረጃ "መ" "በጣም ከፍተኛ ህንጻ** (Mega-High Rise Building)" ማለት ከምድር በላይ ቢያንስ አርባ አምስት እና ከዚያ በላይ ፎቆች ያለው ነው፡፡

2) ለህንፃ ግንባታ ስራ የሚወዳደረው የሀገር ውስጥ ስራ ተቋራጭ ሲሆን የሚጠየቀው ዝቅተኛ መስፈርት ሊሰራ ከታሰበው የህንፃ ስራ በአንድ ደረጃ ዝቅ ያለ መሆን አለበት፡፡

3) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 አፈፃፀም ሊሰራ ከታሰበው የህንፃ ስራ በአንድ ደረጃ ዝቅ ያለ ማለት በደረጃ "ሀ" ስራ ልምድ ያለው የሀገር ውስጥ ስራ ተቋራጭ በደረጃ "ለ" ለመካከለኛ ህንፃ ግንባታ ስራ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡ በደረጃ "ለ" ስራ ልምድ ያለው የሀገር ውስጥ ስራ ተቋራጭ ለደረጃ "ሐ" ግንባታ ስራ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡በደረጃ "ሐ" ስራ ልምድ ያለው የሀገር ውስጥ ስራ ተቋራጭ ለደረጃ "መ" ግንባታ ስራ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

4) ለህንፃ ግንባታ ስራ የሚወዳደረው የውጭ ሀገር ስራ ተቋራጭ ሲሆን ሊሰራ ከታሰበ የህንፃ ደረጃ ጋር እኩል የሆነ ወይም የበለጠ የህንፃ ስራ ልምድ ሊኖረው ይገባል፡፡ ለምሳሌ ለደረጃ "መ" ግንባታ ለመስራት የሚወዳደር የውጭ ሀገር ስራ ተቋራጭ ያለው ልምድ በማናቸውም ሁኔታ ከምድር በላይ አርባ አምስት /45/ ፎቆች ያሉትን ህንፃ ከመገንባት ያነስ ልምድ ሊሆን አይገባም፡፡

## 68. ለድልድይ ግንባታ ስራ የሚጠየቅ ዝቅተኛ መስፈርት

1) ለድልድይ ግንባታ ስራ የሚወዳደረው የአገር ውስጥ ስራ ተቋራጭ ሲሆን የሚጠየቀው ዝቅተኛ መስፈርት ሊሰራ ከታሰበው የድልድይ ስራ በአንድ ደረጃ ዝቅ ያለ መሆን አለበት፡፡ለድልድይ ግንባታ ስራ የሚወዳደረው የአገር ውስጥ ስራ ተቋራጭ ሲሆን፣

   ሀ/ በህንፃ ፕሮጀክቶች ስራ ልምድ ያለው የአገር ውስጥ ስራ ተቋራጭ በድልድይ ስራ አስተማማኝ የስራ ልምድ ያለው ባለሙያ ያለው መሆኑ እና የመሬት ውስጥ ስራ ልምድ ያለው መሆኑ ተረጋግጦ አጭር ርዝመት ያለው ድልድይ ግንባታ ስራ ላይ ለመወዳደር ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

   ለ/ አጭር ርዝመት ባለው ድልድይ ግንባታ ስራ ልምድ ያለው የአገር ውስጥ ስራ ተቋራጭ መካከለኛ ርዝመት ያለው ድልድይ ግንባታ ስራ ላይ ለመወዳደር ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

   ሐ/ መካከለኛ ርዝመት ባለው ድልድይ ግንባታ ስራ ልምድ ያለው የአገር ውስጥ ስራ ተቋራጭ ረጅም ርዝመት ያለው ድልድይ ግንባታ ስራ ላይ ለመወዳደር ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

2) ለድልድይ ግንባታ ስራ የሚወዳደረው የውጭ አገር ስራ ተቋራጭ ሲሆን የውጭ አገር ስራ ተቋራጭ የሚጠየቀው የድልድይ ግንባታ ስራ ልምድ ሊሰራ ከታሰበው የድልድይ ስራ ያነሰ ሊሆን አይገባም፡፡

3) ግዥ ፈፃሚው መስሪያ ቤት ለውጭ አገር ስራ ተቋራጭ ከሚጠየቀው ዝቅተኛ መስፈርት በተጨማሪ በተወሰነ የድልድይ ዓይነት የድልድይ ግንባታ ስራ ልምድ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

4) ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም

   ሀ/ "አጭር ርዝመት ያለው ድልድይ" ማለት ለተሽከርካሪዎች ወይም ለሌሎች የመጓጓዣ ዘዴዎች የሚያገለግል ሆኖ ርዝመቱ ከ25 (ሃያ አምስት) ሜትር ያነሰ ድልድይ ነው፡፡

   ለ/ "መካከለኛ ርዝመት ያለው ድልድይ" ማለት ለተሽከርካሪዎች ወይም ለሌሎች የመጓጓዣ ዘዴዎች የሚያገለግል ሆኖ ርዝመቱ ከ25 (ሃያ አምስት) ሜትር የማያንስ እና ከ50 (ሃምሳ) ሜትር የማይበልጥ ድልድይ ነው፡፡

   ሐ/ "ረጅም ርዝመት ያለው ድልድይ" ማለት ለተሽከርካሪዎች ወይም ለሌሎች የመጓጓዣ ዘዴዎች የሚያገለግል ሆኖ ርዝመቱ ቢያንስ 50(ሃምሳ) እና ከዚያ በላይ የሆነ ድልድይ ነው፡፡

## 69. የመንገድ ኘሮጀክቶች አመዳደብ በንጣፍ ዓይነት

የመንገድ ኘሮጀክቶች ግዥ ሲፈፀም የሚከተሉትን አመዳደብ መሰረት በማድረግ መሆን አለበት፡፡

1) አስፋልት ኮንክሪት (Asphalt Concrete Pavement)፣
2) የድርብ እና ባለሶስት አስፋልት ንጣፍ (Double and Triple Surface Treatment)፤ ወይም ደረቅ/አርማታ ንጣፍ (Rigid Pavement)፣
3) የጠጠር መንገድ (Aggregate Surfacing/Gravel)፣
4) ከባድ ጥገና እና የመንገድ መልሶ ግንባታ (heavy maintenance and Road rehabilitation)፣እና
5) መደበኛና ወቅታዊ ጥገና (Routine and Periodic Maintenance)፡፡

## 70. ለመንገድ ኘሮጀክቶች የግንባታ ስራ የሚጠየቅ ዝቅተኛ መስፈርት

1) ለመንገድ ኘሮጀክቶች የግንባታ ስራ የሚወዳደረው የአገር ውስጥ ስራ ተቋራጭ ሲሆን፣ ሊሰራ ከታሰበው የመንገድ ስራ በአንድ ደረጃ ዝቅ ያለ ልምድ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም፤

ሀ/ በአዲስ የጠጠር መንገድ ግንባታ ስራ ወይም በመንገድ መልሶ ግንባታ ወይም በከባድ የአስፋልት መንገድ ጥገና (Heavy Maintainance) የተገኘ የመንገድ ግንባታ ስራ ልምድ በአስፋልት (asphalt surfacing) ለመወዳደር ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

ለ/ ማንኛውም የአስፋልት ስራ ወይም እንደ አየር መንገድ ያሉ ሌሎች ተመሳሳይ የመንገድ ግንባታ ስራዎች ወይም በመንገድ ደረጃዎች ማሻሻያ ፕሮጀክቶች ላይ የተገኘ ልምድ ለአስፋልት (asphalt surfacing) ፕሮጀክቶች ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

ሐ/ መደበኛና ወቅታዊ ጥገና (Routine and Periodic Maintenance) የተገኘ የመንገድ ግንባታ ስራ ልምድ የጠጠር መንገድ እና የከባድ መንገድ ጥገና (Heavy Maintainance) ግንባታ ለመወዳደር ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

መ/ በመደበኛና ወቅታዊ ጥገና (Routine and Periodic Maintenance) ግንባታ ለመወዳደር ገዥው መስሪያ ቤት ሌሎች አነስተኛ ግንባታዎችን በመስፈርትነት ሊወስድ ይችላል፡፡

2) ለመንገድ ኘሮጀክቶች የግንባታ ስራ የሚወዳደረው የውጭ አገር ስራ ተቋራጭ ሲሆን፣ የውጭ አገር ስራ ተቋራጭ ሊሰራ ከታሰበው የመንገድ ኘሮጀክት ጋር ተመሳሳይ የሆነ ወይም የበለጠ የመንገድ ስራ ግንባታ ልምድ ሊኖረው ይገባል፡፡ እንዲሁም የሚጠየቀው የገንዘብ መጠን በማናቸውም ሁኔታ ሊሰራ በታሰበው የመንገድ ስራ ከተገመተው የገንዘብ መጠን ሊያንስ አይገባም፡፡

71. **ለግድብ ግንባታ ሥራ እና ለመስኖ ግንባታ ሥራ የሚጠየቅ ዝቅተኛ መስፈርት**

1) ለግድብ ግንባታ ሥራ የሚወዳደረው የአገር ውስጥ ስራ ተቋራጭ ሲሆን፣ የሚጠየቀው ዝቅተኛ መስፈርት ሊሰራ ከታሰበው የግድብ ስራ በአንድ ደረጃ ዝቅ ያለ ልምድ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡ በዚህ መሰረት በአነስተኛ የግድብ ሥራ ልምድ ያለው የአገር ውስጥ ሥራ ተቋራጭ ለመካከለኛ ግድብ ግንባታ ሥራ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

2) ለመስኖ ግንባታ ሥራ የሚወዳደረው የአገር ውስጥ ስራ ተቋራጭ ሲሆን፣ የሚጠየቀው ዝቅተኛ መስፈርት ሊሰራ ከታሰበው የመስኖ ስራ በአንድ ደረጃ ዝቅ ያለ ልምድ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡ በዚህ መሰረት በአነስተኛ የመስኖ ዘዴዎች የሥራ ልምድ ያለው የአገር ውስጥ ሥራ ተቋራጭ የመስኖ ዘዴዎች ሥራ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

3) ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም፡

ሀ/ "ትላልቅ ግድብ" ማለት ከ10 ሄክታር እና ከዚያ በላይ የሆነ የውኃ ማጠራቀሚያ ቦታ ያላቸው ግድቦች ናቸው፡፡

ለ/ "መካከለኛ ግድብ" ማለት ከ3 እስከ 10 ሄክታር የውኃ ማጠራቀሚያ ቦታ ያላቸው ግድቦች ናቸው፡፡

ሐ/ "አነስተኛ ግድብ" ማለት ከ 3 ሄክታር በታች የሆኑ የውኃ ማጠራቀሚያ ቦታ ያላቸው ግድቦች ናቸው፡፡

መ/ "አነስተኛ መስኖ" ማለት ከ200 ሄክታር በታች ቋሚ ወይም ሊሻሻሉ የሚችሉ የውሃ መቆጣጠርያ እና ማስራጫ የመሰረተ ልማት አውታሮች ያሏቸው የመስኖ ሥራዎች ናቸው፡፡

ሠ/ "መካከለኛ መስኖ" ማለት ከ200 እስከ 3,000 ሄክታር ቋሚ ወይም ሊሻሻሉ የሚችሉ የውሃ መቆጣጠርያ እና ማሰራጫ የመሰረተ ልማት አውታሮች ያሏቸው የመስኖ ሥራዎች ናቸው፡፡

ረ/ "መካከለኛ መስኖ" ማለት ከ3,000 ሄክታር በላይ ቋሚ ወይም ሊሻሻሉ የሚችሉ የውሃ መቆጣጠርያ እና ማሰራጫ የመሰረተ ልማት አውታሮች ያሏቸው የመስኖ ሥራዎች ናቸው፡፡

## ምዕራፍ ሰባት

## የጨረታ ሥነ ሥርዓት

### 72. የጨረታ ጥሪ ማስታወቂያ

1) የጨረታ ጥሪው በቂ ቁጥር ያላቸው ተወዳዳሪዎች በጨረታው እንዲሳተፉ ለማድረግ ሰፊ ሽፋን ባለው ጋዜጣ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ እና እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች የመገናኛ ዘዴዎች ቢያንስ አንድ ጊዜ ይፋ መሆን አለበት፡፡

2) የጨረታው ጥሪ ማስታወቂያ ቢያንስ የሚከተሉትን ፍሬ ነገሮች ሊይዝ ይገባል፡-

ሀ/ የጨረታውን ማስታወቂያ ይፋ ያደረገው የመንግሥት የልማት ድርጅትስምና የተሟላ አድራሻ፣

ለ/ የሚቀርበውን ዕቃ ወይም አገልግሎት፣ ዓይነት፣ ብዛት እና ርክክቡ የሚፈፀምበትን ቦታ ወይም የግንባታ ሥራውን ዓይነት እና የሚከናወንበትን ቦታ ወይም የምክር አገልግሎቱን ዓይነት እና የሚካሄድበትን ቦታ፣

ሐ/ የግዥ ዘዴውንና የጨረታ መለያ ቁጥር፣

መ/ በጨረታው መሳተፍ የሚችሉ ተወዳዳሪዎች ሊያሟሉ የሚገባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች፣

ሠ/ የጨረታ ሰነዱን ለማግኘት የሚከፈል ዋጋ እና ሰነዱን የሚያገኙበት ሁኔታ፣

ረ/ የመጫረቻ ሰነዱ የመጨረሻ ማስረከቢያ እና የሚከፈትበትን ቀንና ሰዓት፣

ሰ/ ተጫራቾች ወይም ወኪሎቻቸው በጨረታው አከፋፈት ላይ መገኘት የሚችሉ መሆኑን የሚገልጽ መግለጫ፣

ሸ/ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና መጠን፣

ቀ/ ለተጫራቾች መገለጽ እንዳለባቸው በልማት ድርጅቱ የታመነባቸው ሌሎች ጉዳዮች፣

በ/ የልማት ድርጅቱ ጨረታውን በከፊል ወይም በሙሉ የመሰረዝ መብት ያለው መሆኑን፣

3) የጨረታው ጥሪ የጨረታ ሰነዱ በተዘጋጀበት መሠረት ጨረታው በሚካሄድበት ቋንቋ መዘጋጀት ይችላል፡፡

## 73. የጨረታ ሰነድ

1) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በባለስልጣኑ የተዘጋጀውን መደበኛ የጨረታ ሠነድ መነሻ በማደረግ ወይም የራሱን የጨረታ ሠነድ በማዘጋጀት መጠቀም የሚችል ሲሆን የሚዘጋጀው የጨረታ ሠነድ በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩትን ያካተተ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

2) የጨረታ ሰነዱ በጥቅል ድምር የሚከፈል፣ በነጠላ ዋጋዎች የሚከፈል፣ በወጪ ላይ ተደማሪ ሆኖ በሚከፈልና ከሌሎች የተመረጠውን የውል አይነት በግልፅ ማስቀመጥና ለዚህ ተስማሚ የሆኑ የውል ድንጋጌዎችን የያዘ መሆን አለበት፡፡

3) የጨረታ ሰነዱ ጨረታው ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ጨረታው ማቅረቢያ የመጨረሻ ቀንና ሰዓት ድረስ በጨረታ ማስታወቂያው በተገለጸወው መሠረት ተወዳዳሪዎች ዝግጁ መሆን አለበት፡፡

4) የጨረታ ሠነዱ ለተጫራቾች አየር ላይ ከመውጣቱ በፊት በሚመለከተው የልማት ድርጅቱ አካል ሊጸድቅ ይችላል፡፡

5) የልማት ድርጅቱ እንደአስፈላጊነቱ ለጨረታ ሰነዱ ተመጣጣኝ ክፍያ ሊጠይቅ ይችላል:: ሆኖም የሚጠየቀው የክፍያ መጠን ተወዳዳሪዎችን ተሳትፎ የሚገድብ መሆን የለበትም፡፡

## 74. የጨረታ ዝርዝር መረጃ

1) የልማት ድርጅቱ የጨረታ ሠነዶች አንዱ ክፍል ሆኖ የሚዘጋጀውን የተጫራቾች መመሪያ እና የዚሁ አካል የሆነውን የጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ የጨረታ ሰነዱ አካል ማድረግ አለባቸው፡፡

2) በጨረታ ሰነድ የተጫራቾች መመሪያ ላይ ማሻሻያ ማድረግ የማይቻል ቢሆንም በተጫራቾች መመሪያ ላይ የሚደረጉት ለውጦች የሚመላከቱት የጨረታ ዝርዝር መረጃ ሰንጠረዥ ላይ ይሆናል፡፡

3) የጨረታ ዝርዝር መረጃ ሰንጠረዥ የሚከተሉትን ዋና ዋና ሁኔታዎች ያካተተ መሆን አለበት፡-

ሀ/ የሚገዛውን ዕቃ ወይም የግንባታ ስራ፣ የምክር እና ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎቶች አጠቃላይ መግለጫ፣ የልማት ድርጅቱን ሙሉ ስምና አድራሻ እንዲሁም የግዥውን የበጀት ምንጭ፣

ለ/ በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ የሀገር ውስጥ ተጫራቾች የግብር ክፍያ ምስክር ወረቀት፣ የታደሰ ንግድ ፈቃድ እና ሌሎች በልማት ድርጅቱ አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን ደጋፊ ሰነዶች ስለሚቀርቡበት ሁኔታ፣

ሐ/ የውጭ ሀገር ተጫራቾች እንደአግባብነቱ በተቋቋሙበት ሀገር የተሰጣቸውን የኩባንያ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ወይም ፈቃድ ማቅረብ እንዳለባቸው መጠቀሱን፣

መ/ በጨረታ ሰነዱ ግልፅ ያልሆኑ ጉዳዮችን አስመልክቶ ማብራሪያ የሚጠየቅበትን አድራሻና ጊዜ፣

ሠ/ ተጫራች የሚያቀርቡት የመጫረቻ ሰነድ ይዘት፣ ቋንቋ፣ በጨረታ ሰነዱ ውስጥ የሚገለጹ እና በተጨማሪነት የሚያስፈልጉ ማስረጃዎች እና ቅፆች ዓይነት እና ብዛት፣

ረ/ የመጫረቻ ሰነድ ማስረከቢያ ጊዜ የሚያበቃበትን እና ጨረታው የሚከፈትበትን ቀንና ሰዓት፣

ሰ/ ጨረታው ከተዘጋ በኋላ የሚቀርብ የመጫረቻ ሰነድ ተቀባይነት እንደማይኖረው የሚገልፅ መግለጫ፣

ሸ/ ተጫራቾች የማጭበርበር ድርጊት እና ሙስና በሚመለከት በኢትዮጵያ ህጎች የተደነገገውን የሚያከብር መሆኑን በማረጋገጥ ከጨረታ ሰነዱ ጋር ተያይዞ

የሚገኘውን ሙስና ላለመፈጸም ቃል የሚገባበትን ቅጽና ሌሎች በተጫራቾች ተሞልተው እንዲቀርቡ መደረግ አለበት፡፡

ቀ/ የዕቃዎቹ ናሙናዎች በተጫራቾች እንዲቀርቡ የሚያስፈልጉ ከሆነ ተፈላጊዎቹ ናሙናዎች የሚቀርቡበትንና እንደአስፈላጊነቱ በተጫራቾች የሚቀርብበትን ጊዜ እና ቦታ እንዲሁም እነዚህ ናሙናዎች በጨረታው ለተሸነፉ ተጫራቾች የሚመለሱ ወይም ሊመለሱ የማይችሉ መሆናቸውን፣

በ/ የግምገማ ዘዴዎች፣ ለዚሁ ግምገማ የሚያገለግሉትን መስፈርቶች እና እንደአስፈላጊነቱ ለመስፈርቱ የሚኖረውን የነጥብ ድርሻ፣ እንዲሁም ሁለት እና ከሁለት በላይ የሆኑ ተወዳዳሪዎች በግምገማው እኩል ቢሆኑ አሸናፊውን ተጫራች ለመለየት የሚጠቀሙበትን ዘዴ፣

ተ/ ውሉ የዋጋ ማስተካከያ የሚፈቅድ ከሆነ በውል አፈፃፀም ወቅት የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግበት ሁኔታ፣

ቸ/ የጨረታ ማስከበሪያ እና የውል አፈፃፀም ዋስትና መጠን፣ዓይነት እንዲሁም እነዚህ ዋስትናዎች ፀንተው የሚቆዩበትን ጊዜ፣

ነ/ የጨረታው ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ እንዲሁም የርክክቡን ቦታና ጊዜ፣

ኘ/ ጨረታው የቴክኒክ እና የፋይናንስ ሰነዱ ለየብቻው የሚቀርብ ከሆነ የሚቀርብበት ሁኔታ፣

አ/ የቅድሚያ ክፍያ የሚሰጥ ከሆነ፣የቅድሚያ ክፍያውን መጠን እና ተቀባይነት ያለውን የዋስትና ዓይነት፣

ከ/ ተጫራቾች በጨረታው አፈፃፀም ሂደት ቅሬታ ካላቸው በዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች መሠረት አቤቱታ እና ይግባኝ የማቅረብ መብት እንዳላቸው እና አቤቱታው የሚቀርብበትን ሥነ ሥርዓት፣ እና

ኸ/ በልማት ድርጅቱ ከአሸናፊው ተጫራች ጋር ውል ከመፈረሙ በፊት በጨረታ ሰነዱ ከተገለጸው የአቅርቦት መጠን ላይ መጨመር ወይም መቀነስ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በአሸናፊው ተጫራች የቀረበው ዋጋ ሳይቀየር እስከ ሃያ በመቶ (20%) መጨመር ወይም መቀነስ እንደሚችል፡፡

## 75. የብቃትና የግምገማ መስፈርት አዘገጃጀት

1) የልማት ድርጅቱ የመጫረቻ ሰነድ የሚገመገምበትን መስፈርት በጨረታ ሰነዱ የብቃትና የግምገማ መስፈርቶች ላይ በግልፅ ማሳየት አለበት፡፡

2) የጨረታ መገምገሚያ መስፈርት እንደ ግዥው አይነት የሚለያይ ቢሆንም ከሚከተሉት ሁለት መሰረታዊ የመምረጫ ዘዴዎች በአንዱ ተፈፃሚ መሆን ይኖርበታል፡፡

    ሀ/ ለግዥው የተቀመጠውን የቴክኒክ መመዘኛ መስፈርት በመወሰን፣ የቴክኒክ መመዘኛውን ካሟሉት ተጫራቾች መካከል አነስተኛ ዋጋ ያቀረበውን ተጫራች መምረጥ፣ ወይም

    ለ/ ግዥው የሚኖረውን ጠቀሜታ ወይም ኢኮኖሚያዊ እሴት ሊወስኑ የሚችሉ የቴክኒክ መስፈርቶችን ድርሻ በመወሰን እና እያንዳንዱ መስፈርት የሚኖረውን አንፃራዊ ክብደት በግልጽ በጨረታ ሰነዱ ላይ በማሳየትና በእነዚህ መስፈርቶች ላይ የተመሠረተ የቴክኒክ ግምገማ በማካሄድ በአጠቃላይ በቴክኒክ እና በዋጋ ድምር ከፍተኛ ነጥብ ያገኘውን መምረጥ፣

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የሕይወት ዘመን ወጪ ትንተና ዘዴን መጠቀም ይችላል፡፡

4) የልማት ድርጅቱ ተጫራቾችን ያቀረቡትን ሰነድ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በተገለጹት መስፈርቶች መሠረት በመገምገም አሸናፊ የሚሆነውን ተጫራች ከለየ በኋላ የአሸናፊው ተጫራች ወቅታዊ የብቃት ሁኔታ በድሕረ ግምገማ መረጋገጥ አለበት ብሎ ሲያመን ይህንኑና ለድሕረ ግምገማ ዓላማ የሚጠቀምበትን መስፈርት በቅድሚያ በጨረታ ሰነዱ ላይ ማመልከት አለበት፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ለማወዳደሪያነት የሚመረጡት መስፈርቶች ዕቃው ወይም አገልግሎቱ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ለመወሰን አስተዋፅኦ የሚኖራቸው መሆኑን ለማረጋገጥ እና የግዥውን ጠቀሜታ ለመወሰን ባላቸው አስተዋፅኦ ደረጃ መሠረት አንፃራዊ ክብደት ሊሰጣቸው ይችላል፡፡

## 76. የጨረታ ቅፅና የዋጋ ማቅረቢያ ሠንጠረዥ

1) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በሚያዘጋጁት የጨረታ ሰነድ ውስጥ እንደግዥው ባህሪ በተጫራቾች ሊሞላ የሚገባውን የጨረታ ቅፅ፣ ወይም ሰንጠረዥ እና የጨረታ

ሰነዱ ውስጥ መካተታቸው ተገቢ ነው ተብሎ የሚታመንባቸውን ሌሎች ቅፆችን ማካተት አለባቸው፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በልማት ድርጅቶች የሚዘጋጀው የዋጋ ማቅረቢያ ቅጽ እንደአስፈላጊነቱ ዋጋን፣ ታክስን እና ሌሎችን ከዋጋ አቀራረብ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በግልፅ ለማመልከት የሚያስችል እንዲሁም የጨረታ ግምገማን ግልጽና ቀልጣፋ ማድረግ የሚችል መሆን አለበት፡፡

3) የሚዘጋጀው የጨረታ ቅፅ በተቻለ መጠን ተወዳዳሪው ግልፅ የሆነ የመወዳደሪያ ሐሳብ እንዲያቀርብ የሚያስችል፣ የጨረታ አካሄዱን መረዳቱን የሚያረጋግጥ፣ ጨረታውን የሚያደናቅፉ ድርጊቶች እንዳይፈፀሙ የሚከላከል እና ተጫራቹ ላቀረበው የመወዳደሪያ ሐሳብ ሙሉ ኃላፊነት እንዲወስድ የሚያደርግ መሆን አለበት፡፡

## 77. የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ

የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በሚያዘጋጁት የጨረታ ሰነድ ውስጥ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ማካተት አለባቸው፡፡

1) የልማት ድርጅቱ ዝርዝር የቴክኒክ ግምገማ ለሚጠይቁ ግዥዎች ዝርዝር የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ማዘጋጀት አለባቸው፡፡

2) የሚዘጋጀው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ በተጠቃሚዎች ፍላጎት ላይ ተመስርቶ እንደግዥው ዓይነት ጠቀሜታን፣ አሠራርን፣ የቴክኒክ ወይም የዲዛይን ባህሪ እና የመሳሰሉትን መሠረት በማድረግ ውድድርን እንዳይገድብ ተደርጎ መዘጋጀት አለበት፡ ፡

3) የሚዘጋጀው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ የውሉ አንድ ክፍል በመሆን የአቅርቦቱን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

4) የሚፈለገው ዕቃ፣ የምክር አገልግሎት፣ የግንባታ ሥራ ወይም አገልግሎት የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ስለሚፈፀመው ግዥ በቂ ዕውቀት ባላቸው የልማት ድርጅቱ ባለሙያዎች ሊዘጋጅ ይችላል፡፡

5) የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ በሚዘጋጅበት ጊዜ የተወሰነን አምራች የንግድ ምልክት ወይም አገልግሎት ሰጪ ወይም የተመረተበትን ሀገር ማመልከት የለበትም፡፡

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 የተደነገገው ቢኖርም የልማት ድርጅቱ ግዥውን የሚያከናውነው ከደንበኞች ጋር በገባው የስራ ወይም አቅርቦት ወይም አገልግሎት

ውል መሰረት ከሆነ፣ በደንበኛው ፍላጎት ለማሟላት የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ በሚዘጋጅበት ጊዜ የተወሰነን አምራች የንግድ ምልክት ወይም አገልግሎት ሰጪ ወይም የተመረተበትን ሀገር ሊጠቀስ ይቻላል፡፡

7) የሚዘጋጀው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ የልማት ድርጅቱን አሁን ወይም ወደፊት ሊፈጠር የሚችል ፍላጎትን ለማሟላት የሚያስችሉ የጠቀሜታ እሴቶችን ለመግለፅ የሚያስችል እና ጥቅም ላይ ሊውሉ የማይችሉ እሴቶችን የማያካትት መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡
8) እስከተቻለ ድረስ ሀገራዊ ደረጃ የማውጣት እና ጥራት የማረጋገጥ ኃላፊነት የተሰጣቸው ተቋማት ወይም ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያላቸው ተቋማት የሚያወጧቸውን ደረጃዎች እና የብቃት ማረጋገጫዎች ማካተት አለበት፡፡
9) የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫው በጨረታው መሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች የተሟላና ትክክለኛ የመጫረቻ ሰነድ እንዲያዘጋጁ በሚያስችል ዓይነት ተሟልቶ እና በዝርዝር ተዘጋጅቶ የጨረታው ሰነድ አንድ ክፍል መሆን አለበት፡፡

## 78. አጠቃላይና ልዩ የውል ሁኔታዎች

1) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የጨረታ ሰነድ ክፍል ሆነው የተዘጋጁትን የአጠቃላይ እና የልዩ ውል ሰነዶችን በጨረታ ሰነዱ በማካተት ለተጫራቾች ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ አለባቸው፡፡
2) በጨረታ ሰነዱ አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ላይ ማሻሻያ ሊደረግባቸው አይችልም፡፡ ሆኖም አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ላይ የሰፈሩትን አንቀጾች በማጣቀስ በአጠቃላይ የውል ሁኔታው በተፈቀደ አግባብ ብቻ ልዩ የውል ሁኔታውን እንደሚፈፀመው ግዥ ባህሪና ዓይነት ማሻሻል ይቻላል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የሚያዘጋጁት ልዩ የውል ሁኔታ እንደግዥው ዓይነት ሊለያይ ቢችልም የሚከተሉትን ያካተተ መሆን አለበት፡፡

ሀ/ የልማት ድርጅቱንና የተጫራቹን ግዴታና ኃላፊነትን በግልፅ ያመለከተና በሁለቱም ወገኖች ላይ የሚጣሉ ግዴታዎች ህጋዊ መሠረት ያላቸውና ሊፈጸሙ የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

ለ/ እንደአስፈላጊነቱ የውሉ አፈጻጸም የሚከተላቸውን ዋና ዋና ሂደቶች፤ የማስረከቢያ ጊዜ፣ አስተሻሸግ፣ የማጓጓዝ ኃላፊነት፣ የዋጋ ማስተካከያ፣ የክፍያ አፈፃፀም፣ የርክክብ እና የፍተሻ ሥነ-ሥርዓት፣ ዋስትና እና የመሳሰሉትን አተገባበር በግልጽ ያስቀመጠ መሆን ይኖርበታል፡፡

ሐ/ በዚህ መመሪያ የልማት ድርጅቱን ጥቅም ለማስጠበቅ የተቀመጡ የውል ቃሎች እና ድንጋጌዎች በአግባቡ በውሉ የተካተቱ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

## 79. ጨረታ ተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ የሚቆይበትን ጊዜ ስለመወሰን

1) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የጨረታ ሰነድ በሚያዘጋጅበት ጊዜ የመጫረቻ ሰነድ የሚቀርብበትን የመጨረሻ ቀን የሚከተሉትን መሠረት አድርጎ ይወስናል፡፡

ሀ/ ተወዳዳሪዎች ተቀባይነት ያለው የመጫረቻ ሰነድ ለማዘጋጀት፣ መረጃ ለማሰባሰብ፣ ለመተንተን፣ እንደአግባብነቱ እሽሙር ወይም ሽርክና ለመመስረት፣ ከአምራቹ የሚሠጥ ውክልና እና የመፈረም ሥልጣን ማረጋገጫ ለማግኘት እና ሌሎች በጨረታው ለመሳተፍ የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት የሚወስድባቸውን ጊዜ ታሳቢ ያደረገ መሆን አለበት፡፡

ለ/ በዚህ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ጨረታ ተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ የሚቆይበት ጊዜ እንደ ግዥው ዓይነትና የግዥ ዘዴ እንዲሁም ከውስብስብነት አንጻር በዚህ መመሪያ አባሪ 3 ከተገለጸው ቀን በታች መሆን የለበትም፡፡

## 80. ስለ ናሙና አቀራረብ

1) የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ማዘጋጀት የማይቻል በሚሆንበት ጊዜ ወይም ከተዘጋጀው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ በተጨማሪነት ግዥው በተሻለ ተፈፃሚ

ሊሆን የሚችለው የናሙና ምልከታ ሲኖረው መሆኑ ሲታመንበት የልማት ድርጅቱ ጨረታው ከመዘጋቱ በፊት ናሙና ሊያስቀርብ ወይም እንዲቀርብ ሊያደርግ ይችላል፡፡

2) የልማት ድርጅቱ ናሙና ራሱ አቅርቦ ተወዳዳሪዎች ለዕይታ በቀረበው ናሙና መሠረት እንዲያቀርቡ በሚፈለግበት ወቅት፣

ሀ/ የሚቀርበው ናሙና በደንበኛው ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ካልሆነ በስተቀር በአንድ አምራች ወይም የንግድ ምልክት በተሠራ ዕቃ የተወሰነ መሆን የለበትም፡፡ እስከተቻለ ድረስ ተቀባይነት ያላቸው ናሙናዎች ዓይነት ለዕይታ እንዲቀርቡ ሆኖ ከቀረቡት ናሙናዎች ጋር ተመሳሳይ የሆነ የጥራት ደረጃ ያላቸው ሌሎች ዕቃዎችንም ማቅረብ እንደሚቻል ለተጫራቾች ማሳወቅ ይገባል፡፡

ለ/ ተወዳዳሪዎች ናሙናውን በግልፅ በሚያዩበት ቦታ ላይ መደረጉን እና ተገቢ እስከሆነ ድረስ ስለናሙናው መግለጫ የሚሰጥ ባለሙያ መመደቡን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

ሐ/ የልማት ድርጅቱ ተወዳዳሪዎች ዕይታ ካቀረበው ናሙና በተጨማሪ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ የሚያዘጋጅ ከሆነ የሚዘጋጀው መግለጫ እስከተቻለ ድረስ የቀረበውን ናሙና የሚገልፅና ለዕይታ ከቀረበው ናሙና የቴክኒክ ባህሪ ጋር የተጣጣመ ሊሆን ይገባል፡፡

3) በተሰጣቸው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ መሠረት ተወዳዳሪዎች ናሙና እንዲያቀርቡ በሚፈለግበት ወቅት፤

ሀ/ የሚቀርቡት ናሙናዎች ዓይነት፣ ብዛት የሚቀርቡበት ጊዜ እና አኳኋን ተወዳዳሪዎች በግልፅ እንዲያውቁት መደረግ ይኖርበታል፡፡

ለ/ ናሙናዎች ጨረታው ከመከፈቱ በፊት መቅረብ አለባቸው፡፡ ሆኖም ተወዳዳሪው ናሙናውን በወቅቱ ልኮ ከ ተወዳዳሪው ቁጥጥር ውጪ በሆነ ምክንያት በማጓጓዝ ሂደት ቢዘገይ የልማት ድርጅቱ የግዥውን አፈፃፀም አይጎዳም ብሎ እስካመነ ድረስ ተጨማሪ የናሙና ማቅረቢያ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል፡፡

4) ተጫራቾች የተሟላ ናሙና በአካል ማቅረብ የማይችሉ ሲሆን እና የማይችሉበትንም ምክንያት የልማት ድርጅቱ ሲቀበለው ስለናሙናው ያላቸውን መረጃ ማቅረብ እንዲችሉ ሊፈቅድ ይችላል፡፡ ይህም ናሙናውን ፎቶግራፍ ወይም የተገኘውን የናሙና ክፍል ማቅረብን ይጨምራል፡፡ ሆኖም በዚህ መልኩ ተፈፃሚ ለማድረግ የሚቻለው አፈፃፀሙ የተሻለውን ተጫራች በመምረጥ ሂደት ልዩነት የማያመጣ እና በተወዳዳሪዎች መካከል ልዩነት ሊፈጥር የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

5) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በተጫራቾች የቀረቡ ናሙናዎችን በጥንቃቄ የመያዝ እና የመፈተሽ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ሆኖም ተጫራቾች ያቀረቡት ናሙና በሚመረመርበት ወቅት በናሙናው ባህሪይ ምክንያት ቢጠፋ ወይም ቢበላሽ ካሣ አይከፈላቸውም፡፡

6) የናሙናው ምርመራ ከተደረገ በኋላ ናሙና ለተጫራቾች ተመላሽ ይደረጋሉ፡፡ ተጫራቾች ያቀረቡትን ናሙና አሸናፊው ድርጅት ውል ከፈረመበት ቀን ጀምሮ በ3 ወር ጊዜ ውስጥ ካልወሰዱ በውርስ ለልማት ድርጅቱ ገቢ ይደረጋል፡፡

7) በልማት ድርጅቱ የተለየ ውሳኔ ካልተሰጠ በስተቀር የአሸናፊው ተጫራች ናሙና ግዥው እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ በናሙናነት ተይዞ መቆየት ያለበት ሲሆን ናሙናውም በርክክብ ወቅት ለማነፃፀሪያነት እንዲያገለግል መደረግ ይኖርበታል፡፡

## 81. በጨረታ ሰነድ ላይ ስለሚደረግ ማብራሪያ ወይም ማሻሻያ

1) ተወዳዳሪዎች በልማት ድርጅቱ በተዘጋጀ የጨረታ ሰነድ ላይ የማብራሪያ ወይም የማሻሻያ ጥያቄያቸውን ለልማት ድርጅቱ ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡

2) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የጨረታ ሰነድ ላይ ከዚህ በታች የተመለከቱ ሁኔታዎችን አሟልቶ ከማንኛውም ተወዳዳሪ የሚቀርብ የማብራሪያ ወይም ማሻሻያ ጥያቄን ተቀብለው ምላሽ መስጠት አለባቸው፡፡

   ሀ/ ጨረታው ተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ የሚቆይበት ዝቅተኛ ጊዜ ሰላሳ (30) ቀናት ለሆነ ግዥ ለመጫረቻ ሰነድ ማቅረቢያ የተወሰነው ጊዜ ሊያበቃ አስራ አምስት (15) ቀናት እስኪቀረው ድረስ ለቀረበ ጥያቄ፣

ለ/ ጨረታው ተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ የሚቆይበት ዝቅተኛ ጊዜ ሃያ (20) ቀናት ለሆነ ግዥ ለመጫረቻ ሰነድ ማቅረቢያ የተወሰነው ጊዜ ሊያበቃ አስር (10) ቀናት እስኪቀረው ድረስ ለቀረበ ጥያቄ፣

ሐ/ ጨረታው ተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ የሚቆይበት ዝቅተኛ ጊዜ አስራ አምስት (15) ቀናት ለሆነ ግዥ ለመጫረቻ ሰነድ ማቅረቢያ የተወሰነው ጊዜ ሊያበቃ ሰባት (7) ቀናት እስኪቀረው ድረስ ለቀረበ ጥያቄ፣

መ/ ጨረታው ተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ የሚቆይበት ዝቅተኛ ጊዜ አስር (10) ቀናት ለሆነ ግዥ ለመጫረቻ ሰነድ ማቅረቢያ የተወሰነው ጊዜ ሊያበቃ አምስት (5 ) ቀናት እስኪቀረው ድረስ ለቀረበ ጥያቄ፣

ሠ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ከተደነገገው ቀን ባነሰ ጊዜ ለቀረበ ማብራሪያ ወይም የማሻሻያ ጥያቄ የልማት ድርጅቱ ምላሽ እንዲሰጥ አይገደድም፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ የማብራሪያ ወይም የማሻሻያ ጥያቄ ከ ተወዳዳሪዎች ሲቀርብ የልማት ድርጅቱ ጨረታውን ከመክፈቱ በፊት በ3 የሥራ ቀናት ውስጥ ምላሹን ለሁሉም የጨረታ ሰነዱን ለወሰዱ እና አዲስ ለሚወስዱ ተጫራቾች የጨረታው አካል በማድረግ በደብዳቤ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ሊደርሳቸው ይገባል፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 3 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ተወዳዳሪዎች ከልማት ድርጅቱ በተሰጣቸው ምላሽ ወይም ማሻሻያ ላይ ቅሬታ ያላቸው እንደሆነ ይግባኝ ሰሚና ውሳኔ ሰጪ ቦርድ ለማቅረብ እንዲችሉ የልማት ድርጅቱ ጨረታው ሳይዘጋ ማቆየት ወይም የጨረታ መዝጊያ ቀኑን ማራዘም አለበት፡፡

5) ከ ተወዳዳሪዎች ለሚቀርብ የማብራሪያ ወይም የማሻሻያ ጥያቄ የሚሰጠው ምላሽ በጽሑፍ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ወይም እንደአስፈላጊነቱ በልማት ድርጅቱ ድረ-ገጽ ላይ ሊወጣ ይችላል፡፡

6) በልማት ድርጅቶች ከ ተወዳዳሪዎች የሚቀርብላቸውን የማብራሪያ ጥያቄ መነሻ በማድረግ ቀደም ሲል በተዘጋጀ የጨረታ ሰነድ ላይ ማሻሻያ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኙት የጨረታ ሰነዱን ማሻሻል ይችላሉ፡፡

7) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በንዑስ አንቀጽ 6 ላይ በተገለፀው መሠረት በጨረታ ሰነዱ ላይ ማሻሻያ ሲያደርጉና ጨረታውን ለመዝጋት በቀረው ጊዜ ውስጥ ተወዳዳሪዎች የተደረገውን ማሻሻያ አካተው የመጫረቻ ሰነድ ለማዘጋጀት እንደማይችሉ ሲገመት የጨረታ ማስታወቂያ በወጣበት በጋዜጣ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ወይም የጨረታ ሰነዱን ለገዙ ለሁሉም ድርጅቶች በደብዳቤ እና እንደአስፈላጊነቱ በልማት ድርጅቱ ድረ-ገጽ ላይ የጨረታ መዝጊያ ቀኑን ማራዘም አለባቸው፡፡

8) ተወዳዳሪዎች የመጫረቻ ሰነዳቸው ላይ ማሻሻያ ማድረግ ሲፈልጉ የማሻሻያ ኃሳባቸውን ከጨረታ መዝጊያው ቀንና ሰዓት በፊት ማስገባት አለባቸው፡፡

## 82. የጨረታ ቋንቋ

1) በልማት ድርጅቶች የሚያዘጋጀው የጨረታ ማስታወቂያው፣ የጨረታ ሰነድ እና ጨረታው የሚካሄድበት ቋንቋ በአማርኛ ወይም የተሻለ ውድድርና ጠቀሜታ እንዳለው ሲያምን የጨረታ ማስታወቂያው፣ የጨረታ ሰነዱ እና የጨረታው ሒደት በእንግሊዝኛ ቋንቋ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል፡፡

2) ለዓለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ ማስፈፀሚያ የሚዘጋጅ ማናቸውም ሰነድ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ይሆናል፡፡

3) ተወዳዳሪዎች የመጫረቻ ሰነዶቻቸውና ደጋፊ ማስረጃዎቻቸው በጨረታ ሰነዱ ጨረታው እንዲካሄድበት ከተፈቀደው ውጭ በሌላ ቋንቋ የተዘጋጁ በሚሆኑበት ጊዜ በሕጋዊ ተርጓሚ ተተርጉመው የትርጉሙ ቅጅ ከዋናው ሰነድ ጋር መቅረብ አለበት፡፡

4) የልማት ድርጅቱ በተጫራቹ የቀረበው ሰነድ በመጀመሪያ በተዘጋጀበት እና ለጨረታው በተፈቀደው ቋንቋ ትርጉም መካከል ልዩነት እንዳለው ሲያረጋግጥ ልዩነቱ በጨረታው ይዘት ላይ መሰረታዊ ለውጥ አያመጣም ብሎ ካላመነ በስተቀር ሰነዱን ውድቅ ማድረግ ይችላል፡፡

## 83. የመጫረቻ ዋጋ

የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተጫራቾች የሚሰጡት የመጫረቻ ዋጋ በሌላ ተጫራች ዋጋ ላይ ያልተመሰረተ፣ በጨረታው እና በውል አፈፃፀሙ ወቅት የማይለዋወጥ ዋጋ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

## 84. የመጫረቻ ሰነድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ

1) የልማት ድርጅቱ የመጫረቻ ሰነድ ፀንቶ መቆየት ያለበትን ጊዜ በመወሰን በጨረታ ሰነዱ ውስጥ ማካተት አለበት፡፡ የመጫረቻ ሰነድ ወይም የጨረታው ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ለመወሰን የልማት ድርጅቱ የግዥውን ውስብስብነት እና በጨረታው ሊሳተፉ የሚችሉ ተወዳዳሪዎችን ብዛት፣ ግዥውን ለመገምገም የሚወስደውን ጊዜ እና አቤቱታ ወይም ይግባኝ ቢነሳ እልባት ለመስጠት እና ከአሸናፊው ድርጅት ጋር ውል እስከመፈራረም ድረስ የሚፈጀውን ጊዜ ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተገለፀው መሠረት የመጫረቻ ሰነድ ረዘም ላለ ጊዜ ፀንቶ የሚቆይበት ሁኔታ መኖሩን የልማት ድርጅቱ ካላመነ በስተቀር ጨረታው ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ጨረታው ከሚከፈትበት ዕለት ጀምሮ ከሰላሳ (30) ቀናት መብለጥ የለበትም፡፡

3) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የግዥ ሂደታቸውን የመጫረቻ ሰነዱ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ማጠናቀቅ እና ከአሸናፊው ድርጅት ጋር ውል መፈራረም አለባቸው፡፡ ሆኖም ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች የግዥ ሂደቱ ሳይጠናቀቅ ለግዥው የቀረበው ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ የሚያበቃ መሆኑን የልማት ድርጅቱ ሲረዳ ዋጋቸው ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ ለተጨማሪ ቀናት እንዲያራዝሙለት መጠየቅ አለበት፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 3 በተመለከተው መሠረት ተጫራቾች እንዲያራዝሙ የሚጠየቁት ተጨማሪ ቀናት የልማት ድርጅቱ የቀረውን የግዥ ሂደት ለማጠናቀቅ የሚበቃውን ያህል ቀናት ብቻ መሆን አለበት፡፡ ሆኖም ተጫራቾች

በማንኛውም ምክንያት ዋጋቸው ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ ለማራዘም ፈቃደኛ ባይሆኑ ለጨረታ ማስከበሪያ ያስያዙትን ዋስትና መውረስ ሳያስፈልግ ከጨረታው ውድድር እንዲወጡ ይደረጋል፡፡

5) በጨረታው ለተሳተፉ ተወዳዳሪዎች ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ እንዲያሻሽሉ ለቀረበላቸው ጥያቄ ለማሻሻል የሚስማሙ ከሆነ ማሻሻያውን መቀበላቸውን እና ዋጋ ጸንቶ የሚቆበትን ጊዜ ያራዘሙት እስከመቼ እንደሆነ በመጥቀስ በጽሑፍ ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም ለዚህ ጨረታ ያስያዙት የጨረታ ዋስትና መቆያ ጊዜ ማሻሻል ወይም አዲስ ዋስትና ማቅረብ አለባቸው፡፡

6) በዚህ አንቀጽ ንዑሰ አንቀፅ 5 በተገለጸው መሠረት የጨረታ ዋስትናውን ፀንቶ መቆያ ጊዜ ያላሻሻለ ተጫራች ያቀረበው ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ ለማሻሻል ፈቃደኛ እንዳልሆነ ተቆጥሮ ከጨረታው ውድድር ውጭ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

## 85. የጨረታ ማስከበሪያ

1) ከምክር አገልግሎት እና ከዋጋ ማቅረቢያ ግዥ በስተቀር የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ግልፅ ወይም በተገደበ ወይም የሁለት ደረጃ ጨረታ የግዥ ዘዴዎችን በሚጠቀሙበት ጊዜ በጨረታው ሰነድ ውስጥ ለእያንዳንዱ ግዥ የሚጠየቀውን የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በግልፅ መወሰንና ማመልከት አለባቸው፡፡ ሆኖም በተለያዩ ምክንያቶች አስፈላጊነቱን የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ካመነበት ለምክር አገልግሎት ግዥም ቢሆን ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና እንዲያሲይዙ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ቢኖርም የልማት ድርጅቱ ለኤሌክትሮኒክ ልውጥ ሐራጅ ጨረታ እና እንደ ግዥው ባህሪ እንዲሁም አስቸኳይነት ለሌሎች የግዥ ዘዴዎች በጨረታ ማስከበሪያ ምትክ በዚህ መመሪያ አባሪ 4 መሰረት የጨረታ መተማመኛ ቅጽ ፈርመው እንዲያቀርቡ ሊጠየቅ ይችላል፡፡

3) የልማት ድርጅቱ የጠቅላላ ግዥውን ግምታዊ ዋጋ መሠረት በማድረግ ከ0.5% ያላነሰ እና 2% ያለልበለጠ የጨረታ ማስከበሪያ የገንዘብ መጠን ወስኖ በጨረታው ጥሪው እና በጨረታ ሰነዱ ውስጥ መግለፅ ይኖርበታል፡፡ በዚህ መሠረት

የሚወሰነው የጨረታ ማስከበሪያ መጠን ከብር 2,000,000 (ሁለት ሚሊዮን ብር) የበለጠ መሆን የለበትም፡፡

4) የሚቀርበው የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና አቅራቢው ምርጫ ከባንክ በሚሰጥ የተረጋገጠ የክፍያ ማዘዣ፣ በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና ወይም በባንክ የተረጋገጠ ሌተር ኦፍ ክሬዲት ሊሆን ይችላል፡፡

5) ከተጫራቾች የሚቀርበው የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ፀንቶ መቆያ ጊዜ የጨረታው ዋጋ ፀንቶ ከሚቆይበት የመጨረሻ ቀን በኋላ ቢያንስ ለተጨማሪ ሃያ ስምንት (28) ቀናት ፀንቶ መቆየት አለበት፡፡

6) የውጭ ሀገር ተጫራቾች የሚያቀርቡት ከኢትዮጵያ ውጭ ባሉ ባንኮች የተሠጠ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በሀገር ውስጥ ባንኮች ማረጋገጫ ያገኘና በሁኔታ ላይ ያልተመሠረተ መሆን ይኖርበታል፡፡

## 86. የመጫረቻ ሰነድ አቀራረብ

ተጫራቾች የጨረታ ጥሪው ከተደረገበት ዕለት ጀምሮ የጨረታ ሰነዳቸውን ማስገባት እንዲችሉ እስከ ጨረታው መዝጊያ ሰዓት ድረስ ጨረታው ክፍት ሆኖ መቆየት ይኖርበታል፡፡

## 87. የጨረታ አከፋፈት

1) ጨረታው የሚከፈተው በጨረታው ጥሪ ወይም ማሻሻያ ተደርጎ ከሆነ በማሻሻያው ላይ በተገለጸው ቀን እና ሰዓት ይሆናል፡፡ ጨረታው ሲከፈትም፣

ሀ/ ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በቀጥታ የጨረታውን ሥነ ስርዓት ሊከታተሉ በሚችሉበት ሁኔታ ይሆናል፡፡ ሆኖም ተጫራቹ በራሱ ምርጫ ጨረታው በሚከፈትበት ጊዜ በቀጥታ መከታተል ባይችል የጨረታውን መከፈት አያስተጓጉልም፡፡

ለ/ የጨረታው አከፋፈት ሂደት ላይ መከታተል የሚፈልግ የውስጥ ኦዲት ባለሙያ፣ የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና መከታተያ ክፍል እንዲሁም ማንኛውም የመገናኛ ብዙሐን ድርጅት ወኪል ወይም ሌሎች ፍላጎት እና

ጥቅም ያላቸው ሰዎች በታዛቢነት መሳተፍ ቢፈልጉ የጨረታውን የአከፋፈት ሥርዓት በበየነ መረብ መከታተል እንዲችሉ ይፈቀዳል፡፡

ሐ/ ከግዥ ሥራ ክፍል ወይም የግዥ ገምጋሚ ኮሚቴ ቢያንስ 3 አባላት በጨረታ አከፋፈት ሂደቱ ላይ መሳተፍ አለባቸው፡፡ እስከተቻለ ድረስ የግዥው ተጠቃሚ ከሆኑ ሥራ ክፍሎች የሚወከሉ ባለሙያዎች በጨረታው አከፋፈት ስነ-ስርዓቱ ላይ ሊገኙ ይችላሉ፡፡

2) የግዥ ሥራ ክፍል ወይም የግዥ ገምጋሚ ኮሚቴው የጨረታውን አከፋፈት ሂደት ቃለ-ጉባዔ መያዝ አለበት፡፡ ይህ ቃለ-ጉባዔም የተጫራቾቹን ሥም፣ ያቀረቡትን ዋጋ እና በጨረታው አከፋፈት ሂደት ላይ የተነሡ ሌሎችንም አስፈላጊ ነጥቦች የሚይዝ ይሆናል፡፡ ቃለ-ጉባዔውም በጨረታው ላይ ለተሳተፉት እና ጨረታው ሲከፈት ላልተገኙ ተጫራቾች ባስመዘገቡት አድራሻቸው ሊላክላቸው ይገባል፡፡ ጨረታው ሲከፈት የነበሩ ተጫራቾች ቃለ ጉባኤው እንዲሰጣቸው ሲጠይቁ ግልባጩ እንዲሰጣቸው መደረግ አለበት፡፡

3) ማንኛውም በጨረታ መክፈቻ ሥርዓት ላይ ያልተከፈተና ለተጫራቾች ያልተነበበ የመጫረቻ ሰነድ ለቀጣይ ውድድር አያገለግልም፡፡

4) ማናቸውም ተጫራች በጨረታ መክፈቻ ሂደት ወቅት ከጨረታው ውጭ አይደረግም፡፡

5) የቴክኒክና የዋጋ ሰነዱ በአንድ ላይ እንዲቀርብ የተጠየቀ ጨረታ ከሆነ እንያንዳንዱ ተጫራች ያቀረበውን የመጫረቻ ሰነድ በመክፈት የተጫራቹን ስም፣ተጫራቹ ያቀረባቸው የቅድመ ብቃት መረጃዎች፣ ለውሉ ያቀረበውን ዋጋ፣ የዋጋ ቅናሽ መጠንና ሁኔታውን፣ የጨረታ ማስከበሪያ ዓይነት፣ መጠን እና ማናቸውንም የተጫራቾች አንጻራዊ ደረጃቸውን ለማወቅ ይረዳቸዋል ተብለው የሚታሰቡ ሌሎች ሁኔታዎችን ማሰማት አለባቸው፡፡

6) የቴክኒክና የዋጋ ሰነዱ በተለያየ ሁኔታ እንዲቀርብ የተጠየቀ ከሆነ በጨረታው መክፈቻ ሥነ-ስርዓት የቴክኒክ ሰነዱ የያዘው ሀሳብ እንዲከፈት ተደርጎ የተጫራቹን ማንነት ጨምሮ በወቅቱ ሊገለጹ የሚችሉ ነጥቦች ማሰማት አለባቸው፡፡

7) በቴክኒክ ያለፉ ተወዳዳሪዎችን የዋጋ መክፈቻ ጊዜ በማሳወቅ የተወዳዳሪዎችን ዋጋ በመክፈት የተጫራቹን ስም፣ ለግዥው ያቀረበውን ዋጋ፣ የዋጋ ቅናሽ ካለው መጠኑን እና ሁኔታውን፣ እንዲሁም ከዋጋ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች ተጫራቾች እንዲያውቁ መደረግ አለበት፡፡

## 88. ጨረታን መገምገምና ማወዳደር

1) የልማት ድርጅቱ ጨረታውን የተሟላ ነው ብሎ ለቀጣዩ ግምገማ ሂደት ሊያሳልፈው የሚችለው በተጫራቹ የቀረበው የመጫረቻ ሰነድ በመክፈቻ ስነ-ስርዓቱ ወቅት የተከፈተ እና በጨረታ ሰነዱ ላይ የተዘረዘሩትን የቅድመ ሁኔታዎች ተፈላጊ ነጥቦች የሚያሟላ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡

2) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ወደ ዝርዝር ግምገማ ከመግባታቸው አስቀድሞ የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ በሚያደርግበት ወቅት የሚከተሉትን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡፡

   ሀ/ በዘርፉ የታደሰ የንግድ ፈቃድ እና ተጫራቹ የውጭ ሀገር ከሆነ በሀገሩ የተሰጠ ህጋዊ ንግድ ፈቃድ መኖሩን፣

   ለ/ የታክስ ክሊራንስ፣

   ሐ/ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ምስክር ወረቀት እና እንደአስፈላጊነቱ የኤክሳይዝ ታክስ ምዝገባ መኖሩን፣

   መ/ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና፣

   ሠ/ ተጫራቹ የተሰጠውን የጨረታ ቅጽ የሞላ መሆኑን፤

   ረ/ እንዳስፈላጊነቱ የብቃት ማረጋገጫ ሰነዶች፣ ከአምራች ወይም ከአከፋፋዮች የሚሰጥ ውክልና ወይም የሽሙር ማህበር መመስረቻ ሰነድ እንዲሁም ሌሎችም አስፈላጊ ሰነዶች ተካተው መቅረባቸውን፣

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተገለጸው መሠረት የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ ያላሟሉ ተጫራቾች ወደ ሚቀጥለው ዝርዝር የግምገማ ሂደት አያልፉም፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌዎች ቢኖሩም ተጫራቾች በጨረታ ሰነዱ የተጠየቁትን የህጋዊነት ማረጋገጫ ሰነዶች ከመጫረቻ ሰነዳቸው ጋር ባያቀርቡም

የልማት ድርጅቱ እንደ ጥቃቅን ጉድለት በመቁጠር ከጨረታ መዝጊያ በፊት የተዘጋጀ ወይም የተሰጠ እስከሆነ ድረስ ከጨረታ መክፈቻ በኋላ እንዲያቀርብ በማድረግ ተጫራቹን ወደ ቀጣዩ የግምገማ ሂደት እንዲገባ ሊያደርግ ይቻላል፡፡

5) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የማያሟሉ ተጫራቾችን ወደ ዝርዝር ግምገማ ማሳለፍ የለባቸውም፡-

ሀ/ የተጠየቀውን የጨረታ ማስከበሪያ ያላስያዘ፣

ለ/ በልማት ድርጅቱ የተጠየቁትን የሕጋዊነት ሠነዶች ያላቀረቡ ከሆነ፣

ሐ/ ሌሎች ወደ ዝርዝር ግምገማ ለማለፍ የተቀመጡ ሁኔታዎችን ያላሟላ፣

6) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተጫራቾች በአዋጁ፣ በዚህ አፈጻጸም መመሪያ እና በጨረታ ሰነዱ የተቀመጡ የቅድመ ብቃት ግምገማውን ያለፉ ተጫራቾች ብቻ የሚከተሉትን መስፈርቶች ተከትሎ ዝርዝር ግምገማ ማድረግ አለባቸው፡፡

7) አሸናፊው ተጫራች የሚመረጠው፡-

ሀ/ ለግዥው ተቀባይነት ያለውን ዝቅተኛ የቴክኒክ መመዘኛ መስፈርት በመወሰን፣ ዝቅተኛ የቴክኒክ መመዘኛውን ካሟሉት ተጫራቾች መካከል አነስተኛ ዋጋ ያቀረበውን ተጫራች መምረጥ፣

ለ/ ግዥው የሚኖረውን ጠቀሜታ ወይም ኢኮኖሚያዊ እሴት ሊወስኑ የሚችሉ የቴክኒክ መስፈርቶችን ድርሻ በመወሰን እና እያንዳንዱ መስፈርት የሚኖረውን አንፃራዊ ክብደት በግልጽ በጨረታ ሰነዱ ላይ በማሳየትና በእነዚህ መስፈርቶች ላይ የተመሠረተ የቴክኒክ ግምገማ በማካሄድ አጠቃላይ የቴክኒክ እና ዋጋ ድምር ከፍተኛ ነጥብ ያገኘውን መምረጥ፣

8) የቴክኒክና የዋጋ ሠነዱ ለየብቻ እንዲቀርብ የተጠየቀ ጨረታ ሲሆን የልማት ድርጅቱ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 87 መሠረት የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ ያለፉ ተጫራቾችን የቴክኒክ ግምገማ ከዚህ እንደሚከተለው ማከናወን አለባቸው፡፡

ሀ/ የልማት ድርጅቱ የቴክኒክ ግምገማ ያለፉ ተጫራቾች በጨረታ ሰነዱ ላይ የተገለጹ የቴክኒክ ግምገማ መስፈርቶችን ያሟሉ ስለመሆኑ መገምገምና

የተገኘው ውጤት ስልጣን በተሰጠው አካል ከፀደቀ በኋላ ውጤቱን ለተጫራቾች በሙሉ በተመሳሳይ ጊዜ መገለጽ አለበት፡፡

ለ/ የቴክኒክ ግምገማውን ላላለፉ ተጫራቾች የሚላክላቸው ማሳወቂያ የቴክኒክ ግምገማውን ያላለፉበት ምክንያት፣ እንዲሁም አቤቱታ ካላቸው አቤቱታቸውን ማቅረብ እንደሚችሉ የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡ በቴክኒክ ግምገማው ላይ አቤቱታ የቀረበ ከሆነ አቤቱታው የግዥ ህጉን ተከትሎ የመጨረሻ እልባት እስኪያገኝ ድረስ የዋጋው ፖስታ መከፈት የለበትም፡፡

ሐ/ አቤቱታ ቀርቦ ከሆነ ጉዳዩ የመጨረሻ እልባት ካገኘ በኋላ በቴክኒክ ውድድሩ ተቀባይነት ያላገኙ ተወዳዳሪዎች ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ተመላሽ ይደረጋል፡፡

መ/ የቴክኒክ ውጤታቸው ተቀባይነት ላገኙ ተጫራቾች የሚላከው ማሳወቂያ የቴክኒክ ውጤቱ ነጥብ የሚሰጠው ከሆነ ያገኙት ነጥብ፣ የሚከፈትበትን ዕለትና ሰዓት የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡ ማሳወቂያውም በእኩል ጊዜ እንዲደርሳቸው መደረግ እና ሁሉም ፈቃደኛ ተጫራቾች በጨረታው የዋጋ መክፈቻ የጨረታ ሥነ-ሥርዓት ላይ እንዲገኙ የሚያስችላቸው በቂ ጊዜ መስጠት አለበት፡፡

9) በጨረታ ሰነዱ ላይ ከተዘረዘሩት ባህርያት፣ የውል ሁኔታዎች እና ከሌሎች ተፈላጊ ነጥቦች ጋር መሰረታዊ የሆነ ለውጥ እና ልዩነት እስከሌለው ድረስ ወይም የጨረታውን መሠረታዊ ይዘት ሳይለወጥ ሊታረም የሚችል ጥቃቅን ስህተት ወይም ግድፈት ቢኖርም የልማት ድርጅቱ ጨረታውን እንደተሟላ አድርጎ ሊቀበል ይችላል፡፡

10) በጨረታ ሰነዱ የሚቀመጡ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 9 አፈጻጸም ከዚህ በታች የተመለከቱት ሁኔታዎች እንደ ጉልህ ልዩነት ይቆጠራሉ፡፡

ሀ/ የዕቃዎችና የተያያዥ አገልግሎቶች ወሰን፣ ጥራት ወይም አፈፃፀም ላይ የጎላ ልዩነት ይፈጥራል ተብሎ ሲታሰብ፣

ለ/ የግዥ ፈፃሚውን መብቶች ወይም የተጫራቹን ግዴታዎች የማዛባት እና ከጨረታ ሰነዶች ጋር ያለመጣጣም ሁኔታ ሲፈጠር፤ ወይም

ሐ/ በተጫራቾች መካከል ልዩነት ይፈጥራል ወይም የጨረታውን ውጤት ያስቀይራል ተብሎ ሲገመት፡፡

11) በጨረታው እኩል ዋጋ ያመጡ ወይም እኩል ተመራጭ የሆኑ ተጫራቾች በሚያጋጥሙበት ወቅት በዋጋ እና በቴክኒክ ድምር ውጤት ተወዳደረው እኩል የሆኑ ተወዳዳሪዎች በቴክኒክ ከፍተኛ ውጤት ላገኘው ተጫራች ቅድሚያ የሚሰጠው ሲሆን፣ በጨረታ ሠነድ ላይ የተገለጸውን ዝቅተኛ የመወዳደሪያ መስፈርት አሟልተው በዋጋ ብቻ ለሚወዳደሩ ተጫራቾች በሚኖሩበት ጊዜ አሸናፊውን ለመለየት በጨረታው ከሰጡት ዋጋ በታች እንደገና ዋጋ እንዲሰጡ ተደርጎ በዋጋ ዝቅተኛ የሰጠው ድርጅት አሸናፊ ይሆናል፡፡

12) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 11 በተገለጸው መሠረት ዋጋ እንደገና እንዲሰጡ ተደርጎ እኩል ዋጋ ከአቀረቡ አሸናፊው ድርጅት በዕጣ የሚለይ ይሆናል፡፡

13) በጨረታ ውድድሩ ተካፋይ የሆነው አንድ ተጫራች ብቻ ከሆነ የልማት ድርጅቱ የቀረበው አንድ ተጫራች ያቀረበው የመወዳደሪያ ኃሳብ አጥጋቢ እና ዋጋውም ወቅታዊ ፣መሆኑን እንዲሁም የሌሎች ተወዳዳሪዎችን ተሳትፎ የሚገድቡ ምክንያቶች በጨረታ ሰነድ ላይ ያለመኖራቸውን በማረጋገጥ ድጋሚ ጨረታ ማውጣት ሳያስፈልግ የቀረበውን አንድ ተጫራች አሸናፊ ሊያደርግ ይችላል፡፡

14) ግዥው በዓለም አቀፍ ጨረታ የሚፈፀም ሆኖ ለግምገማ ዓላማ ሲባል በተለየ ሁኔታ እንዲቀርብ በጨረታ ሰነዱ ካልተገለጸ በስተቀር በተጫራቾች የሚቀርበው ዋጋና የሚካሄደው የጨረታ ግምገማ ታክስን ማካተት አለበት፡፡ ሆኖም በተጫራቹ ዋጋ ውስጥ ታክስ መኖሩንና አለመኖሩ ግልጽ ካልሆነ ዋጋው ታክስ እንደተካተተ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

## 89. የሒሳብ ስህተቶችን ስለማረም

1) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በምርመራ ወቅት የተገኙ የሒሳብ ስህተቶችን ማረም የሚችሉ ሲሆን የተስተካከሉ የሒሳብ ስህተቶችን በአፋጣኝ ለሚመለከተው ተጫራች ማሳወቅ አለባቸው፡፡

2) ተጫራቹ በሲሳብ ማስተካከያው ከተስማማ ወደ ቀጣይ ግምገማ የሚሄድ ሲሆን በሂሳብ ማስተካከያው የማይስማማ ከሆነ የጨረታ ማስከበሪያ ተወርሶ ከጨረታው እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

## 90. የተሰበረ እና የተጋነነ የጨረታ ዋጋ

1) የዕቃ ግዥን በተመለከተ በተጫራቹ የቀረበው የጨረታ ዋጋ እንደሁኔታው ከታወቀ አምራች ወይም አከፋፋይ ወይም የልማት ድርጅቱ በሚያከናውነው የገበያ ዋጋ ጥናት መሰረት በሚገኘው የገበያ ዋጋ ጋር በአንጻራዊነት ሲታይ የቀረበው ዋጋ ከ10% (አስር በመቶ) የበለጠ ሲሆን እንደተጋነነ የጨረታ ዋጋ እንዲሁም የቀረበው ዋጋ ከ30% (ሰላሳ በመቶ) ያነሰ ሲሆን እንደተሰበረ የጨረታ ዋጋ ይቆጠራል፡፡
2) የምክር እና ከምክር ውጭ የሆነ የአገልግሎት ግዥን በተመለከተ የልማት ድርጅቱ በሚያከናውነው የገበያ ዋጋ ጥናት ጋር በአንጻራዊነት ሲታይ የቀረበው ዋጋ ከ10% (አስር በመቶ) የበለጠ ሲሆን እንደተጋነነ የጨረታ ዋጋ እንዲሁም የቀረበው ዋጋ ከ20% (ሃያ በመቶ) ያነሰ ሲሆን እንደተሰበረ የጨረታ ዋጋ ይቆጠራል፡፡
3) የግንባታ ግዥን በተመለከተ በተጫራቹ የቀረበው የጨረታ ዋጋ ከምህንድስና ግምት ዋጋ ጋር በአንጻራዊነት ሲታይ የቀረበው ዋጋ ከ15% (አስራ አምስት በመቶ) የበለጠ ሲሆን እንደተጋነነ የጨረታ ዋጋ እንዲሁም በተጫራቹ የቀረበው የጨረታ ዋጋ ከምህንድስና ግምት ዋጋ ጋር በአንጻራዊነት ሲታይ የቀረበው ዋጋ ከ20% (ሃያ በመቶ) ያነሰ ሲሆን እንደተሰበረ የጨረታ ዋጋ ይቆጠራል፡፡
4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1፣ 2 እና 3 መሰረት ከተጫራቹ የቀረበው ዋጋ የተጋነነ ሆኖ ሲገኝ የልማት ድርጅቱ ውል ከመፈረሙ በፊት ጨረታውን ወይም የመጫረቻ ሰነድን በማናቸውም ጊዜ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ውድቅ ማድረግ አለበት፡፡
5) የልማት ድርጅቱ በዚህ መመሪያ በተቀመጠው መሠረት ተጨማሪ ምርመራ ሳያከናውን የቀረበው የጨረታ ዋጋ የተሰበረ በመሆኑ ምክንያት ብቻ ተጫራቹን ከውድድሩ ውጭ ማድረግ የለበትም፡፡

6) የልማት ድርጅቱ በቀረበው የጨረታ ዋጋ ላይ ተጨማሪ ምርመራ ለማድረግ እንዲያስችለው የተሰበረ የጨረታ ዋጋ ያቀረበው ተጫራች ዝርዝር ማብራሪያ እና ተያያዥ ሰነዶች እንዲያቀርብ መጠየቅ አለበት፡፡

7) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 መሰረት የልማት ድርጅቱ የሚጠይቀው ማብራሪያ ሌሎች በመደበኛ የጨረታ ሰነዱ ከሚገለጹት ነጥቦች በተጨማሪ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ሊያካትት ይችላል፡፡

ሀ/ ተጫራቹ ባቀረበው ዋጋ ጥራቱንና የመ/ቤቱን ፍላጎት በሚያሟላ መልኩ ለማመጠናቀቅ የሚያስችለው አሳማኝ ምክንያት ያለው ስለመሆኑ፣

ለ/ ሥራውን ማከናወን ወይም አቅርቦቱን መፈጸም የሚያስችለው የተለየ ዘዴ ያለው ስለመሆኑ፣

ሐ/ ሥራውን ወይም አቅርቦቱን በዚህ ዋጋ ለመስራት ወይም ለመፈጸም የሚያስችለው የተለየ ምቹ ሁኔታ ወይም ሙያዊ መፍትሔዎች ያለው ስለመሆኑ፡፡

8) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 መሰረት ከተጫራቹ የቀረበውን ኃሳብ የማይቀበለው ከሆነ የልማት ድርጅቱ ውል ከመፈረሙ በፊት ጨረታውን ወይም የመጫረቻ ሰነድን በማናቸውም ጊዜ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ውድቅ ማድረግ አለበት፡፡

## 91. ከተጫራቾች ጋር ስለሚደረግ ድርድር

1) ጨረታ ከተከፈተ በኂላ የመወዳደሪያ ሀሳብን ለመገምገም በሚያስችሉ ነጥቦች ላይ ማብራሪያ ከመጠየቅና ውል ከመፈፀም ጋር የተያያዙ፣ በሁለት ደረጃ ጨረታ ልዩ ባህሪ ምክንያት፣ ጥራትን መሠረት ያደረገ የምክር አገልግሎት ግዥ በሚከናወንበት ወቅት እንዲሁም ዋጋን የማይነኩ ጥቃቅን ጉዳዮች ላይ ድርድር ማድረግ ይቻላል፡፡

2) የልማት ድርጅቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም ከዚህ በታች በተጠቀሱት ምክንያቶች የዋጋ ድርድር ሊያደርግ ይችላል፣

ሀ/ በጨረታ ውድድሩ የቀረበው አንድ ተጫራች ብቻ ሲሆን ወይም ከተወዳደሩት ተጫራቾች መካከል ለፋይናንሻል ውድድር ያለፈው አንድ ተጫራች ብቻ ሲሆን፣

ለ/ በጨረታው አሸናፊ የሆነው ደርጅት ውል ለመፈረም ወይም ውል ከገባ በኋላ ለማቅረብ ፍቃደኛ ካልሆነና በጨረታው ሁለተኛ የወጣው ድርጅት በመጀመሪያው አሸናፊ በሆነበት ዋጋ ለማቅረብ ፍቃደኛ ካልሆነ፣

ሐ/ በጨረታው አሸናፊ የሆነው ድርጅት ዋጋ ከወቅታዊው ዋጋ አንጻር ከፍ ያለ ከሆነና ጨረታውን ከመሰረዝ የዋጋ ድርድር ማድረግ የተሻለ ጠቀሜታ እንዳለው ሲታመንና በልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ሲፈቀድ፣

## 92. ጨረታን ማፅደቅ

1) የልማት ድርጅቱ የጨረታ ግምገማውን የሚያከናውኑት የግዥ የሥራ ክፍል ወይም እንደአስፈላጊነቱ ጨረታ ለመገምገም የተቋቋመው ጊዜያዊ ቡድን በተጫራቾች የተሠጠው የጨረታ ዋጋ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ግምገማውን በማጠናቀቅ ውጤቱን ከአስተያየት ጋር ግዥውን ለማፅደቅ ስልጣን ለተሠጠው አካል ማቅረብ አለበት፡፡

2) በዚህ መመሪያ መሠረት ግዥውን እንዲያጸድቅ ሥልጣን የተሰጠው አካል ግዥው የግዥ አፈፃፀም ሥርዓትን የተከተለ እና የጨረታ ግምገማው በጨረታ ሰነዱ በተገለጸው መስፈርት መሠረት መሆኑን በማረጋገጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ውሳኔውም ከሚከተሉት አንዱ ሊሆን ይችላል፡-

ሀ/ የግምገማው ሪፖርቱን ሙሉ በሙሉ በመቀበል ቀጣይ አፈፃፀሞች እንዲከናወኑ መፍቀድ፣

ለ/ ሪፖርቱን ባለመቀበል ግምገማው እንዲስተካከልና እንደገና እንዲከናወን ማድረግ፣ ወይም

ሐ/ በዚህ የአፈጻጸም መመሪያ መሰረት ጨረታን ለመሰረዝ የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎች ከተሟሉ ግዥው እንዲሰረዝ፣

3) ግዥውን የሚያፀድቀው አካል አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በቀረበው የግምገማ ሪፖርት ላይ ግምገማውን የሰራው ቡድን ወይም ኮሚቴ ማብራሪያ እንዲሰጠው ሊያደርግ ይችላል፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 (ለ) ላይ በተገለጸው መሠረት ግዥውን የሚያፀድቀው አካል የቀረበውን የግምገማ የውሳኔ ኃሳብ ያልተቀበለ ከሆነ ምክንያቱን በመግለጽ ከዚህ በፊት ግምገማውን ላከናወነው ቡድን እንዲመለስ የሚያደርግ ሲሆን ገምጋሚ ቡድኑም ከግዥ አጽዳቂው በተሠጠው አቅጣጫ መሠረት ግምገማውን እንደገና አከናውኖ የተስተካከለውን ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተመለከተው ቢኖርም ገምጋሚ ቡድኑ ወይም ማንኛውም ገምጋሚ ቡድን አባል የግዥ አፅዳቂ አካሉ በሰጠው አቅጣጫ ወይም በግምገማ ውጤት ላይ የማይስማማ ከሆነ በግምገማ ሪፖርቱ ላይ ያልተስማማበት ሀሣብ ተገልፆ የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ በሰጠው ውሳኔ መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

6) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በጨረታው ውጤት ላይ በሚቀርብ አቤቱታ መነሻነት በአጽዳቂ ኮሚቴው እና በልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ መካከል የሀሳብ ልዩነት ቢፈጠር የበላይ ኃላፊ ውሳኔ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡ :

## 93. ድህረ ግምገማ

1) የልማት ድርጅቱ እንደ አስፈላጊነቱ ከአሸናፊው ድርጅት ጋር የውል ስምምነት ከመግባቱ በፊት የተመረጠው ተጫራች ውሉን በአጥጋቢ ሁኔታ ለመፈጸም የሚያስችል ብቃት እንዳለው ለማረጋገጥ ድርጅቱ ያከናወናቸውን ልምድ፣ አደረጃጀት፣ ህጋዊነት፣ የፋይናንስና የቴክኒክ አቋም በመጫረቻ ሰነዱ ላይ በተቀመጠው መሠረት መሆኑ በድህረ ግምገማ ሊረጋገጥ ይችላል፡፡

2) የልማት ድርጅቱ ለድህረ ግምገማው የሚመረጡ መስፈርቶች አስቀድሞ በጨረታ ሰነዱ ውስጥ መቀመጥ ያለባቸው ሲሆን ለግዥው አስተዋጽኦ የሚኖራቸው መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

3) በድህረ-ብቃት ግምገማ ወቅት ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበ ተጫራች የድህረ ግምገማ መስፈርቱን የማያሟላ ከሆነ ሆኖ ከተገኘ የልማት ድርጅቱ በሁለተኛ ደረጃ ለወጣው ተጫራች ተመሳሳይ የሆነ የድህረ-መረጣ ብቃት ማረጋገጫ ግምገማ ያደርጋል፡፡

## 94. የጨረታ ውጤትን እና አሸናፊነት ማሳወቅ

1) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የጨረታውን ዝርዝር ውጤት በጽሁፍ ወይም በኤሌክትሮኒ ዘዴ ወይም ድረ ገጽ ለተጫራቾች የሚገልጽ ሲሆን በተመሳሳይ ጊዜ የልማት ድርጅቱን ድረ-ገጽ በመጠቀም ለህዝብ ይፋ ያደርጋሉ፡፡

2) የጨረታው ውጤት ተጫራቾች ቅሬታ ካላቸው ለማቅረብ በሚያስችል መልኩ በዝርዝር መገለጽ አለበት፡፡

3) ለአሸናፊው ተጫራች ውል እንዲፈርም የሚላክለት የአሸናፊነት ማስታወቂያ የሚከተሉትን ያካተተ መሆን አለበት፡-

   ሀ/ የልማት ድርጅቱ በተጫራቹ የቀረበውን የመጫረቻ ሐሳብ የተቀበለ መሆኑን፣

   ለ/ ውሉ የሚፈጸምበትን ጠቅላላ ዋጋ፣

   ሐ/ የማስረከቢያውን የመጨረሻ ቀን ፣

   መ/ ተጫራች ውሉን ለመፈረም ፈቃደኛ ካልሆነ በህጉ መሠረት የሚያስከትለውን ተጠያቂነት፣

   ሠ/ ሌሎች በጨረታ ሰነድ ለይ የተጠቀሱ አስፈላጊ ነጥቦች፣

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ለተጫራቹ የሚላከው የአሸናፊነት ማስታወቂያ በልማት ድርጅቱ እና በተጫራቹ መካካል እንደውል ሆኖ ሊያገለግል አይችልም፡፡

5) በጨረታው አሸናፊ የሆነው ተጫራች ውል ለመፈረም ፈቃደኛ ካልሆነ ወይም ውል ቢፈርምም የውል ማስከበሪያ ለማስያዝ ካልቻለ ወይም ውል ከገባ በኂላ በውል ስምምነቱ መሰረቱ ለማቅረብ ፈቃደኛ ካልሆነ የልማት ድርጅቱ በቅድሚያ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ በመገምገም፣ በጨረታው ሁለተኛ የወጣውን ተጫራች በጨረታው አሸናፊ ዋጋ ወይም በጨረታው አሸናፊ ዋጋ ለማቅረብ ፍቃደኛ ካልሆነ የዋጋ ድርድር በማድረግ በሚደረስበት ዋጋ አሸናፊ ማድረግ ወይም አዲስ ጨረታ ማውጣት ይችላል፡፡

6) የልማት ድርጅቱ የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን ካረጋገጠ ተወዳዳሪዎች ያስያዙትን የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ተመላሽ ማድረግ አለበት፡፡

ሀ/ ከአሸናፊ ተጫራቹ ጋር ውል ተፈርሞ ተጫራቹ የውል ማስከበሪያ ዋስትና ያቀረበ ከሆነ፣

ለ/ የጨረታ ማስከበሪያውን የመጠቀሚያ ጊዜ ለማራዘም ፈቃደኛ ያልሆነ ተጫራች የጨረታ ማስከበሪያ ፀንቶ መቆያ ጊዜ ያበቃ ከሆነ፣

95. **ጨረታን ስለመሰረዝ**

1) በአዋጁ አንቀጽ 26 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ጨረታን መሰረዝ ይችላል፡፡

ሀ/ የቀረቡት ተጫራቾች በጨረታ ሰነዱ ላይ የተቀመጠውን ዝቅተኛ መስፈርት የማያሟሉ ከሆኑ፣

ለ/ የወጣው ዝርዝር የጨረታ ሰነድ ወይም መግለጫ ጉድለት ያለበት መሆኑ ሲረጋገጥ ወይም በጨረታ ሠነዱ ላይ ለውጥ ማድረግ በርካታ ተወዳዳሪዎችን ማግኘት የሚያስችል መሆኑ ሲታመን፣

ሐ/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 90(2) በተደነገገው መሰረት የዋጋ ድርድር ተደርጎ ስምምነት ላይ መድረስ ካልተቻለ፣

መ/ የቀረበው አንድ ተጫራች ብቻ ሲሆንና ይህን ተጫራች በብቸኝነት እንዲቀርብ ያስቻለው በዚህ መመሪያ የተዘረጉትን ሥርዓቶች ያልጠበቀ አሠራር መኖሩ ሲረጋገጥ፣

ሠ) ጨረታው አሸናፊ የሆነው ተጫራች የሰጠው ዋጋ የልማት ድርጅቱ ለግዥው ከያዘው በጀት በላይ ሲሆንና ከአሸናፊው ድርጅት ጋር ድርድር ተደርጎ ስምምነት ላይ ካልተደረሰ ወይም የበጀቱን ልዩነት ከሌላ ምንጭ ማሟላት የማይቻል ከሆነ፣

2) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተመለከተው መሠረት ጨረታን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ሲሠርዙ ምክንያቱን የሚገልፅ ማስታወቂያ ለተወዳዳሪዎች ወይም ለተጫራቾች ወዲያውኑ ማሳወቅ አለባቸው፡፡

3) ጨረታውን ውድቅ የማድረግ ውሳኔው የተሰጠው ጨረታው ከመከፈቱ በፊት ከሆነ የመጫረቻ ሠነዱ ሳይከፈት ለተጫራቾች ተመላሽ ይሆናል፡፡

## ምዕራፍ ስምንት
## የውል አስተዳደር

### 96. የውል አጠቃላይ ድንጋጌዎች

1) በልማት ድርጅቶች የሚፈጸም ማንኛውም የግዥ ውል ወይም የውል ማሻሻያ በጽሑፍ መሆን አለበት፡፡
2) ውሉ በግዥ ፈፃሚው የመንግሥት የልማት ድርጅትእና በአቅራቢው ሙሉ ስምምነት ላይ የተመሰረተ ሲሆን ከዚህ በፊት በተዋዋዮቹ ወገኖች መካከል የነበሩት ሁሉም ግንኙነቶች፣ ድርድሮችና ስምምነቶች በዚህ በውል ስምምነቱ ይተካሉ፡፡
3) በውሉ ላይ በተለየ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የሚገቧቸው ውሎች በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ሕጐች መሠረት የሚገዛና የሚተረጐም ይሆናል፡፡

### 97. የውል አዘገጃጀት

4) የሚዘጋጀው የውል ሰነድ የጨረታ ሰነድ ክፍል የሆኑትን አጠቃላይ እና ልዩ የውል ሁኔታዎችን እና ሌሎች የውሉ አካል የሆኑ ሰነዶችን ያካተተ መሆን አለበት፡፡
5) የሚዘጋጀው የውል ሰነድ የመንግሥት ልማት ድርጅቱንናና የአቅራቢውን ግዴታና ኃላፊነት በግልጽ ያመላከተና በመንግሥት ልማት ድርጅቱ እና አቅራቢው ላይ የሚጣሉ ግዴታዎች ህጋዊ መሠረት ያላቸውና ሊፈጸሙ የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡
6) አቅራቢው በውል ሰነዱ ላይ የሚሰጠው አስተያየት በተዋዋይ ወገኖች የጋራ ስምምነት ሲደረስበት የውል ቃላትና ሐረጎች ውስጥ ሊካተት ይገባል፡፡

### 98. የውል ቅድመ ሁኔታዎች

የልማት ድርጅቱ ውል ከመፈረሙ አስቀድሞ የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡-

ሀ/ አቅራቢው ውል ለመፈረም በአዋጁና በመመሪያው የተቀመጡ የብቃት መስፈርቶችን ለማሟላት የሚያስችል ወቅታዊ ብቃት ያለው መሆኑን፣

ለ/ የሚፈጸመው ግዥ ዓይነትና መጠን፣ የውል ዋጋ፣ የአቅርቦት ጊዜ፣ በቂ በጀት እና ለውሉ አፈጻጸም ውጤታማነት እና ቅልጥፍና የሚያስፈልጉ ሌሎች ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸውን፣

## 99. ውል መፈረም

1) የመንግሥት የልማት ድርጅትየጨረታው አሸናፊ ከሆነው ተጫራች ጋር ለዚሁ ዓላማ ተብሎ የተዘጋጀውን እና ስምምነት ላይ የተደረሰባቸውን የውል ቃሎች እና ልዩ ሁኔታዎች የያዘውን የውል ሰነድ መፈራረም አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው ቢኖርም አሸናፊው ድርጅት ባለው አሰራር መሰረት የራሱ የሆነ የውል ሰነድ የሚኖረው ከሆነና በውል ሰነዱ መሠረት ውል እንዲገባ የሚያስገደድ ከሆነ በአቅራቢው በተዘጋጀው መሠረት ውል ሊፈርም ይችላል፡፡

3) የልማት ድርጅቱ እና በአሸናፊው ተጫራች መካከል ውል ካልተፈረመ በስተቀር የጨረታው አሸናፊ በመገለፁ ብቻ ውል እንደተፈረመ አይቆጠርም፡፡

4) የልማት ድርጅቱ እና በአሸናፊው ተጫራች መካከል የሚፈረመው ውል የጸና የሚሆነው ሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች ስምምነታቸውን በፊርማ ሲያረጋግጡ ብቻ ነው፡፡

5) ጨረታውን ያወጣው የልማት ድርጅት የጨረታውን ወይም የቅሬታውን ውጤት ለተጫራቾች ከገለጸበት ቀን ጀምሮ 5 (አምስት የሥራ ቀናት) ከመሙላቱ በፊት የግዥ ውል መፈጸም የለበትም፡፡

6) የጨረታ አሸናፊው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) ላይ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ከተጠናቀቀ በኋላ ባሉት አስር የሥራ ቀናት ውስጥ ቀርቦ ውሉን መፈረም አለበት፡፡

7) የልማት ድርጅቱ እና በአሸናፊው ተጫራች መካከል የሚደረገው ውል የሁለቱን ወገኖች ኃላፊነት በግልፅ ማመልከት ያለበት ሲሆን፣ የሚከተሉትን ጉዳዮች በተጨማሪነት ያካተተ መሆን ይኖርበታል፡-

ሀ/ በውሉ የሚቀርበው ዕቃ፣ የግንባታ ዘርፍ ስራ ወይም የምክር እና ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎቶች ዓይነት፣ ጥራት፣ ብዛት፣ የሚቀርብበት አኳኋን ወይም የማስረከቢያ ጊዜውን፣ የሚከፈለውን አጠቃላይ እና የነጠላ ዋጋ መጠን፣ የአከፋፈል ሁኔታ እና የክፍያ ጊዜውን፣

ለ/ ከሦስተኛ ወገን የሚገኙ አገልግሎቶችን እንደ ትራንስፖርት፣ ኢንሹራንስ፣ ትራንዚት እና የመሳሰሉ ተግባራትን የመከታተል እና የመፈፀም ኃላፊነት የማን እንደሚሆን መጠቀስ ያለበት ሲሆን ኃላፊነቶቹም በተሻለ ብቃት ሊፈፅማቸው በሚችል አካል እንዲሰሩ መደረግ ይኖርበታል፡፡

ሐ/ አቅራቢው በመጫረቻ ሰነዱ ላይ ያመለከተው የዋጋ ቅናሽ ወይም ሌሎች ሁኔታዎችን እና አፈጻጸማቸውን በውሉ ላይ በግልጽ ያመላከተ መሆን አለበት፡፡

መ/ በውል አፈጻጸም ወቅት የሚነሱ አለመግባባቶች የሚፈቱበትን አካሄድ መገለጽ አለበት፡፡

ሠ/ ከውጭ ሀገር ለሚቀርቡ አቅርቦቶች ከጠቅላላው የውሉ መጠን ውስጥ በውጭ ሀገር ገንዘብ እና ከሀገር ውስጥ ለሚቀርቡ አቅርቦቶች በብር ሊከፈለው የሚገባው የገንዘብ መጠን ድርሻ ተለይቶ መገለጽ ይኖርበታል፣

ረ/ የውል አካል የሆኑ የግዥ ሰነዶች እና በመካከላቸው ልዩነት ሲኖር የበላይነት የሚኖረውን ሰነድ፣

ሰ/ ለውል አፈጻጸም የተያዘው የውል ማስከበሪያ ሊወረስ የሚችልባቸውን ሁኔታዎች፣

ሸ/ አቅራቢው በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ዕቃውን፣ ምክር አገልግሎቱን፣ የግንባታ ዘርፍ ስራውን ወይም አገልግሎቱን አጠናቆ ባያስረክብ፣ላዘገየበት ጊዜ የሚወስደውን እርምጃ፣ እንዲሁም

ቀ/ የልማት ድርጅቱ እና በአቅራቢው መካከል ሊኖር የሚገባውን የግንኙነት አግባብ፣ እና ሌሎች ለውሉ አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮች፡፡

## 100. የተዋዋይ አካላት ኃላፊነት

1) በዚህ የአፈጻጸም መመሪያ እና በውል ሰነዱ ላይ የተገለጹ መብትና ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆኖ አቅራቢው የሚከተሉት ኃላፊነቶች አለበት፡፡

ሀ/ ዕቃውን፣ አገልግሎቱን ወይም የግንባታ ስራውን በውሉ ላይ በተገለጸው ዓይነትና መጠን፣ የጥራት ደረጃ፣ እንዲሁም ሌሎች ግዴታዎችን በውሉ ጊዜ ውስጥ መፈጸም፣

ለ/ በውሉ አፈጻጸም ወቅት ለሚያከናውናቸው ተግባራት ሙሉ ኃላፊነት መውሰድ፣

ሐ/ በኢትዮጵያ ውስጥ በስራ ላይ ያሉ ተፈጻሚ የሆኑ ህጎች ማክበርና በዚህ አፈጻጸም መመሪያ እና በውሉ ለተቀመጡ የሥነ ምግባር ደንቦች ተገዥ መሆን፣

2) በዚህ መመሪያ እና በውል ሰነዱ ላይ የተገለጹ መብትና ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የልማት ድርጅቱ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

ሀ/ ለውሉ ቅልጥፋና እና ውጤታማነት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከሚመለከታቸው አካላት ድጋፎችን፣ እገዛዎችንና ፈቃዶችን መጠየቅና እገዛ ማድረግ፣

ለ/ አቅራቢው በውሉ መሠረት ግዴታውን መወጣቱን ሲያረጋግጥ ተገቢውን ክፍያ በወቅቱ መፈጸም፣

ሐ/ አቅረቢው የውል ግዴታውን እየተወጣ እንደሚገኝ የሚያረጋግጡ ማስረጃዎችን ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ መስጠት፣ እና

መ/ የውል አፈጻጸምን አስመልክቶ ከአቅራቢው ለሚቀርብ ማንኛውም ጥያቄ በህጉና በውሉ መሠረት ፈጣን ምላሽ መስጠት፡፡

## 101. ውልን ይፋ ስለማድረግ

1) ሚስጥራዊ ግዥዎች ካልሆኑ በስተቀር የልማት ድርጅቱ በአዋጁ አንቀጽ 63 መሠረት ዋና ዋና የውል መረጃዎችን በልማት ደርጅቱ ድረ-ገጽ ለህዝብ ይፋ ማድረግ አለበት፡፡

2) በልማት ድርጅቱ ድረ-ገጽ ይፋ የሚሆነው ውል ቢያንስ የሚከተሉትን ሁኔታዎች የሚገልጽ መሆን ይኖርበታል፡፡

ሀ/ የውሉ ርዕስ፣

ለ/ የግዥውን ዘዴ፣ ዓይነትና መጠን፣

ሐ/ የተጠቃሚ ባለቤትነት መብት ያላቸውን ሰዎች፣

መ/ የአቅራቢውንና የልማት ድርጅቱን ሙሉ ስምና አድራሻ፣ እና

ሠ/ የግዥውን የውል ዋጋ፣ ውሉ የሚጀመረበት እና የሚጠናቀቅበትን ጊዜ፣

## 102. ውል ስለማሻሻል

1) በውል አፈጻጸም ወቅት እንደሁኔታው የውል ማሻሻያ ማድረግ የሚቻል ሲሆን የሚደረገው የውል ማሻሻያ የልማት ድርጅቱን ጥቅም የማይጎዳ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡
2) ማንኛውም በውሉ ላይ የሚደረጉ ማሻሻዎች በፅሑፍና በተዋዋይ ወገኖች ሥልጣን በተሰጣቸው አካላት መፈፀም አለበት፡፡ በፅሑፍ የሚደረጉት የውል ለውጦች ለቀጣይ አፈጻጸም የዋናው ውል ሰነድ አካል ተደርገው ይቆጠራሉ፡፡
3) በውል አፈጻጸም ወቅት በሚቀርበው ዕቃ ወይም ምርት ላይ በቴክኖሎጂ ምክንያት የሚፈጠሩ ለውጦች በውሉ ላይ ከተገለጸው የጥራት ደረጃ ያላነሰ እስከሆነ ድረስ የልማት ድርጅቱ ወይም በአቅራቢው ጥያቄ መነሻነት በውል ማሻሻያ ሊካተቱ ይችላሉ፡፡

## 103. የውል ማስከበሪያ

1) የልማት ድርጅቱ በዋጋ ማቅረቢያ፣ የኪራይ አገልግሎት ግዥ፣ ከልማት ድርጅት የሚፈጸም ግዥ እና በለቀማ ከሚፈጸም ግዥ በስተቀር ለማናቸውም ሌላ ግዥ የውል ማስከበሪያ መጠየቅ አለበት፡፡ ሆኖም አቅራቢው የውል ማስከበሪያ ለማስያዝ ፈቃደኛ ካልሆነ እና ግዥውን ለመፈፀም ሌላ አማራጭ ከሌለ፣ የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት የውል ማስከበሪያ ላይጠይቅ ይችላል፡፡
2) የዚህ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ቢኖርም ለዋጋ ማቅረቢያ፣ ለኪራይ አገልግሎት ግዥ እና ለለቀማ ግዥ የልማት ድርጅቱ በዚህ መመሪያ አባሪ 5 መሰረት የውል ማስከበሪያ መተማመኛ ቅጽ ሊያስፈርም ይችላል፡፡
3) የጨረታው አሸናፊ ድርጅት ከልማት ድርጅቱ ጋር ውል ከፈረመበት ቀን ጀምሮ በ10 (አሥር) ቀናት ውስጥ የውሉን ጠቅላላ ዋጋ ቢያንስ አስር በመቶ (10%) የልማት ድርጅቱ በጨረታ ሰነዱ ላይ በሚወስነው የዋስትና ዓይነት የውል ማስከበሪያ ማስያዝ አለበት፡፡
4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው ቢኖርም የግዥው መጠን ከፍተኛ እና አቅርቦቱ ቀጣይነት ያለው ሲሆን አቅራቢዎች የሚያስይዙት የውል ማስከበሪያ ዋስትና

ከጠቅላው ግምታዊ ውል መጠን ላይ የሦስት ወሩ የውል መጠን ከ10% ያላነሰ እንዲሆን በልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ሊወሰን ይችላል፡፡

5) አቅራቢው በውሉ መሠረት ግዴታውን ሳይወጣ ቢቀር ለመውረስ እንዲያስችለው ተጫራቹ የሚያቀርበው የውል ማስከበሪያ ውሉ ፀንቶ ከሚቆይበት ጊዜ ቢያንስ ለተጨማሪ ሃያ ስምንት (28) ቀናት ፀንቶ መቆየት አለበት፡፡

6) የልማት ድርጅቱ አቅራቢው በውሉ መሰረት አለመፈጸሙን ሲያረጋግጥ ያስያዘውን የውል ማስከበሪያ መውረስ ይችላል፡፡

7) በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች መካከል የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር የተያዘው የውል ማስከበሪያ አቅራቢው የውል ግዴታውን ሙሉ በሙሉ እንዳጠናቀቀ መመለስ አለበት::

## 104. የውልን አፈፃፀም መከታተል

1) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የውል አፈፃፀምን የሚከታተል የሥራ ክፍል መለየት ወይም የውል ክትትል በተለያዩ አካላት በቅንጅት የሚፈፀም በሚሆንበት ወቅት እነዚህ አካላት ተግባራቸውን በግልፅ እንዲያውቁ ማድረግ አለባቸው፡፡

2) የውል አፈፃፀምን የሚከታተለው የልማት ድርጅቱ የሥራ ክፍል አቅራቢው በውሉ መሠረት የሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት በውሉ ላይ በተገለፀው መሠረት እየተከናወኑ የሚገኙ መሆኑን መከታተል አለበት፡፡

3) በውል አፈፃፀም ክትትል ወቅት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የሚከተሉትን ተግባራት መፈፀም አለባቸው፡፡

   ሀ/ ተቀባይነት የሚኖራቸውን በባንክ የተረጋገጠ የክፍያ ሰነድ ማስተካከያ ጥያቄዎች ተቀብሎ አፋጣኝ ምላሽ መስጠት፣

   ለ/ ተገቢው አገልግሎት ከመገኘቱ በፊት እንደአግባብነቱ የውል ማስከበሪያ፤ በባንክ የተረጋገጠ የክፍያ ሰነድ፤ የጥራት ዋስትና መጠቀሚያ ጊዜዎች እንዳያልፉ ጥንቃቄ እና ክትትል ማድረግ፣

   ሐ/ የግንባታ ስራዎች በተያዘላቸው ጊዜ ገደብ ውስጥ መገንባታቸውን፣ የዕቃ አቅርቦቶች እና አገልግሎቶች በውሉ ጊዜ ውስጥ ለመከናወናቸው ክትትል መደረጉን እና ሪፖርት መቅረቡን፣

   መ/ ከውል አፈፃፀም ጋር በተያያዘ ከአቅራቢዎች ምንም ዓይነት የይገባኛል ጥያቄዎች እንዳይፈጠሩ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ፣

## 105. የቅድመ ክፍያ አከፋፈል

1) በግዥ አፈፃፀም እንደአስፈላጊነቱ ከውሉ ጠቅላላ ዋጋ እስከ ሰላሳ በመቶ (30%) (ሠላሣ ከመቶ) የሚደርስ የቅድሚያ ክፍያ ሊሰጥ ይችላል፡፡ የሚሰጠው የቅድሚያ ክፍያ መጠን በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ እና በልዩ የውል ሁኔታ ላይ መገለፅ አለበት፡፡

2) አቅራቢዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ከሚጠይቁት የቅድሚያ ክፍያ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና እንደአቅራቢው ምርጫ ከታወቀ ባንክ የሚሰጥ የተረጋገጠ የክፍያ ማዘዣ ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና ማቅረብ አለባቸው፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ለግንባታ ዘርፍ ሥራ በተደረገ ውል መሠረት ለሚፈፀም የቅድሚያ ክፍያ ሊደረግ የሚችለው በውል ሰጪ እና በውል ተቀባዩ የጣምራ ፊርማ ሲሆን የቅደመ ክፍያው አጠቃቀመን በሚመለከተ የተለየ ስምምነት የሚስፈልገው ሰሆን፣

    ሀ/ በባንክ ሂሣቡ ከተቀመጠው ገንዘብ ላይ ለሥራ ተቋራጩ ተቋሙ ክፍያ የሚፈፀመው ቀደም ሲል በወሰደው ገንዘብ ተገቢውን ሥራ የሰራ መሆኑ ሲረጋገጥ መሆኑን፣

    ለ/ በቅድሚያ ክፍያ መልክ ከሚከፈለው ገንዘብ ውስጥ ለመንገድ ሥራ የሀገር ውስጥ ተቋራጮች እስከ ስልሳ በመቶ (60%) እንዲሁም ለሕንጻ ሥራ የሀገር ውስጥ ተቋራጮች እስከ ሰላሳ በመቶ (30%) ለመሣሪያ መግዣ ማዋል የሚችሉ መሆኑን፣ የሚገልጹ አንቀጾችን ሊይዝ ይችላል፡፡

4) የሚከተሉት ሁኔታዎች መኖራቸውን ሲረዳ የሀገር ውስጥ ሥራ ተቋራጮች በቅድሚያ ክፍያ መልክ ከተሰጣቸው ገንዘብ ውስጥ ከፊሉን ለመሣሪያ መግዣ እንዲያውሉ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

    ሀ/ የሥራ ተቋራጩ በቅድሚያ ክፍያ መልክ በወሰደው ገንዘብ የገዛውን መሣሪያ በውሉ መሠረት ፕሮጀክቱ ከመጠናቀቁ በፊት ለዕዳ መያዣነት

የማያውል እና በማናቸውም መልክ ለሦስተኛ ወገን የማያስተላልፍ ለመሆኑ ማረጋገጫ የሚያቀርብ ከሆነ፣

ለ/ የሥራ ተቋራጩ የቅድሚያ ክፍያ አከፋፈል ስምምነት ከመፈረሙ በፊት በቅድሚያ ክፍያ መልክ በሚወስደው ገንዘብ የሚገዛቸውን መሣሪያዎች ዓይነት ለአሠሪው የመንግሥት የልማት ድርጅትተቆጣጣሪ መሐንዲስ አቅርቦ መሣሪያዎቹ ለሥራው አስፈላጊ መሆናቸው ከተረጋገጠ፣

ሐ/ መሣሪያዎቹ ከፕሮጀክቱ ባለቤት ፈቃድ ውጪ ከፕሮጀክቱ ወደ ሌላ ቦታ እንደማይንቀሳቀሱ ማረጋገጫ ከቀረበ፣

5) ግዥ ፈፃሚው የመንግሥት የልማት ድርጅትበዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት ተቋራጩ በተከፈለው የቅድመ ክፍያ መሣሪያውን ስለመግዛቱ ህጋዊ ማስረጃ እንዲያቀርብ በማድረግ ማረጋገጥ አለበት፡፡

6) የሀገር ውስጥ ሥራ ተቋራጩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 በተመለከተው መሠረት በተከፈለው የቅድሚያ ክፍያ ለግንባታ ሥራው የሚያስፈልጉ መሣሪያዎቹን ወደ ፕሮጀክቱ ቦታ ካላጓጓዘ በውሉ መሠረት ሊከፈለው የሚገባው የሚቀጥለው ክፍያ አይፈፀምለትም፡

7) በአቅራቢዎች የተወሰደው የቅድሚያ ክፍያ ገንዘብ በውሉ መሠረት በየደረጃው ከሚዘጋጁት የክፍያ ምስክር ወረቀቶች ወይም በየደረጃው ከሚፈፀሙ አቅርቦቶች ሂሳብ ላይ እየተቀነሰ እንዲመለስ መደረግ አለበት፡፡

8) በዚህ አንቀጽ ድንጋጌ ከተቀመጠው የገንዘብ መጠን በላይ የቅድሚያ ክፍያ ለመክፈል አሳማኝ ምክንያት ሲኖር እና ግዥውን ለመፈፀም ሌላ አማራጭ ከሌለ፣ የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት የቅድሚያ ክፍያው መጠን ከፍ ተደርጎ ሊከፈል ይችላል፡፡

## 106. የዋጋ ማስተካከያ

1) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የሚከተሉት ሁኔታዎች መኖራቸውን ሲረዱ 1 ዓመትና  እና ከዚህ በላይ ለሚቆዩ ለግንባታ ስራዎች፣ እንዲሁም 6 ወራት እና

ከዚያ በላይ ለሚቆይ በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈፀም ግዥ የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ የሚችል ሲሆን አስቀድሞ በጨረታ ሰነዱ ላይ ማመልከት አለበት፡፡

ሀ/ ለግንባታ ሥራ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረገው ውሉ ተፈጻሚ መሆን ከጀመረበት ከ6 ወራት በኋላ ሲሆን፣በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈጸም ግዥ ደግሞ ውሉ ተፈፃሚ መሆን ከጀመረበት ከ3 ወራት በኋላ ለሚኖረው የዋጋ ለውጥ ነው፡፡

ለ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ) የተገለጸው ቢኖርም ዋጋቸው በከፍተኛ ሁኔታ ተለዋዋጭ ለሆኑ ምርቶች ወይም አቅርቦቶች ወይም ዋጋ ለማስተካከል አሳማኝ ሆነ ምክንያት ሲያጋጥም እና በልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ተቀባይነት ሲያገኝ ለግንባታ ሥራ የዋጋ ውሉ ተፈጻሚ መሆን ከጀመረበት ከ6 ወራት በፊት እንዲሁም በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈጸም ግዥ ደግሞ ውሉ ተፈፃሚ መሆን ከጀመረበት ከ3 ወራት በፊት የዋጋ ማስተካከያ ሊደረግ ይችላል፡፡

ሐ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ) መሠረት የዋጋ ማስተካከያ የሚደረገው ጊዜ እንደሁኔታው ከታወቀ አምራች ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በተደረገ ገበያ ዋጋ ጥናት በሚገኝ የገበያ ዋጋ መረጃ መሠረት ነው፡፡

2) የልማት ድርጅቱ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግባቸው ዕቃዎች ወይም አቅርቦቶች ለተካተቱበት ግዥ በሚያዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ላይ የሚከተሉትን ጨምሮ ሌሎች አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን ሁኔታዎች በግልጽ ማመልከት ይኖርበታል፡፡

ሀ/ ዋጋ ማስተካከያውን ተግባራዊ ለማድረግ ተወዳዳሪዎች ከመጫረቻ ሰነዳቸው ጋር ማቅረብ ያለባቸውን የመረጃ አይነት፣

ለ/ የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄው የሚቀርብባቸውን ሁኔታዎች፣ የአቀራረብ ዘዴውን እና ከዋጋ ማስተካከያ ጥያቄው ጋር ተያይዘው የሚቀርቡ ማስረጃዎችን ዓይነትና መጠን፣

ሐ/ ሌሎች ለዋጋ ማስተካከያው አፈጻጸም ይጠቅማል ተብሎ የሚታመንባቸውን መረጃዎች እና ተጫራቾች ሊከተሉት ይገባል የሚላቸውን አሰራሮች፣

3) የልማት ድርጅቱ በጨረታ ግምገማ ወቅት ለዋጋ ማስተካከያ ዓላማ የተቀመጡትን ቅድመ ሁኔታዎች ተጫራቾች መቀበላቸውን እና ያቀረቧቸው ማስረጃዎችም ተቀባይነት ያላቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

4) የልማት ድርጅቱ እና በጨረታ ውድድሩ አሸናፊ የሆነው ተጫራች በሚያደርጉት የውል ስምምነት ላይ የሚከተሉት እና ሌሎች ተገቢ ናቸው ተብሎ የታመነባቸው ሁኔታዎች በግልፅ እንዲካተቱ መደረግ አለበት፡፡

ሀ/ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግላቸውን ግብዓቶች በመጠቀም የሚመረቱ ዕቃዎችን ወይም አቅርቦቶችን ዝርዝር እና የማስተካከያውን አፈፃፀም፣

ለ/ ለዋጋ ማስተካከያው አፈጻጸም የልማት ድርጅቱ እና አቅራቢው የተስማሙበት የሰነድ ዓይነት እና ምንጭ፣

ሐ/ ለዋጋ ማስተካከያ የሚቀርበው ማስረጃ በውሉ ላይ በተገለፀው መሠረት መሆን እንዳለበት እና ከሌላ ምንጭ የሚመጣ መረጃ ተቀባይነት እንደማይኖረው፣

መ/ ለአቅራቢው የሚሰጠው የግዥ ትዕዛዝ የጠቅላላ ፍላጎቱን ግምታዊ ክፍፍል መሠረት ያደረገ እስከሆነ ድረስ አቅራቢው በውል ስምምነቱ መሠረት በወቅቱ ስራውን ወይም አቅርቦቱን ማከናወን ባለመቻሉ የሚፈጠረ የዋጋ መናር ማስተካከያ የሚደረግበት ስለመሆኑ፣

5) በማንኛውም ዕቃ እና አገልግሎት ላይ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ ጭማሪ ከውል ዋጋው ከሃያ በመቶ (20%) በላይ በሚሆንበት ወቅት በልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ውሰኔ መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

6) የልማት ድርጅቱ የዋጋ ማስተካከያ ለተፈቀደበት ማንኛውም ግዥ ከአቅራቢው የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄ ባይቀርብም ክፍያ ጥያቄ ሲቀርብለት የዋጋ ማስተካከያ እንዲደረግባቸው በውል ስምምነቱ በተፈቀዱ ግብዓቶች ላይ የዋጋ መቀነስ መኖር አለመኖሩን የማጣራትና የዋጋ ቅናሽ ካለም አስልቶ ከቀረበው የክፍያ ጥያቄ ላይ ከቀነሰ በኋላ መክፈል አለበት፡፡

7) የልማት ድርጅቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት ክፍያው ከመፈጸሙ በፊት የተስተካከለውን ዋጋ ለአቅራቢው በጽሑፍ ማሳወቅ ያለበት ሲሆን፣ይህም የውል ሰነዱ አካል ሆኖ ይቆጠራል፡፡

## 107. ለግንባታ ሥራ ግዥ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 126 የተገለጹት ዝርዝር ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ከግንባታ ስራ ግዥ ጋር በተያያዘ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ ከዚህ በታች የተገለጹትን አሠራሮች ተከትሎ በመደበኛ የጨረታ ሰነዱ ላይ የተመለከተውን ቀመር በመጠቀም የሚሰላ ይሆናል፡፡

ሀ/ ለግንባታ ሥራው የሚያስፈልጉ ዋና ዋና ግብዓቶችና በእያንዳንዱ ዋና ግብዓት ሥር ሊካተቱ የሚችሉ ዕቃዎችን ስብስብ መለየት፣

ለ/ በስራቸው የተለያዩ ዕቃዎች ስብስቦችን የያዙት ዋና ዋና ግብዓቶች፣ከግንባታ ስራው ጠቅላላ ግብዓቶች ውስጥ የሚኖራቸውን ድርሻ በማስላት የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግባቸውን እና የማይደረግባቸውን መወሰን፣

ሐ/ ጨረታው ከመዘጋቱ በፊት በሥራ ላይ ያለ የቅርብ ጊዜ ዋጋ ኢንዴክስ/ጠቋሚ አሃዝ በቀመሩ መሠረት የዋጋ ማስተካከያውን ለማስላት በመነሻነት ይወሰዳል፣

መ/ ለግንባታ ስራ ግዥ የዋጋ ልዩነት የሚሰላው በስራ ላይ ያለውን ወቅታዊ የዋጋ ኢንዴክስ/ጠቋሚ አሃዝን በመጠቀም በቀመሩ መሠረት ይሆናል፣

ሠ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (ሐ) እና (መ) መሰረት የዋጋ ማስተካከያ የሚደረገው ከታወቀ ገበያ ወይም በልማት ድርጅቱ የገበያ ጥናት በሚገኝ መረጃ መሠረት ብቻ ነው፡፡

ረ/ ለግንባታ ስራ ለሚደረገው የዋጋ ማስተካከያ ጭማሪ ከጠቅላላ የግንባታ ሥራው የውል ዋጋ ከ30% (ሠላሳ ከመቶ) በላይ ሲሆን በልማት ድርጅቱ የበላይ ኃለፊ ውሳኔ መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

ሰ/ የስራ ተቋራጩ በውል ስምምነቱ መሠረት መስራት ላልቻላቸው እና ዘግይተው ለተሰሩ የግንባታ ሥራዎች የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ የሚቻለው የግንባታ ሥራዎቹ መሰራት በነበረባቸው ወቅት በነበረው ዋጋ መሠረት ብቻ ይሆናል፡፡

## 108. በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈፀም ግዥ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ

ማንኛውም ከማዕቀፍ ስምምነት ግዥ ጋር በተያያዘ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ ከዚህ በታች የተገለጹትን አሠራሮች ተከትሎ በመደበኛ የጨረታ ሰነዱ ላይ የተመለከተውን ቀመር በመጠቀም የሚሰላ ይሆናል፡፡

ሀ/ በማዕቀፍ ስምምነት መሠረት ተፈፃሚ ለሚሆን ግዥ የሚቀርብ የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄ መቅረብ የሚኖርበት ስምምነቱ ስራ ላይ ከዋለ ከሶስት ወራት በኋላ ሊሆን ይገባል፡፡ሆኖም ከተጠቃሚ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የግዥ ትዕዛዝ ላልቀረበባቸው ዕቃዎች የዋጋ ማስተካከያ አይደረግም፡፡

ለ/ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግበትን ዕቃ ወይም አገልግሎት አስመልክቶ በጨረታው መክፈቻ ወቅት የነበረው የዋጋ መረጃ ከሚገኝበት ተቋም ወይም የታወቀ አምራች ወይም የልማት ድርጅቱ ያጠናው የገበያ ዋጋ እና የማዕቀፍ ስምምነቱ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግበት ጊዜ በማዕቀፍ ስምምነቱ ላይ መገለፅ አለበት፡፡

ሐ/ የልማት ድርጅቱ በሁለቱም ዋጋዎች መካከል ያለውን የዋጋ ልዩነት በማስላት ልዩነት በአቅራቢው ዋጋ ላይ እንዲጨምረ ወይም እንዲቀነስ በማድረግ የሚቀጥለው የዋጋ ማስተካከያ ጊዜ እስከሚደርስ ድረስ የተስተካከለውን ዋጋ ተፈፃሚ ማድረግ አለበት፡፡

መ/ አቅራቢው በውል ስምምነቱ መሠረት ማቅረብ ሲገባው በወቅቱ ላላቀረባቸው እና ዘግይተው ለቀረቡ አቅርቦቶች የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ የሚቻለው አቅርቦቶቹ መቅረብ በነበረባቸው ወቅት በነበረው ዋጋ መሠረት ብቻ ይሆናል፡፡

ሠ/ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረገው ለዚህ ዓላማ በተዘጋጀው ቀመር መሠረት ሲሆን ለመጀመሪያው ዋጋ ማስተካከያ የሚደረገው በጨረታ መክፈቻ ጊዜ እና የዋጋ ማስተካከያ በሚጠየቅበት ወቅት ባሉ የገበያ ዋጋዎች መካከል ያለውን ልዩነት በውል ዋጋው ላይ በመጨመር ወይም በመቀነስ ነው፡፡

ረ/ በቀጣይ የዋጋ ማስተካከያዎች ሲደረጉ ደግሞ እንደ መነሻ ዋጋ የሚወሰደው ቀደም ብሎ የዋጋ ማስተካከያ ወቅት የነበረውን ወቅታዊ ዋጋ እና የዋጋ ማስተካከያ በሚጠየቅበት ወቅት ባሉ የገበያ ዋጋዎች መካከል ያለውን ልዩነት አሁን ባለው የውል ዋጋው ላይ በመጨመር ወይም በመቀነስ ነው፡፡

ሰ/ የማዕቀፍ ግዥ አቅራቢዎች ቁጥር ከአንድ በላይ ሲሆኑና የሚያቀርቡት ዕቃ ምርት መለያ ወይም የንግድ ምልክት የተለያየ በሚሆንበት ጊዜ ለአቅራቢዎቹ የሚደረገው የዋጋ ማስተካከያ እያንዳንዱ አቅራቢ ውል የገባበት የንግድ ምልክት ገበያ ላይ ያመጣውን የዋጋ ልዩነት መሠረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡

## 109. ለምክር አገልግሎት ግዥ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ

ሀ/ የልማት ድርጅቱ 24 ወራት እና ከዚህ በላይ ለሚቆዩ የምክር አገልግሎት ግዥዎች፣ ከ12ኛው ወር ጀምሮ የዋጋ ማስተካከያ እንደሚደረግ አስቀድሞ በጨረታ ሰነዱ ላይ ማመልከት አለበት፡፡

ለ/ በምክር አገልግሎት ግዥ የውል አፈጻጸም ወቅት የአማካሪው ስህተት ባልሆነ ምክንያት የውል መፈጸሚያ ጊዜው በመራዘሙ ለአማካሪው የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን የልማት ድርጅቱ ሲያምንበት የዋጋ ማስተካከያ ሊያደርግ ይችላል፡፡

ሐ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (ሀ) ተገለጸው ቢኖርም ለአማካሪዎች የሚደረገው የዋጋ ማስተካከያ ከውሉ ጠቅላላ ዋጋ ከ20% (ሃያ ከመቶ) በላይ ሲሆን በልማት ድርጅቱ የበላይ ውሳኔ መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

መ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (ሀ) መሠረት የዋጋ ማስተካከያ የሚደረገው ከታወቀ ገበያ ወይም በልማት ድርጅቱ የገበያ ጥናት በሚገኝ መረጃ መሠረት ብቻ ነው፡፡

## 110. ርክክብ እና ፍተሻ

1) የልማት ድርጅቱ አቅራቢው የሚያቀርበው ዕቃ ወይም አገልግሎት ወይም የግንባታ ስራ በውሉ ላይ በተቀመጠው አግባብ ፍተሻ የተደረገበትና ተፈላጊውን የጥራት ደረጃ ያሟላ መሆኑን በማረጋገጥ መረከብ አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚቀርበው ዕቃ ወይም አገልግሎት ወይም የግንባታ ስራ በውሉ ላይ የተገለጸውን የጥራት ደረጃ የማያሟላ መሆኑ በልማት ድርጅቱ ከተረጋገጠ አቅራቢው በውሉ መሠረት መተካት ወይም ማስተካከል አለበት፡፡

## 111. ክፍያ ስለመፈጸም

1) አቅራቢው ለልማት ድርጅቱ የሚያቀርበው የክፍያ ጥያቄ በውሉ የተቀመጡ ተፈላጊ መረጃዎችን በማካተት ተገቢ የክፍያ መጠየቂያ ሰነድ በጽሑፍ ማያያዝ አለበት፡፡

2) የልማት ድርጅቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የውል ግዴታዎች መሠረት አቅራቢው ላቀረባቸው ዕቃዎችና ተያያዥ አገልግሎቶች ወይም የምክር አገልግሎት ወይም የግንባታ ሥራዎችን በውል ዋጋው መሠረት ለአቅራቢው ክፍያ ይፈጽማል፡፡

3) በውሉ ላይ በተለየ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር ግዥ የልማት ድርጅቱ ክፍያ መፈፀም የሚችለው በውሉ ውስጥ የተጠቀሱትን ግዴታዎች መሟላታቸውን ካረጋገጠ በኋላ ነው፡፡

4) የልማት ድርጅቱ የግንባታ ዘርፍ ስራ ግዥ ሲፈፅም ክፍያ የሚፈፀመው ግንባታውን የክንውን ደረጃ መሠረት አድርጎ እና የሚከተለውን አፈፃፀም ተከትሎ መሆን ይኖርበታል፡፡

ሀ/ ለግንባታ ዘርፍ ስራ ክፍያ የሚፈፀመው የስራውን ደረጃ ተከትሎ እንደ ስራው ውስብስብነት ለዚህ ዓላማ ከተቀጠረ አማካሪ ወይም ከልማት ድርጅቱ መሐንዲስ በሚሰጥ የክፍያ የምስክር ወረቀት መነሻነት ብቻ ይሆናል፡፡

ለ/ የክፍያ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ከሥራ ተቋራጩ ጥያቄ ሲቀርብ የቁጥጥር ስራውን የሚያከናውነው አማካሪ ወይም የልማት ድርጅቱ መሐንዲስ የምርመራውን ሥራ በተቻለ ፍጥነት ማጠናቀቅ ይኖርበታል፡፡

ሐ/ በክፍያ የምስክር ወረቀት መሠረት ከሚፈጸመው ከእያንዳንዱ ክፍያ ላይ ለግንባታ ሥራው ጥራት ዋስትና እንዲሆን በውሉ በሚገለጸው መጠን በመያዣ መልክ ተቀንሶ ይያዛል፡፡ በዚህ መልኩ ተቀንሶ የተያዘው ገንዘብ የሚለቀቅበት አግባብ በውሉ ይወሰናል፡፡

## 112. ውል ማጠናቀቅ

1) የልማት ድርጅቱ ከአቅራቢዎች ጋር የተፈረሙ ውሎች ተገቢውን ዕልባት በወቅቱ አግኝተው ውሉ መጠናቀቁን ማረጋገጥ አለበት፡፡ ለዚህም፡-

ሀ/ አቅራቢው በውል ስምምነቱ መሠረት የሚገባውን የግንባታ ዘርፍ ስራ፣ ዕቃ፣ የምክር ወይም ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎቶች አጠናቆ ማቅረቡን፣

ለ/ በውሉ መሠረት የተያዙ ዋስትናዎች፣ የጥራት ዋስትናዎች ተገቢው ክትትል የተደረገባቸው እና አስፈላጊ በሆነ ወቅት ውሳኔ የተሰጠባቸው መሆኑን፣

ሐ/ በውሉ መሠረት ለአቅራቢዎች ሊከፈል የሚገባ ክፍያ የተጠናቀቀ መሆኑን፣ ለተከፈሉ ክፍያዎች ሁሉ በውሉ መሠረት አገልግሎት መገኘቱን፣

መ/ ከሶስተኛ ወገን ማለትም ከኢንሹራንስ ኩባንያዎች፣ ከአጓጓዦች፣ ከጉምሩክ ባስልጣን፣ ከጉምሩክ አስተላላፊዎች፣ ከባንክ እና ከከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎቶች ሰጪዎች ጋር የተያያዙ የልማት ድርጅቱ ጥቅሞች መከበራቸውን እና ግዴታዎች የተፈፀሙ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፣

2) የልማት ድርጅቱ ከአቅራቢው እና ከሦስተኛ ወገን ጋር ያሉ ያልተጠናቀቁ ሒሳቦችን በመዝጋት እንደአስፈላጊነቱ የውል አፈጻጸም ግምገማ ማድረግ አለበት፡፡

## 113. የጉዳት ካሳ

1) የልማት ድርጅቱ በዚህ መመሪያ መሠረት ለዘገየ የውል አፈጻጸም በሚከተለው መሠረት እርምጃ መውሰድ አለበት፡-

ሀ/ አቅራቢው በውሉ ጊዜ ውስጥ ባልፈጸመው መጠን ላይ በየቀኑ 1/1000 የጉዳት ካሳ ከክፍያው ላይ ተቀናሽ ማድረግ ይችላል፡፡

ለ/ በዚህ ዓይነት የሚታሰበው መቀጫ ከውሉ ዋጋ 10% የሚበልጥ መሆን የለበትም፡፡

ሐ/ የውሉ አፈፃፀም መዘግየት በሥራው እንቅስቃሴ ላይ የበለጠ ችግር የሚያስከትል ከሆነ የልማት ድርጅቱ የመቀጫው መጠን 10% እስከሚሞላ ድረስ ለመጠበቅ ሳይገደድ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉን ሊያቋርጥ እንደሚችል የሚገልፅ አንቀጽ በውሉ ሊካተት ይችላል፡፡

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ተፈፃሚ የሚሆነው አቅራቢዎች ዘግይተው ለልማት ድርጅቶች በሚፈጽሙት ውል ላይ ብቻ ሲሆን፣ የጉዳት ካሳ ክፍያው ሊቀነስ የሚገባው ለአቅራቢው ከሚከፈለው ቀሪ ክፍያ ላይ ብቻ ነው፡፡

3) አቅራቢው በውሉ መሠረት ዕቃውን፣ አገልግሎቱን ወይም የግንባታ ሥራውን ካልፈጸመ ወይም በውሉ የተቀመጡ ሌሎች ግዴታዎችን ሳይወጣ ቢቀር የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ የውል ማስከበሪያውን በመውረስ ውሉ እንዲቋረጥ ማድረግ ይችላሉ፡፡

## 114. ውልን ስለማቋረጥ

ዝርዝሩ በውል ሰነዱ መሠረት የሚገለጽ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የልማት ድርጅቱ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ ለአቅራቢው ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉን ሊያቋርጥ ይችላል፡፡

ሀ/ አቅራቢው ዕቃውንና ተያያዥ አገልግሎቱን ወይም የምክር አገልግሎቱን ወይም የግንባታ ሥራውን በውሉ መሠረት ካልፈጸመ ወይም ከፍተኛ የውል አፈፃፀም ችግርን ጨምሮ ሌሎች በውሉ የተቀመጡ ግዴታዎችን ሳይወጣ ቢቀር ወይም በህግ የተከለከሉ ተግባራትን ፈጽሞ ቢገኝ ወይም መክሰሩ ወይም በዕዳ መያዙ ከተረጋገጠ፣

ለ/ የልማት ድርጅቱ ከኢኮኖሚ ከበጀት ወይም ከቴክኒክና ቴክኖሎጂ ምክንያቶች አንጻር ውሉን መፈጸም የማይቻል ወይም የማያስፈልግ ሲሆን፣

ሐ/ የልማት ድርጅቱ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 111 ላይ የተዘረዘሩና ከአቅም በላይ ተብለው የተለዩ ሁኔታዎች ምክንያት አቅራቢው ውሉን ለመፈጸም እንደማይችል ሲረጋገጥ፡፡

## 115. ከአቅም በላይ ሁኔታ

1) ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ነው ሊያሰኙ የሚችሉ ምክንያቶች ከሚከተሉት አንዱ ሊሆኑ ይችላሉ፣

ሀ) ውል እንዳይፈጽም በመንግስት የሚደረግ ክልከላ፣

ለ) እንደ መሬት መናወጥ፣ መብረቅ፣ማዕበል እና የመሳሰሉ ተፈጥሯዊ መቅሰፍቶች፣

ሐ) የጠላት፣ የውጭ ሀገር ወይም የሀገር ውስጥ ጦርነት፣

መ) ውል የገባው ወገን መሞት ወይ ባልታሰበ ሁኔታ የሚደርስበት ከባድ አደጋ ወይም ጽኑ ህመም፣

ሠ) በፍትሐብሔር ሕግ የተዘረዘሩ ሌሎች ከአቅም በላይ አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ፣

2) ግልጽ የሆነ ተቃራኒ የውል ቃል ከሌለ በቀር ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ከአቅም በላይ የሆኑ ችግሮች ተደርገው ሊቆጠሩ አይችሉም፡፡

ሀ) በተዋዋይ ፋብሪካ ወይም ስራውን ከሚያከናውንበት ባንደኛው ቅርንጫፍ ውስጥ የተደረገ የሠራተኛ አድማ ወይም የልማት ድርጅቱ መዘጋት፣

ለ) ለውሉ አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑ አቅርቦቶች ዋጋ መወደድ ወይም መርከስ፣

ሐ) ተዋዋይ ያለበትን የውል ግዴታ አፈጻጸም ወጪ የሚያከብድበት አዳዲስ ህግ መውጣት፣

## 116. ማስታወቂያዎችና የጽሑፍ ግንኙነቶች

1) ማንኛውም በውሉ መሠረት በአንዱ ተዋዋይ ለሌላው ወገን የሚሰጠው ማስታወቂያ በውሉ በተጠቀሰው መሠረት በጽሑፍ መሆን አለበት፡፡ በጽሑፉ የተደረገ ግንኙነት ማለት ፅሑፉ ለተቀባዩ መድረሱ ሲረጋገጥ ነው፡፡

2) አንድ ማስታወቂያ ውጤት ሊኖረው የሚችለው ማስታወቂያው በአካል ለተዋዋዩ ሕጋዊ ተወካይ ሲደርስ ወይም በውሉ ላይ በተመለከተው አድራሻ የተላከ ከሆነ ነው፡፡

## 117. የውል አለመግባባቶችን ስለመፍታት

1) ከውል አፈፃፀም ጋር በተያያዘ በልማት ድርጅት እና በአቅራቢዎች መካከል የሚፈጠር ማንኛውም አለመግባባት እስከተቻለ ድረስ በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች ውይይትና ስምምነት መፈታት አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተደነገገው ቢኖርም በልማት ድርጅቱ እና በአቅራቢዎች መካከል የሚፈጠር ማንኛውም አለመግባባትነት በውል ስምምነቱ መሠረት መፈታት አለበት፡፡

## ምዕራፍ ዘጠኝ
## የአቤቱታ እና ይግባኝ  አቀራረብና አወሳሰን ሥርዓት

### 118. አቤቱታና ይግባኝ አቀራረብ ጠቅላ ድንጋጌ

1) ከግዥ አፈጻጸም ጋር በተገናኘ  በልማት ድርጅት የተከናወነ ወይም ሳይከናወን የቀረ ተግባር  የግዥ አዋጅ፣ የግዥ አፈጻጸም መመሪያዎቹንና የጨረታ ሠነዱ ላይ የተመለከቱ ሁኔታዎችን ጥሷል ብሎ የሚያምን እና በዚህም ምክንያት የደረሰበት ወይም ሊደርስበት የሚችል ጉዳት ስለመኖሩ ማሳየት የሚችል   ተወዳዳሪ ለልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ወይም ለይግባኝ ሰሚና ውሳኔ ሰጪ ቦርዱ ሊያቀርብ ይችላል፡ ፡

2) ተጫራቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት አቤቱታ ሊያቀርብ የሚችለው የመንግሥት የልማት ድርጅትከአሸናፊው ተጫራች ጋር ውል ከመግባቱ በፊት ብቻ ነው፡፡

3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ቢኖርም የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ ከልማት ድርጅቱ ጋር ውል ከፈረመ በኋላ የቀረበ አቤቱታ ሊታይ ይችላል፡፡

   ሀ/ ውሉ የተፈረመው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተቀመጠው የአቤቱታ እና ይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ከማለፉ በፊት ከሆነ፣

   ለ/ የጨረታው ውጤት  ከተገለጸ በኋላ ወይም የልማት ድርጅቱ  ለቀረበበት አቤቱታ ምላሽ ከሰጠ በኋላ አምስት (5) ተከታታይ የሥራ ቀናት ከመጠናቀቁ በፊት ውሉ የተፈረመ ከሆነ፣

   ሐ/ በአዋጁና በዚህ የአፈጻጸም መመሪያ መሠረት የጨረታ ውጤት ለተጫራቾች ሳይገለጽ ውል የተፈረመ ከሆነ፣

### 119. አቤቱታን ለልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ስለማቅረብ

1) የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ከግዥ አፈጻጸም ጋር ተያይዘው የሚቀርቡ አቤቱታዎችን አጣርቶ ምላሽ መስጠት አለበት፡፡

2) በልማት ድርጅቱ በተከናወነ ወይም ሳይከናወን በቀረ ተግባር ምክንያት የሚቀርብ አቤቱታ በመጀመሪያ ደረጃ ለልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ መቅረብ አለበት፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በጨረታ ሠነድ ይዘት ላይ ከ ተወዳዳሪዎች በሚቀርብ የማብራሪያና የማሻሻያ ጥያቄ መነሻ ግዥ ፈጻሚው የመንግሥት የልማት ድርጅትየማብራሪያና የማሻሻያ ምላሾች ከሰጠበት ወይም ምላሽ መስጠት ይገባው ከነበረበት ቀን አንስቶ በሚቆጠር አምስት (5) የሥራ ቀናት ውስጥ ተወዳዳሪው ይግባኙን በቀጥታ ለይግባኝ ሰሚና ውሳኔ ሰጪ ቦርዱ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

## 120. አቤቱታ የሚቀርብበት ጊዜ

1) በግዥ አፈጻጸም ሂደት ጉዳት ወይም በደል ደርሶብኛል የሚል ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች ለአቤቱታው መሠረት የሆነውን የመጨረሻ ውሳኔ በይፋ ካወቀበት ወይም ማወቅ ይገባው ከነበረበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር አምስት (5) ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ጨረታውን ላወጣው የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ማቅረብ አለበት፡፡ ከዚህ ጊዜ በኂላ ለልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

2) ጉዳዩ አቤቱታ ባቀረበው ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች እና ጨረታውን ባወጣው የመንግሥት የልማት ድርጅትበስምምነት ካልተፈታ በስተቀር አቤቱታው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ሰባት (7) ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ውሳኔውን እና የውሳኔውን ቅጅ አቤቱታውን ላቀረበው ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች እንዲደርሰው ማድረግ አለበት፡፡

3) የጨረታው ቴክኒካል እና ፋይናንሻል መወዳደሪያ ሠነድ ተለያይቶ እንዲቀርብ የተጠየቀ ከሆነ ተጫራቾች የመጫረቻ ሠነዳቸውን በተለያየ ሁኔታ እንዲያቀርቡ በተደረገበት ጨረታ፣

ሀ/ ማንኛውም ተጫራች የቴክኒክ ግምገማው፣ ወይም ይህንን የአፈጻጸም መመሪያ ወይም የጨረታ ሠነዱን መሠረት አድርጎ አልተከናወነም የሚል ቅሬታ ካለው ቅሬታውን በአምስት (5) የሥራ ቀናት ውስጥ ማቅረብ እንደሚችል የልማት ድርጅቱ የቴክኒክ ግምገማ ውጤቱን ለተጫራቾች በሚያሳውቅበት ወቅት ማመልከት ይኖርበታል፡፡

ለ/ የልማት ድርጅቱ የዋጋ መወዳደሪያ ሰነድ ሊከፍት የሚችለው የቴክኒክ

ግምገማ ውጤቱን ለተጫራቾች ካሳወቀ ከአምስት (5) ቀናት በኋላ ይሆናል፡ ፡ ሆኖም የቴክኒክ ግምገማውን በሚመለከት የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ አቤቱታ ቀርቦ ከሆነ ለአቤቱታው ምላሽ መስጠትና ምላሹን ከሰጠ በኋላ እስከ አምስት (5) የሥራ ቀናት ወይም ደግሞ ለቦርዱ ይግባኝ ቀርቦ ከሆነ ቦርዱ የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ የዋጋ መወዳደሪያ ፖስታ ሳይከፈት ማቆየት ይኖርበታል፡፡

ሐ/ አቤቱቱታ የቀረበበት ማናቸውም ግዥ የሚጣራው ለጨረታው የተዘጋጀውን የጨረታ ሠነድና ይህንን የአፈጻጸም መመሪያ መሠረት በማድረግ ይሆናል፡ ፡

## 121. የግዥ አፈጻጸም ሂደትን ማገድ ስለመቻላቸው

1) ጨረታውን ያወጣው የመንግሥት የልማት ድርጅት አቤቱታውን በዚህ መመሪያ አንቀጽ 115 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ የቀረበ መሆኑን ካረጋገጠ አቤቱታው ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ የጨረታው ሂደት ታግዶ እንዲቆይ ማድረግ አለበት፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው ቢኖርም አቤቱታ የቀረበበት የመንግሥት የልማት ድርጅትጨረታው ከመከፈቱ በፊት የቀረበ አቤቱታ በመሆኑ ምክንያት ጨረታን ከመክፈት እና ከአሸናፊው ድርጅት ጋር ውል ከመፈረም ጋር ከተያያዙ እንቅስቃሴዎች ውጪ ያሉ የጨረታ ሂደቶች ግዥው ሳይታገድ አቤቱታውን ማጣራት ይቻላል፡፡
3) የመንግሥት የልማት ድርጅትለሚቀርብበት አቤቱታ የሚሰጣቸው ማናቸውም ውሳኔ እንዲሁም የውሳኔ ምክንያቶች እና ሁኔታዎች የግዥ ሥርዓቱ አንድ አካል ሆነው መያዝ አለባቸው፡፡

## 122. የአቤቱታ የሚጣራበት ሂደት እና ውሳኔ አሰጣጥ

1) የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ የሚወስነው ውሳኔ የቅሬታውን መነሻ ምክንያት፣ ውሳኔ የሚያስፈልጋቸውን ጭብጦች፣ ትንታኔዎች፣ ከውሳኔ ላይ ለመድረስ ያስቻለውን ሕግና ምክንያት እንዲሁም ማስረጃዎችን የያዘ መሆን አለበት፡፡

2) የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ውሳኔ ለመስጠት አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ከማንኛውም ሰው ማንኛውንም ዓይነት ማስረጃ እንዲቀርብለት በጉዳዩ ላይ የውሳኔ ኃሳብ ከማቅረቡ በፊት የሚመለከተውን ሰው ወይም አካል መጠየቅ ይችላል፡፡

3) የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ቅሬታው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሰባት (7) ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ለቅሬታው ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

4) የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ በቀረበው አቤቱታ ውሳኔ ካልሰጠ፣ አቤቱታ አቅራቢው የሰባት (7) ተከታታይ የሥራ ቀናት ጊዜ ገደብ ከተጠናቀቀበት ቀን ጀምሮ ባሉት አምስት (5) ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ለቦርዱ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

## 123. ይግባኝ ለቦርዱ ስለሚቀብበት አግባብ

1) በዚህ መመሪያ መሰረት ለቦርዱ የሚቀርበው ይግባኝ በአዋጁ የተደነገገው የአቤቱታ ማቅረቢያ እና የውሣኔ አሰጣጥ ዘዴ እንደሁኔታው ማስተካከያ ታክሎበት ለዚህ መመሪያ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው ቢኖርም ይግባኝ የቀረበበት የመንግሥት የልማት ድርጅትጨረታው ከመከፈቱ በፊት የቀረበ ይግባኝ በመሆኑ ምክንያት ጨረታን ከመክፈት እና ከአሸናፊው ድርጅት ጋር ውል ከመፈረም ጋር ከተያያዙ እንቅስቃሴዎች ውጪ ያሉ የጨረታ ሂደቶች ግዥው ሳይታገድ ቀጣይ የግዥ ሂደቶችን መቀጠል ይችላል፡፡

## 124. ይግባኝ ለመደበኛ ፍርድ ቤት ስለማቅረብ

1) በአዋጁ አንቀጽ 81 መሠረት ቦርዱ እንዲሁም በአዋጁ አንቀጽ 84 መሠረት ባለስልጣኑ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማናቸውም ተከራካሪ ወገን ይግባኙን ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊያቀርብ የሚችለው በሕግ ትርጉም ረገድ ቦርዱ በሰጠው ውሳኔ ላይ ብቻ ነው፡፡

2) በቦርዱ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ተከራካሪ ወገን ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ቀጥሎ ባሉት 15 (አስራ አምስት) የስራ ቀናት ውስጥ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

## ምዕራፍ አስር

## የጥፋተኝነት ሪፖርት የሚቀርብበት እና የሚጣራበት ሥርዓት

### 125. የጥፋተኛነት ሪፖርት አጠቃላይ ገጽታ

በግዥ አፈጻጸም ሂደት የመንግሥት የልማት ድርጅትበተጫራቾች ወይም በአቅራቢዎች ሕገ ወጥ የሆነ ወይም ሕጋዊ ጥቅሜን የሚጎዳ ድርጊት ተፈጽሞብኛል ብሎ ሲያምን በጨረታ ሠነዱ ወይም በውል ስምምነቱ መሠረት የሚወስዳቸው እርምጃዎች እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለባለሥልጣኑ የጥፋተኛነት ሪፖርት ማቅረብ ይችላል፡፡

### 126. የጥፋተኝነት ሪፖርት አቀራረብ

1) በማንኛውም የመንግሥት የልማት ድርጅትግዥ ላይ የተሳተፈ ማንኛውም ተጫራች ወይም አቅራቢ በተሳተፈበት ግዥ የሚመራበት ህግ ከሚያዝዘው ውጭ መፈጸሙን ውል ለመፈረም ፈቃደኛ አለመሆኑን፣ ማጭበርበሩን፣ ሀሰተኛ ሠነድ ለውድድር ማቅረቡን፣ መመሳጠሩን፣የሙስና ተግባር መፈጸሙን እና ወይም የገባውን የውል ግዴታ አለመፈጸሙን ማሳየት ከቻለ በጥፋት ፈጻሚው ላይ የጥፋተኝነት ሪፖርት ለባለሥልጣኑ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

2) ባለሥልጣኑ የጥፋተኝነት ሪፖርት ለቀረበበት ማንኛውም ተጫራች ወይም አቅራቢ የቀረበበትን የጥፋተኝነት ሪፖርት መሰረት በማድረግ ያለውን ማስረጃና ማብራሪያ በሰባት (7) ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ እንዲልክ መከታተል አለበት፡፡

3) ባለሥልጣኑ ከልማት ድርጅቱ እንዲሁም ከተጫራቹ ወይም ከአቅራቢው የቀረበለትን መግለጫና ማስረጃዎች ከአዋጁ፣ ከዚህ የግዥ አፈጻጸም መመሪያ፣ከጨረታ ሠነዱ እንዲሁም ከግዥ ውሉ አኳያ በማጣራት የጥፋተኝነት ሪፖርቱ በቀረበ በአሥራ አምስት (15) የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔውን የጥፋተኝነት ሪፖርት ላቀረበው የመንግሥት የልማት ድርጅትእና የጥፋተኝነት ሪፖርት ለቀረበበት አቅራቢ ወይም ተጫራች እንዳስፈላጊነቱ ለሚመለከታቸው ሌሎች አካላት መላክ አለበት፡፡

## 127. የሚሰጡ ውሳኔዎች

1) ማንኛውም ተጫራች ወይም አቅራቢ የግዥውን የግምገማ ውጤት ሆን ብሎ ለማዛባት ወይም ለማስለውጥ በጨረታው ሂደት ወይም በውል አስተዳደር ወቅት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መፈጸሙ ከተረጋገጠ እንደሁኔታው ከሁለት ዓመት ላላነሰ ጊዜ ማንኛውም የመንግሥት የልማት ድርጅትበሚያወጣው ግዥ ላይ እንዳይሳተፍ ለማድረግ ከአቅራቢነት መዝገብ ይሰረዛል፡፡

   ሀ/ የሙስና ተግባር ማለትም በግዥ ሙያ ላይ ለተሰማራ ባለሙያ ወይም ኃላፊ ጉቦ ወይም ማባበያ ወይም ማንኛውንም ዋጋ ያለው ነገር መስጠቱን በማስረጃ ሲረጋገጥ፣

   ለ/ የማጭበርበር ማለትም ሐሰተኛ ወይም ህጋዊ ያልሆነ ሠነድ ማቅረቡ ወይም በባለሥልጣኑ ታግዶ እያለ የእገዳ ጊዜውን ሳያጠናቅቅ በሌላ የመንግሥት የልማት ድርጅትግዥ ጨረታ ላይ ተካፍሎ መገኘቱ ወይም ከውል ውጭ ጥራት የጎደለው ዕቃ ወይም አገልግሎት ወይም የግንባታ ሥራ ወይም የምክር አገልግሎት፣ እውነተኛ ወይም ትክክለኛ አስመስሎ ማቅረቡ ሲረጋገጥ፣

   ሐ/ ከሌሎች ተጫራቾች ጋር ተመሳጥሮ ዋጋን በመወሰን የልማት ድርጅቱ ከነጻ ውድድር ማግኘት የሚችለውን ጥቅም ማሳጣቱ ሲረጋገጥ፣

   መ/ ከልማት ድርጅቱ ሠራተኞች ወይም ኃላፊዎች ጋር በመመሳጠር ከውሉ ውጭ የሆነ ዕቃ ወይም አገልግሎት ወይም የምክር አገልግሎት ወይም የግንባታ ሥራ ማቅረቡ ሲረጋገጥ፣

   ሠ/ በግዥ ሥራ ላይ የተሰማራ ባለሙያ ወይም ኃላፊ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መጉዳትን ወይም ለመጉዳት ማስፈራራት (መዛቱን) ወይም ማስገደዱ ሲረጋገጥ፣

   ረ/ ቀደም ሲል በባለስልጣኑ የተጣለበትን ቅጣት ከፈጸመበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠር በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሌላ ዕገዳ የሚስከትል ጥፋት መፈጸሙ ሲታወቅ፣

2) ማንኛውም ተጫራች ወይም አቅራቢ የሚከተሉትን ተግባራት መፈጸሙ ሲረጋገጥ፣ እንደጥፋቱ ክብደት እየታየ ከስድስት ወራት ያላነሰ እና ከሁለት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ በማንኛውም የመንግሥት የልማት ድርጅትግዥ ላይ እንዳይሳተፉ ለማድረግ ከአቅራቢነት መዝገብ ይሰረዛል፡፡

ሀ/ በገባው ውል መሠረት አቅርቦቱን ወይም አገልግሎቱን ወይም የምክር አገልግሎቱን ወይም የግንባታ ሥራውን ባለማጠናቀቁ ወይም አቅርቦቱን ጀምሮ በማቋረጡ ምክንያት በልማት ድርጅቱ ላይ የገንዘብ ኪሳራ ወይም የስራ መጓተት ወይም የጥቅም ማጣት ካስከተለ፣

ለ/ በጨረታ ውድድሩ አሸናፊ መሆኑ በፅሁፍ ተገልጾለት ውል ለመፈረም ፈቃደኛ ባለመሆኑ ምክንያት የልማት ድርጅቱ ግዥውን ከሌላ ተጫራች በመፈጸሙ ለኪሳራ ወይም የስራ መጓተት ካስከተለበት፣

ሐ/ ከሶስት ዓመት ወዲህ ሌላ ጥፋት ፈጽሞ ከባለሥልጣኑ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት የነበረ ሆኖ አሁን የቀረበበት ሌላ ማስጠንቀቂያ የሚያሰጥ የግዥ አፈጻጸም ጥፋት ፈጽሞ ከተገኘ፣

3) ማንኛውም ተጫራች ወይ አቅራቢ የሚከተሉት ጥፋቶች መፈጸሙ ሲረጋገጥ ማስጠንቀቂያ ሊሰጠው ይችላል፡፡

ሀ/ ውል ገብቶ አቅርቦቱን ወይም የምክር አገልግሎት ወይም የግንባታ ሥራውን በውሉ በተቀመጠው ጊዜ ሳይሆን ዘግይቶ በማቅረቡ ምክንያት በልማት ድርጅቱ ሥራ ችግር መፍጠሩ፣

ለ/ በልማት ድርጅት ፕሮፎርማ እንዲሰጥ ተጠይቆ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆኑ ከተረጋገጠ፣

ሐ/ ተጫራቹ ወይም አቅራቢው ከምርት ልዩነት ወይም ከውጪ ምንዛሬ እጥረት ጋር ተያይዞ ከድርጅቱ አቅም በላይ የሆነ ሁኔታ እንደገጠመው ከሦስተኛ ወገን ማረጋገጫ ያቀረበ እንደሆነ፣

4) ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 በተዘረዘሩት ቅጣቶች መሠረት በባለስልጣኑ የተሰጠው ውሳኔ ግልባጭ በደብዳቤ ወይም የኤሌክትሮኒክ ዘዴን በመጠቀም ለሁሉም የመንግሥት የልማት ድርጅቶች እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

5) ባለሥልጣኑ ከላይ በተመለከተው ሁኔታ የሚሰጠው ውሳኔ እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተጫራቹ ወይም አቅራቢው በፈጠረው ችግር ምክንያት የደረሰባቸው ኪሳራ በግዥ ውላቸው እና አግባብነት ባለቸው ሌሎች ህጎች መሠረት መጠየቅ ይችላል፡፡

6) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የሚያቀርቡት የጥፋተኝነት ሪፖርት የተሟላ ማስረጃ የሌለው እንዲሁም ሪፖርቱን ካቀረቡ በኃላ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ተጨማሪ መረጃና ማስረጃ እንዲያቀርቡ ከባለስልጣኑ ተጠይቀው በወቅቱ ካላቀረቡ ባለስልጣኑ ክሱን ሊዘጋ ይችላል፡፡

## 128. ውሳኔውን እንደገና ማየት

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 153 ንዑስ አንቀጽ ከ1 እስከ 3 የተደነገገው ቢኖርም ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን በስምምነት እልባት የሚሰጡበት፣የጥፋተኛነት ሪፖርት የቀረበበት ድርጅት ጥፋቱን ተቀብሎ ግዴታውን ሲወጣ ወይም ጥፋቱን ሲያርም ባለሥልጣን መ/ቤቱ የሚወስናቸው ውሳኔዎች ከሚከተሉት አንዱ ሊሆን ይችላል፡፡

ሀ) ክሱን ተገቢውን መረጃ በማየት መዝጋት፣

ለ) የሚቀርቡ መረጃዎችን በማጣራት እገዳውን ማንሳት፣

ሐ) የሚቀርቡ መረጃዎችን በማጣራትና ውሳኔውን በድጋሚ በማየት ቅጣቱን ማቅለል፣

መ) የመጀመሪያውን ውሳኔ የሚያስቀየር ባለመኖሩ ቅጣቱን የሚያጸና ውሳኔ፣

2) ባለስልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 84 መሠረት የቀረበለትን የጥፋተኛነት ሪፖርት መርምሮ ውሳኔ በመስጠት ሂደት በወንጀል የሚያስጠይቅ ድርጊት የተፈጸመ መሆኑን ሲያረጋግጥ ጉዳዩን ለመመርመር እና እርምጃ ለመውሰድ በሕግ ስልጣን ለተሰጠው የህግ አስፈጻሚ አካል ያሳውቃል፡፡

## 129. መረጃን ስለማቅረብ

ባለስልጣኑ በአዋጁ መሠረት የቀረበለትን የጥፋተኛነት ሪፖርት መርምሮ ውሳኔ በመስጠት ሂደት በወንጀል የሚያስጠይቅ ድርጊት የተፈጸመ መሆኑን ሲረዳ አግባብነት ላለው የመንግስት አካል መረጃ መስጠት አለበት፡፡

## ምዕራፍ አስራ አንድ
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 130. የተሻሩ መመሪያዎች

በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ፣ አሠራር፣ ልማድ ወይም ሰነድ በዚህ መመሪያ ተሽሯል::

## 131. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተጀመሩ የግዥ ሂደቶች፣ ውሎች እና የግዥ አቤቱታዎች የመንግሥት የልማት ድርጅቶቹ ባወጧቸው መመሪያዎች መሠረት ፍፃሜ ያገኛሉ፡፡

## 132. መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በገንዘብ ሚኒስቴር የድህረ ገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ፣ ግንቦት 18 ቀን፣ 2017 ዓ.ም.

አህመድ ሺዴ
የገንዘብ ሚኒስትር

አባሪ -1

**<u>የቀድሞ ሰራተኞች በጨረታ ስለሚሳተፉበት አግባብ</u>**

**በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት የቀድሞ ሰራተኞች ላይ ሊፈጠር የሚችለውን የጥቅም ግጭት ለመከላከል የሚሞላ ቅጽ ነው፡፡**

በልማት ድርጅቱ የቀድሞ ሠራተኛ የሚሰጥ መረጃ፣

1. በተቋሙ ስራ የጀመረበት ጊዜ------------------------------------------

2. ተቋሙን የለቀቀበት ጊዜ-----------------------------------------------

3. ከጨረታው ጋር በተገናኘ ምንም አይነት የጥቅም ግጭት የለብኝም፡፡

4. በጨረታ ሰነዱ ውስጥ የሰፈሩትን መስፈርቶችን አሟላለሁ፡፡

5. ጨረታውን በተመለከተ የሰጠሁት መረጃ ትክክለኛ ነው፡፡

ከጨረታው ጋር በተገናኘ የሰጠሁት መረጃ በአጠቃላይ እውነትና የተረጋገጠ ሲሆን በልማት ድርጅቱ የሚያሳስቱ እና ውሸት ሆኖ ቢገኝ ከዚህ የጨረታ ሂደት ውጪ እንደምሆን በተጨማሪም የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በሚያወጣቸው ጨረታዎች እንዳልሳተፍ እንደጥፋተኛነት በመቁጠር ሪፖርት ለመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን በማቅረብ በልማት ድርጅቶች ግዥዎች ቢታገድ የማልቃወም መሆኑን እና ከላይ የተዘረዘሩትን ግዴታዎች ማሟላቴን እንዲሁም ከዚህ የመንግሥት የልማት ድርጅትከለቀቅሁ ከአንድ ዓመት በላይ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም-----------------------------------------------

ኃላፊነት-------------------------------------------

ፊርማ---------------------------------------------

አባሪ -2

<u>የግዥ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች የጥቅም ግጭት፣</u>

በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 27 **ንዑስ አንቀጽ 1** መሰረት ከግዥ ጋር በተገናኘ የሚሳተፉ ባለሙያዎችና ኃፊዎች የጥቅም ግጭት አለመኖሩን ከዚህ በታች የተዘረዘዘሩትን በፊርማቸው በማረጋገጥ መሆን ይገባዋል፡፡

1. ከግል ጥቅማቸው ጋር የተተያያዘ እና ኃላፊነታቸውን በትክክል እንዳይወጡ የማድረግ ውጤት ያለው ወይም የዚህ አይነት ውጤት ሊያስከትል የሚችልን ማናቸውም ሁኔታ ከግምገማው ጋር በተያያዘ አለመፈጠሩን ማረጋገጥ፣
2. ከግዥ ግምገማው ጋር በተያያዘ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል ስጦታ አለመቀበላቸውን ማረጋገጥ፣
3. ከግዥ ፈፃሚው የመንግሥት የልማት ድርጅትበጽሑፍ ካልተፈቀደላቸው በስተቀር መረጃውን ለሦስተኛ ወገን አሳልፈው መስጠት አለመስጠትና ከሥራው ጋር በተያያዘ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያገኙትን መረጃ በምስጢር መጠበቅ፣
4. ከተጫራቾች የሚቀርብን የመጫረቻ ሠነድ ያለምንም አድሎ እና ልዩነት መመዘን እና ውጤቱን አለማዘባት፣
5. በግምገማ ላይ የሚሳተፍ ማንኛውም ሰው በጨረታ ሠነድ ዝግጅትም ሆነ ዋና ዋና የፍላጐት መግለጫ ዝግጅት ወቅት ያልተሳተፈ መሆኑን ማረጋገጥ፣
6. ከላይ ከተዘረዘሩት አንዱን መከሰቱን ካረጋገጠ የጊዜያዊ ኮሚቴ አባሉ ለወከለው የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ በጽሁፍ በማሳወቅ ከግዥ ሂደቱ እራሱን ማግለል አለበት፡፡ ሆኖም እራሱን የሚያጋለው የኮሚቴ አባል እራሱን ከስራ ለማሸሽ መሆን ግን የለበትም፡፡

ስለሆነም የኮሚቴው አባላት ከላይ የተዘረዘሩትን አንብበው መስማማታቸውን በፊርማቸው ያረጋግጣሉ፡፡

የኃላፊው/የባለሙያው ስም _________ የሥራ መደብ _________________________ አድራሻ _________________________ የስልክ ___________ የኢ-ሜይል ___________________ቀን _________

አባሪ -3

<u>ጨረታ ተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ የሚቆይበት ጊዜ</u>

በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 78 ንዑስ አንቀጽ 1 (ለ) በተገለፀው መሰረት ተጫራቾች የመጫረቻ ሰነዳቸውን ማዘጋጃና ማቅረቢያ አነስተኛው ጊዜ ከዚህ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

| ተራ ቁጥር | የግዥው ዓይነት | ውስብስብነት | ግልጽ ጨረታ | | የተገደበ ጨረታ | | ዋጋ ማቅረቢያ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዓለም አቀፍ | ብሔራዊ | ዓለም አቀፍ | ብሔራዊ | |
| 1 | የግንባታ ዘርፍ ሥራ | ውስብስብ | 30 | 20 | 30 | 20 | 2 ቀናት |
| | | ውስብስብ ያልሆነ | 20 | 15 | 15 | 20 | |
| 2 | ዕቃ | ውስብስብ | 20 | 15 | 20 | 15 | |
| | | ውስብስብ ያልሆነ | 15 | 10 | 15 | 10 | |
| 3 | ሌሎች አገልግሎቶች | ውስብስብ | 30 | 20 | 30 | 20 | |
| | | ውስብስብ ያልሆነ | 15 | 10 | 15 | 10 | |
| 4 | የምክር አገልግሎት<br>• የፍላጎት መግለጫ (EOI) | ውስብስብ | 10 | 7 | | | |
| | | ውስብስብ ያልሆነ | 7 | 5 | | | |
| | • የመወዳደሪያ ሀሳብ ማቅረቢያ | ውስብስብ | 30 | 20 | 30 | 20 | |
| | | ውስብስብ ያልሆነ | 15 | 10 | 15 | 10 | |

አባሪ -4

**<u>በተጫራቾች የሚሞላ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ቅጽ</u>**

በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 86 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በተጫራቾች የሚሞላ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ቅጽ ነው፡፡

የግዥው መለያ ቁጥር……(የጨረታ መለያ ቁጥር ይግባ)

ለ…………………………………( የመንግሥት የልማት ድርጅትሙሉ ስም ይግባ)

/የተጫራቹ ሙሉ ስም ይግባ/ ከአሁን በኂላ "ተጫራች" እየተባለ የሚጠራው በግዥ መለያ ቁጥር ……………….(የግዢ መለያ ቁጥር እና የዕቃዎችና ተያያዥ አገልግሎቶች…….. (አጭር መግለጫ ይግባ) ከአሁን በኂላ ጨረታው እየተባለ የሚጠራውን ለማቅረብ በ…………………./የጨረታ ማስረከቢያ ቀን……/…….ወርና……ዓ.ም…..አስገባ/ የተጻፈውን ጨረታ ያስገባን ስለሆነ እኔ ………………………………………./የድርጅቱ ስምና ባለቤት ወይም የመፈረም ሥልጣን ያለው ኃላፊ ስም አስገባ/ ከዚህ በታች የተገለጹት ሁኔታዎች ሲሟሉ የተጠቀሰውን የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና/ የጨረታ ዋስትናው መጠንና የገንዘቡት ዓይነት በቃላት እና በቁጥር ግልጽ/ ሙሉ ኃላፊነት ድርጅቱ የሚወስድ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የዋስትና ሰጪው የተለመደ ማህተብ ተደርጎበት/ዋስትናው የሚቆይበት የቀን ብዛት በቁጥር፣ በወር ወይም በዓመት መሆኑ ተለይቶ ይገለፅ/ ይታሽጋል፡፡

**የሚከተሉትን ግዴታዎች በመረዳት ተፈጻሚ ለማድረግ ተስማምቻለሁ፡፡**

ሀ/ በጨረታ ሠነዱ የተገለጸው የመጫረቻ ሠነድ ማቅረቢያ የመጨረሻ ቀን ካለፈ በኂላ ወይም በመጫረቻ ሠነዱ የተገለጸው የጨረታ ዋጋ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ከጨረታው እራሴን ላለማግለል፣ ወይ

ለ/ በመጫረቻ ሠነዱ የተገለጸው የመጫረቻ ዋጋ ጸንተ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ የግዥ ውል እንድፈርም የቀረበልኝን የጽሁፍ ጥያቄ በመቀበል ውል ለመፈረም ፈቃደኛ ለመሆን፣ ወይ

ሐ/ በጨረታው ውድድር አሸናፊ በመሆኔ ውል እንድፈርም እና የውል ማስከበሪያ እንዳስይዝ ስጠየቅ የውል ማስከበሪያውን ለማስያዝ ፈቃደኛ ለመሆን፣ እና ከላይ በፊደል ተራ ሀ እስከ ሐ እና በጨረታ ሠነዱ የተገለጹትን ሌሎች ተግባራት ባልፈጽም የልማት ድርጅቱ በሚያቀርበው የጽሁፍ ጥያቄ ከላይ የተገለጸውን የጨረታ ማስከበሪያ የገንዘብ መጠን ለመ/ቤቱ ወዲያውኑ ለመክፈል ተስማምቻለሁ፡፡

ይህ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ጨረታው ጸንቶ ከሚቆይበት ጊዜ በተጨማሪ ለ28 ቀናት በህግ ፊት ጸንቶ ይቆያል፡፡ ይህን ዋስትና በተመለከተ ከተጠቀሰው ጊዜ ዘግይቶ የሚቀርብ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡

ስም……………………..(ጨረታውን የሚፈርመው ሰው ሙሉ ስምና ሕጋዊ ሥልጣን ይግባ)

ፊርማ …………………(ስምና ማዕረጉ ከላይ የተጠቀሰው ሰው ፊርማ ይግባ) ፈ

ወይም (ወኪል ከሆነ ጨረታውን ለመፈረም ህጋዊ ሥልጣን የተሰጠው ሰው ሙሉ ስምና ፊርማ ይግባ)

ቀን…………………… (የተፈረመበት ቀን፣ ወር እና ዓመተ ምህረት ይግባ)

**አባሪ -5**

## <u>በተጫራቾች የሚሞላ የውል ማስከበሪያ ዋስትና ቅጽ</u>

በግዥ አፈጻጸም *መመሪያው* አንቀጽ 102 ንዑስ አንቀጽ 2 *መሠረት* በተጫራቾች የሚሞላ የውል ማስከበሪያ ዋስትና ቅጽ ነው፡፡

*ቀን*-------------------------------------የግዥ *መለያ* ቁጥር:- --------------------------------------------

ለ:-------------------------------------------------------------------- *[የግዥ ፈፃሚ የመንግሥት የልማት ድርጅትሙሉ ስም ይግባ]*

<u>*የአማካሪው ሙሉ ስም ይግባ*</u> (ከዘህ በኋላ "አማካሪ" እየተባለ የሚጠራ) በቀን---------- ወር___ ዓ.ም.____ በተፈረመው ውል ቁጥር-----------------------(ካሁን በኋላ "ውል" እየተባለ የሚጠራው) *መሠረት የአገልግሎቶች ዝርዝር ይገለጽ (--------------------------------------------- --------------------------------------)* ለማቅረብ ግዴታ የገቡ ሲሆን፣

በተጠቀሰው ውል ውስጥ እርስዎ አማካሪው ለገቡበት የውል ግዴታ ይሆንዎ ዘንድ *የዋስትና አይነት ይገለጽ (-----------------------------------------------------------------------------------)* ከታወቀ ዋስትና ሰጭ መጠኑ ለተጠቀሰው ገንዘብ የውል ማስከበሪያ ዋስትና እንዲያቀርቡ አጥብቀው የጠየቁ ስለሆነ፡፡

እኛ ከዘህ በታች ፊርማችንን ያኖርንና ህጋዊ አድራሻችን----------------------------------------------- ----------- <u>*የዋሱ ሙሉ ስም ይግባ*</u> <u>*ሕጋዊ የመኖሪያ አድራሻው*</u> *(ሙሉ የዋሱ አድራሻ ይግባ)*፣ የሆንን (ካሁን በኋላ "ዋስ" እየተባለን የምንጠራው) ለአማካሪው ዋስትና ለመስጠት የተስማማን ስለሆነ፣

ስለዚህ እኛ አማካሪውን በመወከል እስከ *የዋስትናው የገንዘብ ዓይነትና መጠኑ በአሀዝ እና በፊደል ይግባ* (-----------------------------------------------------------) ለሚደርስ ዋስትና ተጠያቂ

መሆናችንንና አማካሪው ውሉን መጣሱን በመግለጽ የክፍያ ጥያቄ በጽሑፍ እንደቀረበልን ያላንዳች ማስረጃና ክርክር ክፍያ ለተጠየቀበት ምክንያት እስከ *የዋስትናው መጠን በአሀዝና በፊደል ይግባ* ----------------------------- የሚደርስ ለመክፈል ግዴታ እንገባለን፡፡

ይህ ዋስትና የሚፀናው እስከ ቀን---------------- ወር------------ ዓ.ም----------ድረስ ይሆናል፡፡

ስም-------------------------------------(ጨረታውን የሚፈርመው ሰው ሙሉ ስምና ሕጋዊ ሥልጣን ይግባ)

ኃላፊነት፡---------------------------------------------[ዋስትናው የሚፈርመው ሰው ኃላፊነት ይግባ]

ፊርማ …………………(ስምና ማዕረጉ ከላይ የተጠቀሰው ሰው ፊርማ ይግባ)

ዋስትናው ለመፈረም ሙሉ ውክልና የተሰጠው አካል-------------------------------------------- [የተጫራቹ ሙሉ ስም ይግባ]

ቀን------------------------------------------- (የተፈረመበት ቀን፣ ወር እና ዓመት ምህረት ይግባ